# ልጅን እንዴት ላሳድግ

## በምዕራብ አገሮች

ረጅም ባልተጓዙበት ዕድሜ፣ ሠፊና ድንቅ ቁም ነገር መቋጨት ለሁሉም የተሰጠ ጸጋ አይደለም። የሐምራዊት መጽሐፍ ማንኛውም ቤተሰብ ሊያነበውና ሊጠቀምበት የሚገባ እውነታዎች ያዘለ ነው። ደጋግሞ ይባርካትና የተባረከ በረከት እንድትደጋግመን ያብቃት።

*ወይዘሮ አለምጸሐይ ወዳጆ*
*አርቲስት*

ወላጅነት አሳዳጊነት ውል እንደጠፋው ልቃቂት እየተውተበተበ ባለበት በዚህ የጭንቅ ሰዓት እንደዚህ መጽሐፍ ዐይነት አስተዋይና ደፋር ድምፅ ማግኘት እንዴት ጥሩ ነገር ነው! የሐምራዊት መጽሐፍ በጣም ብርቱ ርዕሰ ጉዳይ ይዞአል፤የያዘውን ጉዳይ በርጋታና በጨዋነት ያስተነትናል ፤ለዛሬ የሚሆን ተግባራዊ ምክር ይለግሣል፤ እቅጩን ለመንገር አይፈራም፤በሰሜን አሜሪካ ብቻ ሳይሆን ቁስ አምላኪነት (materialism) በገነነባቸው የትም ቦታዎች ለሚገኙ ሁሉ በጣም ጠቃሚ መጽሐፍ ነው:: ምነው ቀደም ብዬ ባገኘሁት ለሚሉ አዛውንት ወላጆች; በተረፈው ጊዜም እንኳ ለመጠቀም አታመንቱ እላለሁ::

*አቶ ንጉሤ ቡልቻ*
**ከቃለ-እግዚአብሔር አንባቢዎች ማኅበር**

ርእስ፤ ልጅን እንዴት ላሳድግ፤ በምዕራብ አገሮች
ጸሐፊ፤ ሐምራዊት ተስፋ

አሳታሚ ሞሪስ ቡክ ፓብሊሺንግ

Printed in the United States by Morris Publishing®
3212 East Highway 30
Kearney, NE 68847
1-800-650-7888

አስተያየት ወይም ጥያቄ ካለዎት፤በሚቀጥለው አድራሻ ይጻፉ
hamrawittesfa@yahoo.com


*ያለ አሳታሚው ፍቃድ አብዝቶ ማሳተም የተከለከለ ነው። በማንኛውም መልኩ መረጃዎችን ለመውሰድ ከተፈለገ፣ ሥርዐቱን ጠብቆ ሊጠቀስ፣ በግርጌ ማስታወሻ ሊመላከት ይገባዋል።*

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system or transmitted in any form or by any means-electronic mechanical photocopying recording or other wise-without the prior written permission of the copy right owner.






# አበርክቶት



በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ ላለውና በሕይወት አካሄዱ አቅጣጫዬን ለቀረጸው ለአባቴ፣ ለአቶ ተስፋ ገብረማርያም ይሁንልኝ።



በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ ላለውና በሕይወት አካሄዱ አቅጣጫዬን ለቀረጸው ለአባቴ፣ ለአቶ ተስፋ ገብረማርያም ይሁንልኝ።

# ምስጋና

መጀመርያ፣ አነሳሥቶ ላስጀመረኝ፣ አስጀምሮም ላስጨረሰኝ ቸሩ እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው ማለት እወዳለሁ።

ቤተሰቦቼ ማለትም እናቴ ወይዘሮ ፍቅርተ ገብረ ማርያምና አቶ ንጉሤ መንገሻ ለሰጣችሁኝ ልባዊ ፍቅርና ድጋፍ ከልብ አመሰግናለሁ። ባገር ቤትም ሆነ በውጭ ያላችሁ ዘመዶቼ ለሕይወቴ ላበረከታችሁት አዎንታዊ ተጽእኖ በሙሉ፣ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፤ የቁራ ሰፈር ቤተሰቦቼ በልቤ ውስጥ ያላችሁን ትልቅ ስፍራ ቃላት አይገልጸውም፤

እኅቴ ሰድሴ በሕይወት ገጠመኞቼ ሁሉ ከጎኔ ሆነሽ አብረሽኝ ስለቆምሽ፣ እኅቴ ሰብለ፣ ደጋፊ አበረታቼ ስለሆንሽልኝ፤ አባቡ ሚንዳ በሕይወቴ ውስጥ ስላሳደርከው አዎንታዊ ተጋቦት፣ ዶ/ር ዓለሙ ቢፍቱና ወይዘሮ ውድነሽ ማሩ እምነታችሁ ከልባዊ ፍቅርና አገልግሎት ጋር የተቈራኘ ተምሳሌታዊ አገልግሎት በመሆኑ፣ አቶ በየነ ገብራይ አባታዊ ምክርህና ድጋፍህ ለዓመታት አብሮኝ ስለኖረ፣ ጸጋ ተስፋዬና ኤርምያስ ተስፋዬ በብዙ ስለደገፋችሁኝና ከጐኔ ስለቆማችሁ፣ ወይዘሮ ጸሐይነሽ መልሰቦ በጸሎትና ድጋፍ ከጎኔ ስለነበሩ ከልብ አመሰግናለሁ።

አቶ ብርሃኑ በላይነህ (ሻለቃ) ድጋፍህ ወሰን የሌለው ስለነበረ፤ የዚህ መጽሀፍ እዚ ደረጃ የመድረስ ምክንያቱ ስለሆነ፣ አቶ ተስፋዬ ሮበሌ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል በአርትኦቱ ሥራ ስለረዳኸኝ፣ አቶ ዮናስ አስፋው በአርትኦት ሥራው ውስጥ ስለነበረው ትልቅ ተሳትፎ አቶ ወርቃፈራሁ ከበደ የእንግሊዘኛ ጽሁፎችን ባማረ አማርኛ በመተርጎም ስለተባበርከኝ፤ ከልብ አመሰግናችኋለሁ፤ ዕድሜና ጤና ይስጣችሁ ብል ያንስ ከሆን አይበዛም፡

የጊዜ ጥበት ሳይበግራችሁ፣ የጽሑፉን ረቂቅ በማንበብ አስተያየት የሰጣችሁኝን ውድ ወገኖቼን ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ።።

የሚሺጋን፤አናርበር ኮሚኒቲ፣ በተለያየ መንገድ ያገዛችሁኝ ወገኖቼ፣ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ።

በአንዳንድ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸው ሕይወታቸውንና ገበናቸውን ገላልጠው ላጫወቱኝ ወንድም እኅቶቼ ያለኝ አድናቆትና ከበሬታ እጅግ ታላቅ ነው:: የእናንተ ታሪክና ተሞክሮ ለሌላው ሕይወት ትልቅ ፋና ወጊ ብርሃን ፈንጣቂ እንደሚሆን አልጠራጠርም::

ባላችሁ በቻላችሁት ለሕዝብ ላገራችሁ እያበረከታችሁ ላላችሁ ለውድ ወገኖቼ፣በራሴና በአገሬ ሕዝብ ስም ሆኜ ልባዊ ምስጋናን አቀርባለሁ።

ሐምራዊት ተሰፋ





# ማውጫ


**መቅድም**------------------------------------------9

**መግቢያ**------------------------------------------11

**የውጭ አገሩ ሕይወታችን**------------------16

**ምዕራፍ አንድ:– መልካም የልጅነት ሕይወት**-----------------------------------22

**ምዕራፍ ሁለት:– የልጆች ለቁም ነገር መብቃት**-----------------------------------41

**ምዕራፍ ሶስት:– የልጆች ራስን ችሎ መቆም**-------------------------------56

**ምዕራፍ አራት:–ፍሬያማነት በልጆች ሕይወት**----------------------------------72

**ምዕራፍ አምስት:–ተግጋሮቶችን የሚቋቋሙ ልጆችን ማፍራት**-------------------122

ምዕራፍ ስድስት:–ልጆቻችንን በሥነ ሥርዐት አስታጥቆ ማሳደግ----------155

ምዕራፍ ሰባት:–በቤት ውስጥ ችግር ቢገጥም-----------------------------------170

ምዕራፍ ስምንት:–ልጆቻችን የባህሪ ለውጥ ሲያሳዩ------------------------------------------181

ምዕራፍ ዘጠኝ:–የወላጅን የግል ሕይወት በተመለከተ---------------------------------------199

ምዕራፍ አስር:–ወላጅን እና ልጆችን ለመርዳት የማህበረሰቡ ሚና ---------------204

ጠቃሚ ድረገጾች/መጽሐፍት-----------------227

ዋቢ መጽሐፍት----------------------------231





# መቅድም

ይህን መጽሐፍ መጻፍ ለምን አስፈለገ? በመሠረቱ ይህን መጽሐፍ የመጻፍ ዐላማ አልነበረኝም። በሌላ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ፣ ሌላ መጽሐፍ የመጻፍ ዕቅዱና ፍላጎቱ ግን ነበረኝ፤ የተወሰነም ነገር በመጻፍ ላይ እገኝም ነበር። ዓመት ከመንፈቅ በፊት፣ ለወላጆች የሚሆን መልእክት ማዘጋጀት እንዳለብኝ፣ ሐሳብ ወደ ልቤ ይመጣ ጀመር። በየሰንበቱ ወደምሄድባት ቤተ ክርስቲያን በአንድ ገጽ ወረቀት የሰፈረች ለወላጆች የምትሆን መልእክት አዘጋጅቼ በታዳሚው ፊት አነበብሁ። ሁለት ሦስቴ ይህንኑ አደረግሁ።በውስጤ ያለው ሸክም ግን ከመቅለል ይልቅ እየከበደ መጣ።መልእክቱ የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ወላጆች ብቻ ሳይሆኑ ብዙ ሰዎች የሚሰሙበትን መንገድ ማውጠንጠን ጀመርሁ።

አንኳር አንኳር የሆኑትን ነጥቦች በአንድ ገጽ ወረቀት ላይ አስፍሬ፣ ኢትዮጵያውያን ወላጆች በብዛት ወደሚገኙበት ቦታ በኢሜል እንዲሁም በፋክስ መላክ ጀመርሁ። ወረቀቷን የላኩላቸው ሰዎች በአካል የማውቃቸው አልነበረም፤ እነዚህም ሰዎች ወረቀቱን እያባዙ እንዲያሠራጩ ነገርኋቸው። ዞሮ ዞሮ ቀዳማይ ዐላማዬ፣ በወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ሐሳብ ሰዎች ገንዘባቸው እንዲያደርጉት መጓጓቴ ነው። ወደ ዐሥር የሚሆኑ ቦታዎች ላክሁ። ከላክሁባቸው ቦታዎች መኻል አንድ ሰው፣ "ይህን ጽሑፍ የበለጠ አፋፍተሽው፣ ወደ መጽሐፍ ለምን አትቀይሪውም" ሲል ሐሳብ አቀረበልኝ። ከዚህ በፊት አስቤው ያልነበረ ሐሳብ ስለሆነ፣ የተቀበልሁት በግማሽ ልብ ነበር። በሌላ ርእሰ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ለማዘጋጀት እየሞከርኩ የነበረ መሆኑም፣ ምክሩን ወዲያው እንዳልቀበል ምክንያት ነበር። ለእእምሮዬ ይህን ልበለው እንጂ፣ ልቤ ግን ሊያርፍ አልቻለም።

የቅርብ ባልንጀራዬም ይህንኑ ሐሳብ በመድገም፣ "ይህን ጽሑፍ ወደ መጽሐፍ ብትቀይሪው መልካም ይመስለኛል" ስትል ለሁለተኛ ጊዜ ልቤን አንኳኳችው። እኔም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ እነዚህ ወገኖቼ የሰጡኝን ምክር በመቀበል፣ በርእሰ ጉዳዩ ላይ መጽሐፍ ማዘጋጀት እንዳለብኝ ውስጤ ተነሣሣ። በዚህ ጉዳይ ላይ ለወላጆች ተብሎ የተጻፈ ትምህርት ሰጪ መጽሐፍ እኔ በግሌ ያለማግኘቴ

ጉዳዩ አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ወቅታዊም እንደ ሆነ ተሰማኝ። እነሆም ዛሬ ይህችን የመጀመሪያ መጽሐፌን ለማስነበብ ዕድል አገኘሁ።

ግማሹን የልጅነት ዘመኔን ያሳለፍሁት በምድረ ኢትዮጵያ ነው። አባቴ፣ እኔንና ሁለት ወንድሞቼን ያሳደገን ብቻውን ነበር። ፍቅርን መግቦ ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ያሳየን የነበረውም አክብሮት በቀላል የሚገመት አይደለም። ዘወትር ይገልጽልን የነበረው ፍቅር፣ እንዲሁም ከእኛ ጋር ያሳልፍ የነበረው ጊዜ፣ ሕይወቴ የለመለመ እንዲሆንና የልጅነት ዘመኔንም በደስታ እንዳስታውሰው ያደርገኛል። አባቴ ቱጃርም ሆነ የተረፈው ሰው አልነበረም። ነገር ግን ያሳየን ፍቅር እንዲሁም ይሰጠን የነበረው ጊዜ፣ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ነገር ትቶ አልፏል። ይህም ከራሴ ባለፈ ለማኅበረሰቤ እንዳስብ ጥሩ መደላድል ያደረገ ይመስለኛል።

በዐሥራዎቹ ዕድሜዬ ወደዚህ ወደ አሜሪካን አገር መጣሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ፣ ከማላውቃት እናቴ ጋር አብሬ መኖሬ፣ የዕድሜ ፈተና የባህል ችግር ወዘተ ተደማምሮ ልጅ ሊያጋጥመው የሚችለውን ፈተና አልፌበት አይቼዋለሁ። እንደ ብዙዎቹ የአገሬ ልጆች፣ ራሴን ችዬ ለመቆም ፈተና ውስጥ ገብቼ አውቃለሁ። እኔ ካለፍሁበት ፈተና በተጨማሪ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ከብዙ ጓደኞቼ ጋር ተወያይቼአለሁ ከወላጆች ጋር ስላለው ያለመግባባት እንዲሁም በሌላ ባህል ውስጥ የመኖር ፈተና እጅግ ፈታኝ እንደ ሆነ ከብዙ ኢትዮጵያውያን ሰምቻለሁ። ከላይ የዘረዘርኋቸው ጉዳዮች ለዚህ አርዕስት ትልቅ ፍላጎት እንዲኖረኝ የበኩላቸውን ድርሻ ያበረከቱ ይመስለኛል።

የተማርሁት የማኅበረሰብ ጥናት ነው። በራስ ተሞክሮ እንደሚገኘው ዐይነት ዕውቀት በትምህርት ቤት ሊገኝ ባይቻልም፣ በተሞክሮዬ ያገኘሁትን ዕውቀት በጥልቀት እንዳጤነው ትልቅ በር ከፍቶልኛል። በተለይ ወላጆች በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ ልጆቻቸውን የማሳደግ ኀላፊነታቸውን እንዴት መወጣት እንደሚችሉ እንዲሁም ዕርዳታ ሊያገኙባቸው የሚችሉባቸውን ማኅበራዊ ተቋማት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ጥሩ ግንዛቤ ሰጥቶኛል። ስለዚህ በቀለም ትምህርትም ሆነ ከተሞክሮዬ ያገኘሁት ዕውቀት በተወሰነም መጠን ይህን መጽሐፍ እንዳዘጋጅ ክህሎት የሰጠኝ ይመስለኛል። አንባብያን ከዚህ መጽሐፍ ጠቃሚ ምክር እንዲያገኙበት ናፍቆቴ ነው።





# መግቢያ

ኢትዮጵያ ሄደን፣ "በምዕራብ አገሮች የኑሮ ሁኔታ እንዴት ይመስሎታል?" ብለን አብዛኛውን ሰው ብንጠይቅ፣ "እንዴ እዚያማ ምን ችግር አለ! ሁሉ ነገር የተመቸ አይደል እንዴ?" የሚል ምላሽ ማግኘታችን እሙን ነው። እኛ ግን፣ ኑሮ ከዚያ ሆነው እንደሚያስቡት፣ በዐይነ ኅሊና እንደሚያዩት ቀላል እንዳልሆነ፣ የራሱ የሆነ ሸክምና የራሱ ፈተና እንዳለው ተረድተናል።

በተለያየ መንገድ የተወለድንበትን አገር ጥለን፣ እዚህ ውጭ አገር ሰፍረናል። አንዳንዶቻችን ሳንወድ በስደት፣ ሌሎቻችን ፈልገንና ጓጉተን በስንት ጥረት፣ አዲስ አገር መጥተናል። ጉዳያ የአመጣጣችን ምክንያት ይለያይ እንጂ፣ ሁላችንም ያስተዋልነው አንድ እውነት አለ። ይኸውም፣ በውጭ አገር ስንኖር፣ ሁሉ በእጅ፣ ሁሉ በደጅ እንዳልሆነ በተመክሯችን አይተነዋል። እነዚህ አገሮች የሰጡን ብዙ ጥሩ ነገር እንዳለ ሁሉ፣ ከውጭ ለሚያየው፣ ብዙ ጊዜ ተገልጦ የማይታይ የየራሳችን ሸክም አለብን።

ዘመዶቻችንን እና ወዳጆቻችንን እንናፍቃለን። በአካል ከአገራችን የመጣን ቢሆንም ኅሊናችንና ሐሳባችን ግን አዘውትሮ ወደዚያው መለስ ቀለስ ማለቱ አልቀረም። ናፍቆት ሆዳችንን እያባባ ሁሉ፤ ትተነው ወደመጣነው በትዝታ እንድንነጉድ ያደርገናል።

አብዛኞዎቻችን ለመጣንበት ሀገር እንግዳ፣ ለባሕሉም ፈጽሞ ባዕድ ነን። ኑሮን የጀመርነው እንደ አዲስ ነው። የአገሩ ተወላጆች በተወለዱበት፣ ባደጉበትና በለመዱት ምድርና ባሕል ዘና ብለው ይኖራሉ። እኛ ግን ለቋንቋው፣ ለባሕሉ፣ ለሠፈሩ፣ለሥራው እና

ለአኗኗሩ ባይተዋር ነን። ሰው ከልጅነት ሕይወት በኋላ ዐዋቂ በሆነበት ወቅት ሁሉን ነገር እንደ አዲስ ሲጀምር ቀላል አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ፣ አገር ቤት የነበረን የቤተሰብና የጓደኛ ድጋፍ እዚህ የለንም። እዚህ ቤተሰብና ጓደኛ ቢኖረንም እንኳ፣ በቁጥር ጥቂትና አብዛኛው በየራሱ የሕይወት ሩጫ ዙርያ የተጠመደ ነው። ስለሆነም ይህንን አዲስ ሕይወት ብቻችንን እየተጋፈጥን ነው። ኑሯችንን ሊያከብድብን የሚችለው ናፍቆት፣ ብቸኝነትና ባይተዋርነት ብቻ አይደለም። በአሜሪካ፣ ሕይወት ፋታ የማይሰጥ ዕረፍት የሌሽ ነው። አኗኗሩ የሚያሯሩጥና አእምሮን ወጥሮ የሚይዝ ነው። እንዲህም ሆኖም፣ በአገራችን የምንረዳቸውና የእኛን እጅ የሚመለከቱ ወዳጅ ዘመዶች አሉ። ይህ ሁሉ ቀላል አይደለም። ምንም እንኳን ጥሩ በልተን ጥሩ ለብሰን ብንታይም፣ በውስጣችን ግን ለዐይን የማይታይ ሸክም አለብን።

ይሁንና ይህ ሁሉ እንዲህ ሆኖም፣ ይኸው በሕይወት ሰንብተናል፤ አሀዱ ብለን የጀመርነውን ኑሮ ተላምደነው፣ ሌውንም እያስለመድን ዘልቀናል። የእኛንም ፈለግ የሚከተሉ ልጆች አፍርተን በሕይወት ጉዞ ላይ እንገኛለን። ወደ ፊት እየተራመድን ነው፤ ደግሞም ወደ ተሻለ ሕይወትም እንገሠግሣለን። ሆኖም የድል ግስጋሴ ላይ መሆናችንን እናረጋግጥ። መምጠቅ ባለብን ነገር ሁሉ መጥቀን እንሂድ፤ ሁሉም ባለበት አይሆንምና።

ይህ የሚያሯሩጠን፣ የሚያራውጠንና የምንወጣው ተራራ ሁሉ አንድ ቀን ያልፋል። ከጊዜ በኋላ የድካሜን ጣፋጭ ፍሬ አገኛለሁ ብለን በተስፋ እየለፋንባቸው ያሉ ቁም ነገሮች አሉ። የልጆቻችን የተሳካ ሕይወት ከእነዚህ ውድ ቁም ነገሮች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው። በሌሎች ኀላፊና አናሳ ነገሮች ላይ ስኬትን አግኝተን በዚህ ዋነኛ ነገር ላይ ከተሰናከልን የሚያስቆጭ ይሆናል።ቆም ብለን አድራጎታችንን እንፈትሽ። ትልቅ ፍቅር አለን





ማለት፣ ለልጆቻችን የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ እየሰጠናቸው ነው ማለት አይደለም። እየሮጥንና እየለፋን ነው ማለት የሚረዳቸውንነገር እየሰጠናቸው ነው ማለት አይደለም።

ከፍቅርና ጥረታችን ጋር አብሮ ጎን ለጎን መሄድ ያለበት አንድ ዋና ነገር አለ። ይኸውም ትክክለኛ ግንዛቤ ነው። ልጆቻችንን በሚጠቅማቸው ነገሮች ላይ ትክክለኛው ግንዛቤ እንዲኖራቸው አድርገናል ወይ? በዚህ አገር ባህል ውስጥ ሲኖሩ በሕይወታቸው ደስተኛ እንዲሆኑ፣ ውስጣቸው እንዲጠነክርና እንዲለመልም ምን ይረዳቸዋል በሚለው ነገር አኳያ ትክክለኛ መረዳት ይዘናል ወይ? ይህ ዋነኛው ጥያቄ ነው፤በዚህ ጉዳይ ላይ የተሳሳተ ግንዛቤ ካለን ፍቅራችንና ትጋታችን ሁሉ ከንቱ ይቀራል።

በባዕድ አገር ሆነን ቀን ከሌሊት ከለፋን አይቀር፣ መሥዋዕትነት ከከፈልን አይቀር፣ የላቀ ዋጋ ላለው ነገር እንድከም። ልጆቻችን ፍሬ አፍርተውና ለምልመውልን አይተን ደስ ይበለን። ልክ ያልሆነ አስተሳሰብ አሸንፎን፣ ባልጠበቅነው ሁኔታ፣ ትክክል ከሆነው ግባችን እንዳያሰናክለን፣ ፍቅራችንና ልፋታችን ተጣምረው ልንጨብጠው ከሚገባን ፍሬ እንዳንተጓጎል በዕውቀት እንፋለም፤ አካሄዳችንንም እንመርምር።

የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን በተመለከተ ከዚህ በታች ያሉትን አስተሳሰቦች ልብ እንበል። በሁሉም ነጥቦች ላይ የተሳሳተ ነገር ላይኖረን ይችላል፤ በአንዳንድ ነገሮች ጠንካሮች ስንሆን በሌሎች ነገሮች ደግሞ ደካሞች ልንሆን እንችላለን። ደካማ ጐናችንን ፈልገን ማግኘት የጥንካሬያችን መገለጫ ነው፤ የስኬት አሃዱ ነውና። ራሳችንን እንገምግም ተዘወትረው የሚደመጡ የተሳሳቱ ግንዛቤዎቻችን ከሞላ ጐደል ለመቃኘት እንሞክር፤

**_ስለ ልጆች የሚንጸባረቅ የተሳሳተ የወላጅ አመለካከት_**

- "በምእራብያውያን አገሮች መኖራቸው በራሱ ጥሩ ሕይወትን ይሰጣቸዋል"::
- "የሚበሉት የሚጠጡት ይኑር፣ የሚለብሱት የሚተኙበት ይኑራቸው እንጂ ምንም አይሆኑም!"::
- "የምገዛላቸው ዘመናዊ ልብስና መጫወቻ የሚያስፈልጋቸውን ርካታና ሰላም ይሰጣቸዋል"::
- "የሌሎች ሰዎች ልጆች ያገኙትን ነገር ሁሉ የእኔም ልጆች ማግኘት አለባቸው"::

**_ወላጅ ከልጁ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ አዘውትሮ የሚያንጸባርቃቸው የተሳሳቱ ግንዛቤዎች_**

- "ልጆቼ ናቸው፤ የእኔ ናቸው፤ እንደምወዳቸው ያውቃሉ፤ ሁሉን የማደርገው ለእነሱ እንደሆነ ይረዳሉ፤ ስለዚህም ልነግራቸውም ሆነ ላሳያቸው አያስፈልግም"::
- "ከልጆቼ ጋር አብሬ መዋሌ በራሱ ትስስሬን ያጠነክረዋል"::
- "ልጆች ቅሬታና ሐዘን አይሰማቸውም"::
- "ፍቅሬን መግለጼና ከልጄ ጋር መጫወቴ ልጄን ያሞላቅቃል:: ልጆቼ ያከብሩኝ ዘንድ ቆጠብ ኮስተር ብዬ መታየት አለብኝ"::
- "ወላጁ እስከሆንኩ ድረስ ሁሉመናው ሆኜ፣ ላሳድገው ይገባል"::

**_ልጆችን ትልቅ ቦታ ማድረስን በተመለከተ በወላጆች ዘንድ የሚንጸባርቁ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች_**

- "ጎበዝ ልጅ ማለት በዚህ የትምህርት ሞያ፣ የሚያተኩር፣ ወደዚህኛው የሥራ መስክ ለመንዝ የመረጠ፣ ልጅ ብቻ ነው"::
- "እንደ ወላጅነቴ፣ ለልጄ የሚጠቅመውንና ሊወስደው የሚገባውን አቅጣጫ ሁሉ ጠንቅቄ ዐውቃለሁ::ሥራዬ ሊሆን የሚገባው፣ ያየሁሉትን የእኔን ህልም እርሱ እንዲፈጽም ነው"::
- "ልጅን ከወንድም እህቱ ወይም ከሌላ ጋር እያስተያየሁ፣ 'እንደ እገሌ፣ እገሊት ጎበዝ አይደለህም'፤ 'ከእነርሱ ጋር ስትነጻጸር ይህ ይቀርሀል ብዬ ሳመላክተው በበጎ ቅናት ይነሣሣል"::





**_ልጅን ሥነ ሥርዐት ማስያዝን በተመለከተ፣ የምንመራባቸው የተሳሳቱ ግንዛቤዎች_**

- "ቁጣና አካላዊ ቅጣት ልጅን በማጎበዙ ሂደት ላይ ዋነኛ ድርሻ አለው"::
- "ልጅን ካልጮኹበት አይሰማም"::
- "ወላጅ እንደ መሆኔ መጠን ልጄ ላይ ተጽእኖ የማምጣት ዕድሉ ዘወትር አለኝ"::
- "አትኩሮት መስጠት ያለብኝ እየተበላሸ ላለው ልጄ ብቻ ነው"::
- "ልጅ የጠባይ ለውጥ የሚያመጣው መስመር ሲለቅ ብቻ ነው"::
- "ወላጅ ሲናገረው የራሱን ሀሳብ የሚገልጽ ልጅ ተዳፍሯል።
- "ወላጅ ፊት ዝም የሚል ክፉ የማይናገር ልጅ ሁሉ ጨዋ ነው"::
- "ባጠፋ እንኳ፣ ለልጄም ሆነ በልጄ ፊት አጥፍቻለሁ ማለትና ይቅርታ መጠየቅ፣ ልጆቼ እንዲንቁኝ በር መክፈት ነው"::

_በአጠቃላይ ኑሮዋችንን በተመለከተ፣ በዚህ በምእራብያውያን ባህል ውስጥ የምንኖር ሰዎች ያለን ዋነኛ የተሳሳተ ግንዛቤ_

- _"አንድ ቀን ይህ የሚያሯሩጠኝ ነገር ይሳካና፣ እርፍ ብዬ ከቤተሰቤ ጋር እኖራለሁ" የሚል ነው።_ ይህ መጽሐፍ ለእነዚህና ከእነዚህ ጋር ተዛማጅ ለሆኑ የተሣሣቱ ግንዛቤዎች መልስ ለመስጠት ሙከራ ያደርጋል::

## የውጭ አገሩ ሕይወታችን

ሕይወት ጥድፊያና ፍጥነት በሆነባቸው አካባቢዎች ልጆቻችንን የምናሳድግ ከሆነ፣ "በጉደለውና በሚሞላው መካከል እንዴት ከቤተሰቤ ጋር የሰላም፣ የደስታና የፍቅር ጊዜ ላሳልፍ እችላለሁ" የሚለው ጥያቄ ዘወትር የምናስበው ነገር ሊሆን ግድ ነው:: "ይህንና ያንን አሟልቼ ስጨርስ እፎይ ብዬ ሕይወቴን እመራለሁ" የሚለው ሐሳብ መቼም የማይሞላ ምኞት መሆኑን ዐውቀን አውጥተን እንጣለው:: "ነገር ሲሰምርልኝ ፣ዳገት ቁልቁለቱን ወጥቼ ስጨርስ ያኔ ዕርፍ እላለሁ" በማለት ያቺን ቀን የምንጠባበቅ ከሆነ ሰላምን፣ ደስታንና ዕረፍትን ሳናጣጥም ጊዜው ይነጉዳል:: "ሁሉን አሳክቼ ስጨርስ ያኔ ከቤተሰቤ ጋር የደስታና የፍሥሐ ጊዜን አሳልፋለሁኝ" ብለን በቀጠሮ የምንጠብቅ ከሆነ፣ ከልጆቻችን ጋር አብሮ ለማሳለፍ ያለን ዐላማ ከዳር ሳይደርስ፣ ጊዜ ጊዜን እየወለደ ዐድገው ከቤት ሲወጡ እናያቸዋለን:: እንዲሁ እንደ ከነፍን፣ አሟላዋለሁ የምንለው ቋት ሳይሞላ፣ በመዋከብ ጊዜው ያልፋል :: ይህ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ለማወቅ የምንሻ ካለን ሕያዋን ምስክር ሆነው በውጭ አገር ለብዙ ዓመታት የቆዩትን ሰዎች ጠይቀን መረዳት እንችላለን::

እንደአሜሪካ አገር ባሉ፣ ፍጥነት በበዛባቸው ቦታዎች፣ ሁሌ የሚጨረስ አይጠፋም፤ ሁሌ የሚከፈል ነገር ይኖራል:: እንዲያው ልንደርስበት ወደምንከጅለው ነገር ለመድረስ፣ ትንፋሻችን ቁርጥ ቁርጥ እስኪል ድረስ የሚያሯሩጠን ነገር መቼም አይጠፋም:: ቴሌቭዥኑን ገዝተን ገና ደስታው ሳይወጣልን፣ ግዛኝ ግዛኝ የሚል መኪና ፊታችን ይጋረጣል:: መኪና በገዛን ሰሞን ገና ዕፎይ ሳንል የወር ክፍያው ከተፍ ይላል:: እንዲያው ባጠቃላይ እንዲህና እንዲያ ስንል ዕድሜ እንደዘበት ይፈተለካል::





እንግዲያውስ ታዲያ፣ የሕይወት ትርጉም ምንድነው? ከልጆቻችን ጋር አይን ለአይን እየተያየን ከልብ የመነጋገር ዕድል ሳናገኝ ሕይወት የምትከንፍ ከሆነ ምን ጣዕም አላት? ታዲያ ሰላም ማለት ምንድነው? በአመት አንዴ የምንወስደው የዕረፍት ጊዜ ይሆን? አዲስ ልብስ ለብሰን ወደ ኢትዮጵያ የምንልከው ፎቶ ይሆን? ሕይወት እንዲህ ከሆነ፣ በቤቱ ከልቡ ሥቆ፣ ከቤተሰቡና ከልጆቹ ጋር የሆዱን አውርቶ፣ ተመስገን ብሎ በሳር ጎጆ ውስጥ የሚኖረው ያገሬ ገበሬ ሕይወት በእጥፍ አይሻልምን?

ቆም ብለን እናስብ! የሕይወታችን ትርጉም፣ እንዲሁ መሮጥ ብቻ እንዳይሆንብን እናስተውል:: በውጭ አገር መኖራችን ለምን እንደሆነ ልብ ብለን ማጤን ይኖርብናል:: የዚህ አገር ኑሮ ለማበባችን እንጂ ለመጠውለጋችን፣ ለማፍራት እንጂ ለመጨንገፍ እንዳይሆንብን እንጠንቀቅ::

የልጆቻችን የልጅነት ጊዜ ተመልሶ ላይመጣ እየነጎደ ነው:: ከአይናችን የተሰወረ ትልቅ ዋጋ ልንሰጠው የሚገባ ነገር አለ ወይ? አዲስና ምቾት ያለው ሶፋ ቢኖረን ክፉ አይደለም:: ነገር ግን የቤተሰብ ፍቅር ጠፍቶ እንዲያው ለትንግርት የተቀመጠ ሶፋ፤ ጥሩ አይደለም፤ ጊዜ አልፎ ይጣላልና፤ ያውም ከነአዲስነቱ:: አዲስ ቤት መልካም ነው፤ ነገር ግን ቤቱን ለመግዛት ሲባል የቤተሰብ ሕይወት የሚሠዋበት ከሆነ፣ ለቤተሰብ አብሮነት ጊዜ የሌለን ከሆነ ያ ትርጉም አይኖረውም፤ ነገ ደግሞ ለሌላው፣ ሽያጭ ላይ ይውላልና። ጠንክሮ መስራት ተገቢ ነው። እንሩጥ፤ እንሥራ፤ነገር ግን ሩጫችን ግዙዝ ለሆነው ስናፈጥበት መልሶ ለሚያፈጥብን የቤታችን ዕቃ ብቻ አይሁን::

ብዙዎቻችን፣ ቤተሰባችንን ከልብ እንወዳለን፤ግን ሳናስተውል ቤታችንን እያፈረስን እንዳይሆን ቆም ብለን ብናስብ ይበጀናል። በትናንሹ ነገር ተጠላልፈን ዐውራ ነገሮችን

እየጣልን ዕድሜና ጊዜያችን እንዳያልፍ:: "እረ ለመሆኑ ቅድሚያ ልሰጠው የሚገባኝ ነገር ምንድነው?"፤ "እንዲሁ ስባዝን ቸል ያልኩት ነገር ምንድነው?" ብለን ራሳችንን እንመርምር:: ከለፋን አይቀር፣ ላባችን ከፈሰሰ አይቀር ፍሬው ጣፋጭ ለሆነ ነገር እንልፋ:: ደስተኛ ሆኜ ዐደግሁ የሚሉ ልጆች፣ በፍቅር የተሞሉ ልጆች፣ ቤተሰቦቻቸውን ዘመዶቻቸውን የሚያከብሩ፣ ሩቅ የሚያዩ፣ ትልቅ ቦታ የሚያነጣጥሩ ሁነኛ ልጆች ይኖሩን ዘንድ ራእይ ይኑረን::

ወላጆች ለልጆቻቸው አስፈላጊ የሆኑ ዋነኛ ነገሮችን እንዳይሰጡ ለማገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው፣ በውጥ የተተከለ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው። ብዙ ወላጆች፣ አገራቸውን ጥለው በመምጣት በባዕድ ምድር ዋጋ የሚከፍሉት "ልጆቻችን ወደፊት ብሩህ ሕይወት ያጋጥማቸዋል በሚል የተሰፋ ስንቅ ነው:: ማንም ወላጅ፣ በማይረባ ነገር የራስን ሆነ የልጆቹን ጊዜ ለማጥፋት አይፈልግም:: ሆኖም፣ የተሳሳተ አመለካከት፣ ልጆች በሕይወታቸው ደስታ፣ ሰላም እና ፍቅር ሊሰጧቸው የሚችሉትን ነገሮች ሳያገኙ እንዲያድጉ ሊያደርግ የሚችል ዋነኛ አጋጅ ጠላት ነው::

ለቤተሰባችን እና ለኛ ጎጂ በሆነ አቅጣጫ እንድንራመድ የሚያደርጉን የተለያዩ አይነት የስህተት ምርጫዎች አሉ:: አንዳንዴ ሳናስበው፣ ኀይላችንና አትኩሮታችን በውድድር ሕይወት ውስጥ ይዋጣል። በእኔና በቤተሰቤ ሕይወት ውስጥ ቋሚና ዘላቂ የሆነ የሕይወት ጉዳይ ምን ማድረግ ይገባኛል ከማለት ይልቅ እከሌና እከሌ የገዙትን ጠፊና አላፊ ምድራዊ ቁሳቁስን ለመግዛት እንጨነቃለን:: ቤታችንና ቤተሰቦቻችንን በሚታየውና ብልጭልጭ በሆነው ነገር አሳምረን፣ ሰው እንዲያይልን ስንል ሀይላችንንና ጉልበታችንን እንጨርሳለን:: ውጨን በማሳመሩ ላይ ተጠምደን የውስጡን እንዘነጋለን። ከልጆቻችን ጋር ሊኖረን የሚገባን ግንኙነት የሠመረ ያበበ እንዲሆን፣ ፍሬ የምናፈራባቸው ጊዜያት በከንቱ ያልፋሉ:: ልብ እንበል! የዛሬ 30 ዓመት መለስ ብለን ያለፍንበትን ሁሉ ስናየው





ዋና ነገር ሆኖ የሚታየን፣ "እገሌ እንደገዛው መኪና ገዛሁ ወይ እገሌት ያላት ቤት ዐይነት ባለቤት ሆንሁ ወይ" የሚለው አይደለም፤ በምን ዐይነት ሰላም ውስጥ እኔና ቤተሰቤ ኖርን የሚለው ፤ ያ ነው ዋነኛ ጥያቄ የሚሆንብን:: ልጆቼ ከልብ ስቀው ዐደጉ ወይ? በቤቴ ውስጥ ጥሩ ትዝታ ነበር ወይ? ከዓመታት በኋላ መለስ ብለን ብናይ፣ በውስጣችን የሚመላለሰው ያ መሰረታዊ ጥያቄ ነው:: ጊዜው አይሩጥብን፣ የውድድር መንፈስ ውጭን የመቀባባት መንፈስ ከትልቁ ሥዕላችን የሚያርቀን መጥፎ አጥማጅ መንፈስ መሆኑን እንወቅበት:: መውጣት የሚገባንን መሰላል ሁሉ እንውጣ፤ ግን ለውድድር ጨዋታ ብለን አናድርገው:: እነዚ ኩኩሉ ጨዋታዎች ለጊዜው ትልቅ ነገር መስለው የሕይወት ዋና ዋና ነገሮች ከዐይናችን ይሰልቡብናልና::

ሌላው የእኛና የልጆቻችን ሕይወት ውስጥ ሰላምን፣ አብሮ ማሳለፍን፣ ትስስርን ወዘተ እንድንረሳ የሚያደርገን፣ የሩጫ መንፈስ ነው:: አንዳንዶቻችን ሳናስበው፣ መጨረስ ያለበት ጉዳይና የበለጠ ማግኘቱ፣ ዋነኛ የሕይወት መሪያችን ሆኗል:: የቤቱ ዕዳ ተከፍሎ መጨረሱ አእምሮዋችንን የያዘው ዋነኛ ነገር ሆኗል:: የመኪና ግባችን ማታ የሚያስተኛን ጧት የሚያነቃን ሥዕል ሆኗል፤ እና ለዋናዎቹ ነገሮች፣ አእምሮዋችን ሳናስበው ይከለላል:: ልጆቻችንን የምናያቸው፣ "ተነሥ ትምህርት ቤት ሂድ" ለማለት እና ኋላ ደግሞ "የቤት ሥራህን ሥራ" ለማለት ብቻ ይሆናል፤ ጊዜውም ይሄዳል:: የውክቢያ ሕይወት ጠባይን በደንብ እንረዳ:: አንዱ ስለተጨረሰና ስለተሳካ ያ ስሜቱ አይጠፋም:: ሁሌ አንዱ ሲሳካ ደግሞ ሌላው በአእምሮዋችን ይጋረዳል፤ ያ ዋናውና መቼም የማይጠፋው የጥድፍያ ሕይወት ጠባይ ነው::

በቤተሰብ መካከል ፍቅር ግንኙነት ትስስር ያላቸው ጊዜዎች ሁሌም የነበሩ መቼም የማይለወጡ የሕይወት የልብ ትርታዎች ናቸው:: በሁሉ መካከል ትልቁ ሥዕላችን ከጠፋን "ከትላልቆቹ ግቦቻችን" ጋር ተቆላልፈን እንቀራለን::

ላመንበት አላማና ህልም ጠንክረን እንስራ፤ በሁሉ መሀል ግን አካሄዳችንን እየገመገምን ይሁን "የቤተሰቤን ጉዳይ ከአይምሮዬ ከልቤ፣ ዐይኔ ጉጉቴ የሆነ የሚደረስ ቦታ ላይ ብቻ ሆኗል ወይ? እነጭንቀት፣ እነውጥረት፣ እነ "የበለጠ ፍለጋ" ጧት የሚያስነሡኝ እና ማታ የሚያስተኙኝ ጓደኞቼ ሆነዋል ወይ? ከቤተሰቤ ልጆቼ ጋር ትስስርን አብሮ መሣቅን ከልብ ማውራትን ከልለውብኛል ወይ" ብለን ሁኔታውን እናጢን:: እነዚህ የጥድፊያ ስሜት፣ ቁሳቁስን የመጠማት ስሜት፣ በቅጽበት መፍትሄ የሚያገኙ ፍላጎቶች ይምሰሉ እንጂ፣ መቼም የማይጠፉ ከዓይናችን ስር 20 አመት የሚሰልቡብን አደገኛ ነገሮች መሆናቸውን ተረድተን ባለን ኀይል ሁሉ እንፋለማቸው::

አንዳንዶቻችን ደግሞ "ለልጆቼ የሚያስፈልጋቸውን ላቅርብላቸው የሚል ዐላማ ኖሮን፣ ነገር ግን የትኛው ቀዳሚና አንገብጋቢ ነው በሚለው ነጥብ ላይ የተሳሳተ መንገድ ይዘናል:: ለእነሱ ይህን ያንን ማድረጉ፣ ያንን መግዛቱ አብረናቸው ከምናሳልፈው ጊዜ የበለጠ የሚጠቅማቸው ይመስለናል:: ልጆቻችንን፣ በሳምንት አምስት አይነት እንቅስቃሴ (activity) ውስጥ ማሳተፉ፣ ከእነሱ ጋር ከሚኖረን አንድ ለአንድ ትስስር የበለጠ የሚጠቅማቸው ይመስለናል:: በመልካም ምኞት ሆነን፣ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ቀን ሌሊት እናበረታታቸዋለን ግን ለነገ ሕይወታቸው ስንዘጋጅላቸው፣ የዛሬው ሕይወታቸውን ፍላጎታቸውን እንረሳለን፤ አብረናቸው አንሥቅም፤ እንደ ብርሀን ፍንትው ባለ ፊት አናወራቸውም፣ ዕቅፍ አድርገን "እንዴት እንደምወዳችሁ ታውቃላችሁ ወይ" ለማለት ወይም ከልባችን ከልጆቻችን ጋር ለማውራት ጊዜ አንወስድም:: የሚጠቅማቸው የሚመስለንን ውጫዊ ነገር ሁሉ እናደርጋለን፤ ግን በተሳሳተ ግንዛቤ ሥር ሆነን፣ ከሁሉ የሚያስፈልጋቸው ነገር ላይ እጃችንን እንሰበስብባቸዋለን::

ልጆቻችን በችሎታ ትልቅ ቦታ እንዲደርሱ ጠንክሮ መሥራቱ ጥሩ ብቻ ሳይሆን፣ አስፈላጊም ነው፤ ግን በጭንቀት ውጥረት የሚሞላን





ከሆነ፣ ልጆቻችንን ከልብ ሳናያቸው ሳናወራቸው ሳንተቃቀፍ የልባችንን ሳንነግራቸው ከቤት እንዲወጡ የሚያደርግ ከሆነ፣ ያ ተገቢ አይደለም፤ ለልጆቻችን ጠቃሚ በመሆን ፋንታ እርግማን ይሆንባቸዋልና:: ከምንም በላይ ስለ መሰረታዊ እውቀቶች ስለፍቅር ሊያስተምሯቸው ከሚችሉት ከቤተሰቦቻቸው ለያይቶና፣ አራርቆ ያሳድጋቸዋልና::

ብዙ የሚደረግ ነገር እያሰብን፣ ይህን ሳላደርግላቸው፣ ያንን ሳላደርግላቸው የሚለው ጸጸት ውጥር አድርጎ ሊይዘን ይችላል:: ልጆቻችንን የሚያስፈልጋቸውን ለመስጠት ብዙ የተወሳሰበ ነገር ውስጥ መግባት የለብንም:: ዋናው መርሆ ከተረዳን ለልጆቻችን የሚረዳ ትልቅ ነገር ልናበረክት እንችላለን::

ለሁሉ ቁስ አካል የሚሠራ፣ አንድ ወጥ የሆነ የአስተዳደግ ዘዴ አለ ለማለት አይደለም፤ የልጆቻችን ጸባይና ሁናቴ የተለያየ ነው፤ ሁሉም ወላጅ፣ እንደየባህሉና አመለካከቱና እምነቱ፣ ልጆቹን የሚያሳድግበት፣ የተለያዩ ዘዴዎች ይኖራሉ:: እንደዛም ሆኖ ግን፣ ለሁሉም ቤተሰብና ልጆች የሚሰሩ የጋራ መሰረታዊ ነጥቦች አሉ:: እነዚህን ነጥቦች ወደ መቃኘቱ እንዝለቅ::

# ምዕራፍ አንድ

## መልካም የልጅነት ሕይወት

"የልጅ አስተዳደግ ላይ የተደረጉ የተለያዩ ጥናቶች፣ ውጤታቸው በአስገራሚ ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። ስለ ሌሎች የጥናት ክፍሎች እንዲህ ነው ብሎ ለመናገር በጣም ያስቸግራል። ሌሎች የጥናት ክፍሎች፣ ውጤታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ይቀያየራል፤ ነገር ግን "ጥሩ የልጅ አስተዳደግ ምንድነው" በሚለው ላይ የተደረጉ ሳይንሳዊ መርሆዎች ለአለፉት 40 አመት መደምደሚያቸው አልተቀየረም"[1]

### መልካም የልጅነት ጊዜ እንዴት ይገኛል?

**ቤተሰብ ከልጅ ጋር የሚኖረው ፍቅራዊ ትስስር የልጅ ህይወት ማበብ ላይ ዋነኛ አስተዋጽኦ አለው:: ልጆች መልካም የልጅነት ጊዜ እንዲኖራቸው ዋነኛ አስተዋጽኦ ያለውም ይህ ከቤተሰብ ጋር የሚኖራቸው በፍቅር የተሞላ ትስስር ነው::**

> "ወላጅ ለልጁ ያለው ፍቅር፣ መውደድና እንክብካቤ ለልጆች ጤናማ አስተዳደግ ዋነኛ አስተዋጽዖ እንዳለው መተንበይ ይቻላል። ባጠቃላይ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፣ በፍቅር በእንክብካቤ ያደጉ ልጆች፣ ችሎታ ያላቸው፣ ሀላፊነት የሚሰማቸው፣ ራሳቸውን የቻሉና በራስ መተማመን ያላቸው፣ ውጤታማ የሆኑ እንዲሁም ብስጩነትን የሚቆጣጠሩ ይሆናሉ።"[2]

[1] Steinberg Laurence (2011) you and your adolescent, Simon and Schuster

[2] Maccoby, E. E., & Martin, J. A. (1983). Socialization in the context of the family: Parent-child interaction. In P. H. Mussen & E. M. Hetherington, Handbook of child psychology:Vol4. Socialization, personality, and social development (4th ed.). New York: Wiley





ልጆቻችን ያበበ የልጅነት ጊዜ እንዲኖራቸው የምናደርግበት ዋናው መንገድ ከእነርሱ ጋር በምናሳልፈው የአንድ ለአንድ የትስስር ጊዜ ነው:: የአንድ ለአንድ የትስስር ጊዜ ማለት ምን ማለት ነው? ከልጆቻችን ጋር በየቀኑ ከሚኖረን አጥና፤ አምጪ፤ አታድርግ፤ ነይ፤ ተው ወዘተ-- ከሚለው ንግግር ያለፈ፣ ከእነሱ ጋር አንድ ለአንድ የምናሳልፈው ልዩ ጊዜ ማለት ነው:: "ይህ አብሮ የማሳለፍ ጊዜ ምን ጥቅም አለው? ዞሮ ዞሮ ልጆቼ አይደሉ? አብረን እንኖር የለ እንዴ?" እንል ይሆናል:: ነገሩን በራሳችን እንኳ እንየው:: ሁሉ ያለበት፣ የሞላበት አገር ውስጥ እንኖራለን፤ ነገር ግን የበዛውና ያማረው ውጫዊ ነገር ምንስ ቢያምር፣ብቻውን የምንፈልገውን ደስታና ፍቅር እንዳልሰጠን አይተናል፤ ከውጫዊው ነገር ጋር ሲመዛዘን፣ ከምንወደው ሰው የምናገኘው ፍቅር በሕይወታችን ላይ ትልቅ ዋጋ አለው፤ አይደለምን? እንግዲህ እናስበው፣ ለእኛ ለትላልቆቹ እውነቱ እንደዚህ ከሆነ፣ ፍቅር እንደ ውሀ ለሚጠማቸው ልጆቻችን ከእኛ ከቤተሰባቸው ጋር ያላቸው የአንድ ለአንድ ጊዜ በደስታ ለማበባቸው በጣም ወሳኝ ነው::

ሥራዬ ብለን ከልጆቻችን ጋር የአንድ ለአንድ ጊዜ ስናሳልፍ፣ ከምንም ነገር በላይ በጣም እንቀራረባለን:: ልጅና ወላጅ በሚለው ብቻ አንወሰንም፤ በፋንታው፣ በኋላ ሲያድጉ እንኳ ከልብ እንድንተሳሰር የሚያደርገን፣ እንዲሁም በችግር ውስጥ አብረን እጅ ለእጅ ተያይዘን የችግር መላ እንድንፈልግ የሚረዳን ዐይነት ጠንካራ ገመድ ይፈጠራል::

ከልጆቻችን ጋር አንድ ለአንድ ጊዜ ማሳለፋችን፣ልጅ ከልጅነቱ ጀምሮ ለእኛ እውነቱን መናገር፣ ግልጽ ሆኖ ስለሚያጋጥመው፣ ስለሚያልፍበት በግልጽ ማውራት እንዲጀምር ይረዳዋል:: ለልጆቻችን ጊዜያችንን ስንሰጣቸው፣ በሕይወታቸው በጣም ደስ ያሰኛሉ:: ለእነርሱ ያለንን ፍቅር ከመረዳታቸው በላይ አብረን የምናሳልፈው ሰአት እኛንም እንደሚያስደስተን በማወቃቸው ትልቅ ትምህርት እንዲኖራቸው ይረዳቸዋል:: በኋላ አድገው ስለ ልጅነታቸው ጊዜ መለስ ብለው ሲያስቡ፣ ያላቸው ትዝታ በደስታ

እና በፍቅር የተሞላ ይሆናል። ባጠቃላይ ልጆቻችንን ደስተኛ፣ በፍቅር የተሞሉ፣ ስለ ራሳቸው ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው እንዲሆኑ እንዲሁም ከእኛ ከወላጆቻቸው ጋር ያላቸው ቅርርብ ከፍተኛ የሆነ እንዲሆን ይረዳል።

ጊዜ ማሳለፍ የምትለዋ ነገር ስናስባት ከበድ የምትለን ነገር ነች። ሩጫ በበዛበት አገር ውስጥ ነን ያለነው፤ አንዳንዴ 24ቱንም ሰዓት የምንሮጥ ይመስላል። እውነትም የሚሰራውም ሆነ የሚጨረሰው ነገር ብዙ ነው። "እንዴት ብዬ ነው ከዚህች ካለችኝ የተጣበበች ሰዓት ወስጄ ከእነርሱ ጋር የማሳልፈው" ብለን እናስብ ይሆናል። ቁም ነገሩ የሠዓቱ እርዝመት አይደለም። ቅንጣት ጊዜ እንኳ እየወሳሰድን፣ ምን ያህል እንደምናስባቸው እንደምንወዳቸው፣ ለልጆቻችን በተግባር ማሳየታችን፣ ነው ዋናው ነገር። ከእነርሱ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ እንደምንፈልግና ምን ያህል እንደሚያስደስተን ልጆቻችን ማወቃቸው፤ ያ ነው ትልቁ ነገር።

ጥቂት ደቂቃዎች እየወሳሰድን ከእነርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፍ እንዴት እንደሚያስደስተን፣በተግባር እናሳያቸው።ጧት ሲነሡ እንቀፋቸው፤ እንሳማቸው። "እንዴት ዐደራችሁ" እንበላቸው። ትምህርት ቤት ስንወስዳቸው እናውራቸው። አብረናቸው እንወያይ፤ ስለተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ያላቸውን አስተያየት እንጠይቅ። ከትምህርት ቤት ስናመጣቸው "የዛሬ ውሎዋችሁ እንዴት ነበር" እንበላቸው፤ ሲመልሱልንም ከልብ እናዳምጥ። ይህ ከኛ ጋር የሚፈጥሩት ልምምድ የእነርሱን ሕይወት ብሩህ ከማድረጉም በላይ፣ እኛ እነርሱ ስለሚያልፉበት ነገር ግድ ያለን እንደሆንን እንዲረዱ ያደርጋል። ከሥራ ደውለን "እንዴት ዋላችሁ" እንበላቸው። "አንድ የምነግርህ ወይም የምነግርሽ ነገር አለ" ብለው ጉጉት ብለው ሲነግሩን፣ ሁልጊዜ " አይ አሁን ማድመጥ አልችልም፤ ብዙ ሥራ አለብኝ" በማለት ፈንታ ትንሽ ጊዜ ሰጥተን እንስማቸው

በትናንሽ ጊዜዎች ውስጥ ከልጆቻችን ጋር የምንተሳሰርባቸው መንገዶች ብዙ ናቸው። የተለያየ ጨዋታ እንጫወት፤ እንቀፋቸው፤ እንኮርኩራቸው። ከልጆቻችን ጋር አብረን እግዚያብሄርን እናምልክ





ማታ ከሥራ ስንመጣ አንዳንዴ ቀስቅሰንም ቢሆን እንሳማቸው። ደኅና ዕደሩ እንበላቸው። በቀኑ ውሏችን ስላጋጠሙን ነገሮች እንንገራቸው፣ እናስቃቸው። ቤት ውስጥ የምንሠራው ብዙ ነገር ካለን በምንሠራው ነገር ውስጥ እነርሱንም እናስገባቸው ። ዐውቀን በእነርሱ ችሎታ ያለ የሚሠራ ሥራ ፈጥረን (የእውነት ሥራም ባይሆን ማለት ነው) "እሺ አሁን የእኛ ቤተሰብ ተባብረን ሥራ እንሰራለን፤ በዚህ ጉዳይ እንድታግዘኝ/እንድታግዢኝ እፈልጋለሁ" እንበላቸው። ከእኛ ጋር ሆነው በኅብረት ከሰሩ በኋላ እርዳታቸው እጅግ ትልቅ እንደሆነ እንንገራቸው። ይህ ቤተሰብ አብሮ ተባብሮ ለአንድ ግብ መሥራት እንዳለበት ከማስተማሩም በላይ ከእኛ ጋር ያላቸውን ትስስር ይጨምረዋል። አብረን ተባብረን በጋራ አላማ በመስራት፣ ከእነርሱ ጊዜያችንን እንዳሳለፍን ስለሚያዩም በጣም ደስ ይሰኛሉ።

30 ደቂቃ ወይም አንድ ሠዓት ያህል ጊዜ ሲኖረን ደግሞ፣ አብረን ልናደርጋቸው የምንችላቸው ብዙ ነገሮች አሉ፤ ስለ ልጅነታችን ጊዜ የሚያወሳ ታሪክ እንንገራቸው። ሥዕል አብረን እንሳል፤ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የጥያቄና የመልስ ጊዜ ይኑረን። ስለ እርስ በእርሳችን፣ የቤተሰብ ቀልድ እናውራ፤ እንሳቅ። ማን፣ ምን ያቃል ጥያቄ እንጠያየቅ። ፍቅር ያለበትና ለልጅ ተገቢ የሆነ ይሁን እንጂ ለምናደርገው ነገር አንድ ዐይነት ቀመር መኖር የለበትም።

ከላይ እንዳልነው ይህ ለልጆቻችን ሕይወት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ልጅነታቸውን ደስተኛ ያደርገዋል። ላሁኑ ብቻ ሳይሆን ለወደፊት ሕይወታቸው ሁሉ የሚጠቅማቸው ውስጣዊ መደላደል ይፈጠራል። በሌላ መልኩ፣ "ልጆቼ ናቸው፤ እንደምወዳቸው ያውቃሉ" ብለን ችላ ካልናቸው፣ በቁሳቁስ ነገር ተከበው ግን በብቸኝነት ተውጠው እኛ ወላጆቻቸው እንኳ እንደማናያቸው እየተሰማቸው ይኖራሉ። አንድ ቀን አብሬያቸው አሳልፋለሁ ብለን ከጠበቅን ዛሬ ዛሬን እየወለደ ጊዜው ይፈተለካል፤ ልጆቻችንም ከእኛ

ጋር ሊኖራቸው የሚገባው ትውውቅ እና ትስስር ይጠፋል:: ካደጉ በኋላ ልብ ለልብ እናውራ ብንል የከበደ ይሆንብናል::

## ፍቅራችንን ማሳየት

ሌላው የልጆቻችንን ደስታ፣ ከእኛ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና እና ውስጣዊ ጥንካሬያቸውን በትልቁ የሚወስነው፣ እኛ ፍቅራችንን ለእነርሱ የምንገልጽበት መንገድ ነው:: በውስጣችን ያለው ፍቅር፣ ወጥቶ በግልጽ መታየት አለበት:: አንዳንዴ፣ "እኔ ልጆቼን በውስጤ መውደዴ በቂ ነው" ብለን እናስባለን:: ነገር ግን፣ በውስጥ ያስቀመጡት ፍቅር ከሚያሳዩት ፍቅር በጣም የተለየ ነው:: ልጅ እንደ እኛ አይደለም:: አዎ፤ ልጅ እንደ እንደ አዋቂ፣ አስቦ አመዛዝኖ፣ "በሚታይ መልኩ ባይቀርብልኝም እንኳ በውስጥ እንደሚወዱኝ ዐውቃለሁ" አይልም:: ልጅ እንደምንወደው የሚረዳው በውጭ የሚገለጸውን ገምግሞ ነው፤ የውስጥ የልባችንን ተገንዝቦ ሳይሆን፣ የምንገልጽለትንና የምናሳየውን ፍቅር አይቶ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በእነዚህ ምእራብ አገሮች የሚኖሩ ልጆች፣ ያለ ዘመድ ከበባ፣ ብቻቸውን የሚያድጉ በመሆናቸው፣ እንዲሁም ከቴሌቭዥን፣ ከትምህርት ቤትና ከጓደኞቻቸው፣ ልጆቻቸውን የማይወዱ፣ ብዙ ቤተሰቦች እንዳሉ፣ ደጋግመው ስለሚሰሙ ይህንኑ በውስጣቸው ቋጥረው ያድጋሉ:: የጠቆረ ፊት ሁሌ ባዩ ጊዜ፣ ወላጆቼ ይጠሉኛል ብለው ያስባሉ:: አዎ፤ ልጆቻችንን በውስጣችን ምንስ ያህል ብንወዳቸው፣ ግን ከውጭ የምናሳያቸው ተቃራኒውን ከሆነ፣ በውጭ ሁሌ የሚያዩት የእኛን ግሣጼ እና ጩኸት ብቻ ከሆነ፣ እንደገጽታችን ይመስላቸዋል:: "እንጃ፤ ወላጆቼ እኔን መውደዳቸውን እርግጠኛ አይደለሁም፤በእኔ መደሰታቸውን የማቅበት አንዳችም መንገድ የለም" በሚል መንፈስ ያድጋሉ::

በውስጣችን ፍቅር እያለ፣ በውጫዊው ሁኔታ ሁሌ ተቃራኒውን አናሳያቸው:: ለእንግዳ የማንከለክለውን ፈገግታ ለልጆቻችን





እንንሳቸው:: ለእንግዳ የማንከለክለውን ጥሩ ንግግር ለልጆቻችን እንንፈጋቸው:: ከእኛ ተገልጦ የሚያዩት ፍቅር የእውነት እንደሚያድሳቸውና እንደሚገነባቸው ተረድተን፣ የውጭ ፊታችን የውስጡን ፍቅራችንን ከማሳየት እንዳይከልልብን እንወስን:: ፍቅራችንን በግልጽ እና በማያሻማ መንገድ እናሳያቸው:: ከእንግዳ ጋር ጊዜ ወስደን እንደምንስቀው ሁሉ፣ ከልጆቻችንም ጋር አብረን እንሣቅ፤ እንጫወት፤ እንቀላለድ:: ከጓደኞቻችን ጋር ትዝታን እንደምናወራው፣ ከልጆቻችንም ጋር እንደዚያ እናድርግ:: ከሥራ ስንመጣ ፊታችንን አጥቁረን፣ የቤቱ ጌታ ወይም የቤቱ እመቤት ቤት መስለን ሳይሆን ቤተሰብ መስለን፣ "እሰይ አባቴ መጣ እሰይ እናቴ መጣች" በሚሉት ዐይነት መልኩ ሆነን እንግባ::

የልቤን ያውቃሉ በሚል ልጆቻችንን የሚጎዳና ዝቅ ሊያደርጋቸው የሚችል ንግግር አንናገራቸው:: በውስጣችን ያለው ፍቅር ምንስ የበዛ ቢሆን በተቃራኒ መልኩ የሚገለጽ ከሆነ ከንቱ እንደሆነ፣ ፍቅራችን ሕይወታቸውን የሚያድሰው ወጥቶ ሲገለጽላቸው መሆኑን ተረድተን፣ ፍቅራችንን የሚመጥንና የሚወክል ቃልን እንጠቀም::"እወድሀለሁ ልጄ፤ አንቺ ለእኔ ውዴ ነሽ" እንበላቸው:: ለእነሱ ብቻ ሳይሆን እነርሱ ፊት ለሌላ ሰው ስለ እነርሱ ጥሩ እናውራ:: "የእኔ ልጅ እኮ እንዲ ነው፤ ልጄን እንዴት እንደምወዳት ታውቃላችሁ አይደል" እያልን እነርሱ እንዲሰሙ ሆነን እናውራ:: ይህን ፍቅር ከሁሉ ከሚያምኑት ከወላጆቻቸው ሲገለጽ መስማታቸው የልጆቻችንን ዓለም በትልቁ ይለውጠዋል:: ስለ ራሳቸው ያላቸው አመለካከት ብሩህ እንዲሆን ያደርጋል:: በሕይወታቸው ደስተኛ እንዲሆኑ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል:: "እናቴ በእውነት ትወደኛለች፤ አባቴ በእውነት ይወደኛል" ብለው በእኛ ተደስተው ያድጋሉ::

ከአንድ በላይ ካለንም ሁሉም ልጆቻችን እኩል እንደምንወዳቸው ማወቅ አለባቸው:: በፍጹም አንዱን ልጅ ከሌላው አብልጠን አንያዝ:: ሳናስተውለው፤ አንዳንዴ እንደዚያ እናደርጋለን:: ለአንድ ልጅ የተለየ አትኩሮት፣እንክብካቤ፣ ቦታ ...ወዘተ እንሰጣለን:: ይህ

አይነቱ ነገር ልጆችን በጣም ይጎዳል:: የልጅን ውስጣዊ ጥንካሬ፣ ጉብዝና፣ ራእይ ያጨልማል:: ከዚህም በላይ፣ በወንድምና እህት መካከል ያለውን ንጹሕ ፍቅር ያበላሻል:: ልጆች የማየት ክህሎት አላቸው:: አያውቁም የምንለውን ነገር እንኳ የማወቅ ችሎታ አላቸው:: የማያይ የሚመስል ልጅ እንኳ እነዚን ነገሮች ያስተውላል:: አንድ ልጅ ለወንድሙ ለእህቱ ከሱ የተሻለ አቀራረብ እንዳለን ሲያይ፣ "እኔን ስለማይወዱኝ ነው፤እህቴ የተሻለ ነገር ስላላት ነው" ወይም "እኔ እንደዚያ ወንድሜ እንደዚህች እህቴ እንዳይወዱኝ የሚያደርገኝ ደካማ ነገር ስላለኝ ነው" የሚል መንፈስ፣ ውስጣቸው ይቀበራል::

እዚህ ጋር አንድ ነገር ልብ እንበል:: በውጭ የቤተሰብን እንክብካቤ የማይፈልግ የሚመስል ልጅም ከሌላው ወንድምና እህቱ እኩል የቤተሰብን አትኩሮት ይፈልጋል:: ይህ ማለት፣ ፍቅራችንን የምንሰጥበት መንገድ ለሁሉ ልጅ አንድ ዐይነት መሆን አለበት ለማለት አይደለም:: በእርግጥ እያንዳንዱ ልጅ ተፈጥሮው የተለያየ ነውና፣ ከእኛ የሚፈልገው የአትኩሮት አይነትና መጠን የተለያየ ሊሆን ይችላል:: ሴት ልጃችን ዐቅፈን እንድንስማት ትፈልግ ይሆናል። ወንዱ ደግሞ ከወላጅ ጋር ቁጭ ብሎ ስለ ስፖርት ማውራት ይፈልግ ይሆናል:: አንዳንድ ልጅ በፍቅር ሙገሳ የተሞላ ንግግራችን ከፍተኛ ደስታ ሊሰጠው ይችላል:: ሌላ ልጅ ደግሞ ከወላጅ ጋር ብቻውን ጊዜ ማሳለፍ በጣም ያስደስተው ይሆናል:: የልጅን ጸባይና ፍላጎት ገምግመን አቀራረብ እና ፍቅር አገላለጣችንን መለዋወጡ ጥሩም፣ አስፈላጊም ነው። ነገር ግን፣ ለአንድ ልጅ የተለየ እንክብካቤ እንዳለን ፣ የበለጠ እንደምንወደው እና የበለጠ ቦታ እንድምንሰጥ ...ወዘተ የሚያሳይ ነገር አናድርግ፤ በንግግርም አንግለጽ::

"አባት የእዚህ ልጅ ደጋፊ እናት የዚያች ልጅ ወዳጅ ነች"፣ የሚለውን አባባል እናቁም:: "ከእናንተ ልጆቼ መካከል ማንንም ከማንም አላስበልጥም፤ በእኔ አይን ሁሉ እኩል ነው" ብለን ሁሌ እንንገራቸው:: ልጆች መጥተው ደግሞ ከወንድም እኅት አንዱን





እንደምናስበለጥ ሲነግሩን ነገሩን በደንብ እናጢን:: የእውነትም እኛ ደግሞ ላንድ ልጅ የበለጠ ማድረግ ጀምረንም ከሆነ፣ ያንን ስምተን በቶሎ እናስተካክል፤ ልጅ የፈለገውን ነገር ለማግኘት በመሻት የሚለው ነገር ከሆነም፣ በተገቢው መንገድ፣ "እኔ ሁላችሁንም እኩል እወዳለሁ"፣ እንበላቸው::

## *በቤት ውስጥ ያለ ሰላም*

ልጅ ከሚጫወትበት መጫወቻ፣ እንዲሄድ ከሚደረግበት መዝናኛ ሥፍራ፣ ከሚኖርበት ቤት ማማር፣ በቤት ውስጥ ያለው የሰላም አየር፣ በደስታው ላይ የበለጠ ተጽእኖ አለው:: የወላጅ ሰላምና ደስታ፣ በልጆቻችን ሕይወት ውስጥ ትልቅ ተጽእኖ አለው፤ ስለ ሕይወት ያላቸውን አመለካከትም ሊቀይር ትልቅ ሀይል አለው:: እናት ለልጇ ምንስ ጥሩ ብታደርግ፣ እሷ ግን ሰላም አጥታ ተጨንቃ የምትኖር ከሆነ፣ ምሬት ተስፋ መቁረጥን የሚያንጸባርቁ ቃላቶችን ሁሌ የምትናገር ከሆነ ልጅ ሰላሙን ያጣል:: አባቱ በውጥረትና እረፍት ማጣት ሁሌ ሲመላለስ እያየ ካደገ ልጅም ደስታን አጥቶ ይኖራል:: ያኔ በልጅነት ያስተዋለው የእናት እና አባቱ የውጥረት ኑሮ፣ መካሪውና አስታዋሹ ይሆናል:: መቆዘም እና ሁሌ ትንፋሽን ይዞ መሯሯጥ የሕይወት ክፍል መሆን እንዳለባቸው፣ ከሚወዳቸው እናትና አባቱ ይማራል:: ፈገግታ፣ ሰላም፣ ያረፈ መንፈስ የሕይወታቸው ክፍል የሆነ ወላጆች ደግሞ ተቃራኒውን ትምህርት ለልጃቸው ያቀብላሉ፤ወደፊት ሕይወታቸውን ሊመሩባት የሚገባውን ትልቅ ምሳሌ ያስተምሯቸዋል:: ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችን ስንል ከውጥረት ሕይወት ለመራቅ፣ በሰላም መንገድ ሕይወትን ለመምራት የሚያስችሉንን እርምጃዎች እንውሰድ:::

በባልና ሚስት መካከል ያለ ወይም የሌለ ሰላም፣ ልጅ ሕይወት ላይ ትልቅ ተጽእኖ አለው::

> "ልጅን በጥሩ ሁኔታ ለማሳደግ ምን ማድረግ አለብን ለሚለው ጥያቄ፣ ለአመታት የተደረጉ ጥናቶች እንደሚገልጹት፣ ወላጅ ከልጅ ጋር የሚኖረው ፍቅራዊ ትስስር ከሁሉም ዋነኛው ነው። ከፍቅራዊ ትስስር

ቀጥሎ ልጅ ላይ ዋነኛ ተጽእኖ ያለው፣ አባትና እናት እርስ በእርስ ያላቸው ግንኙነት እና ከወጀብ ነጻ የሆነ ሰላማዊ ሕይወት መምራታቸው ነው። እነዚህ የቤተሰብ ልምምዶች ለልጅ በቀጥታ ከምናደርግለት ሌሎች ነገሮች የበለጠ፣ ለደህንነቱ ያበረክታሉ።"[3]

ባልና ሚስት እየተፎካከሩ፣ እኔ ዐውቃለሁ ብለው፣ እርስ በእርሳቸው እልህ እየተያያዙ፣ ልጄን ስለምወድ ብለው በተናጥል ብዙ ከሚያደርጉለት ይልቅ፣ አንድ ላይ ቆመው ሰላምን መያዛቸው፣ ለልጅ ሕይወቱ ዕጥፍ ደስታ ያመጣለታል:: በሌላ በኩል፣ በተናጠል ምንስ ነገር ቢደረግለት፣ በአባትና እናት መሀል ጥልና ፉክክር እስካለ ድረስ፣ ያ የምንሰጠው ነገር ሁሉ ሊያስደስተው ሀይል ያጣል:: ልጅ ሁሉን ያስተውላል:: እነዛ የሚወዳቸውና ወደላይ ከፍ አድርጎ የሚመለከታቸው ወላጆቹ ጤነኛ ባልሆነ ነገር ውስጥ እንዳሉ ሲያይ፣ ሰላምና ደስታው እንዲጠፉ፣ ከዕድሜው በላይ እንዲያስብና ውስጡ እንዲቆዝም ያደርገዋል::

## የሚያድሳቸውን ለማወቅ የልጅን ፍላጎት ማጤን

ልጆቻችን የሚፈልጉትን በትክክል ለመረዳት ማየትና ማዳመጥ፣ ልጆቻችን የእውነት የሚያድሳቸውን ነገር መስጠት እንድንችል ያደርገናል:: ብንሰማቸው፣ ብንገመግማቸው ልጆቻችን በአፋቸው ባይነግሩን እንኳ በተለያየ መንገድ ከእኛ የሚፈልጉት ምን እንደ ሆነ ያሳዩናል:: የሚያስደስታቸውን ነገር ስንል፣ ልጆች ጊዚያዊ ደስታ ሲፈልጉ "ይሄንን ብትገዙልኝ፣ ብታደርጉልኝ ደስተኛ እሆናለሁ" ብለው ለደቂቃ የሚናገሩትን ዐይነት ፍላጎት ማለት አይደለም:: የእውነት ውስጣቸውን የሚገነባቸው፣ ቀናቸውን የሚያበራላቸው ምን ስናደርግላቸው እንዴት ስናወራቸው እንደሆነ፣ በተለያየ መንገድ ያሳዩናል:: ጥንቃቄ ካልወሰድን፣ "ልጆቼ በእውነት የሚያስደስታቸው ነገር ምንድን ነው?" ብለን ቀስ ብለን በመገምገም

3 Epstein 2010 Robert Epsteing Scientific American Mind November 2010 issue page





ፈንታ፣ ያስደስታቸዋል ብለን በራሳችን በወሰንነው ነገር ውስጥ ልንራራጥ እንችላለን:: በዚያ መንገድ ከቀጠልን ደግሞ፣ ፍየል ወዲህ ቅምዝምዝ ወዲያ እንደሚባለው ከልጆቻችን ጋር በተለያየ አቅጣጫ ሮጠን በኋላ ልንነቃ እንችላለን::

ብዙ ያደጉ ልጆች "እኔ ልጅ ሆኜ የምፈልገው ነገር ይህ ነበር፤ ነገር ግን ቤተሰቦቼ ያንን ከልብ የሚያስደስተኝን ነገር ሳይሰጡኝ ዐደግሁ" ብለው ያወራሉ:: ምናልባትም እነዚያ ወላጆች፣ ደስተኛ ልጆች ካፈሩት ወላጆች እኩል ልጆቻቸውን ይወዱ ነበር ይሆናል:: ነገር ግን፣ "በዚህ ሂደት ውስጥ ልጅ ቦታ የለውም፤ የልጅ ነገር ልጅ ነው፣ለልጄ የሚሆነውን ነገር ሁሉ እኔ ዐውቃለሁ" ብሎ በራስ መንገድ ብቻ የመሮጥ ያመጣው ጣጣ ነው::

በአሜሪካ ውስጥ የታወቀ ፊልም ሰሪ የነበረ አረን ስፔሊንግ (Aaron Spelling) የሚባል ሰው ነበር:: ይህ ሰውና ቤተሰቡ የሚኖሩበት መኖርያ ቤት ትልቅነቱ በካሊፎርንያ ውስጥ አንደኛ ነው ይባል ነበር:: የዚህ ሀብታምና ታዋቂ ልጅ ዛሬ በእድሜ ትልቅ ሆና ስለ ሕይወት ታሪኳ የሚናገር መጽሐፍ ጽፋለች:: ቶሪ ስፔሊንግ (Tori Spelling) የምትባለው ይህች ሰው፣ "sTori TELLING" በሚለው መጽሐፏ ላይ፣ ስለልጅነት ጊዜ ትዝታዋ እንዲህ ስትል ታወሳለች:: ጓደኞቼ "እንዴት ታድለሻል" እያሉ ይቀኑብኝ ነበር:: እውነትም እናቴና አባቴ በጣም ብዙ ገንዘብ ነበራቸው:: በልጅነት ዘመኔ፣ ሊያስደስቱኝ ፈልገው በገንዘባቸው ተጠቅመው በጣም ብዙ ያደርጉልኝ ነበር:: አባቴም፣ "ልጄ አንቺን ስለምወድሽ ይህን ይህን አደርግልሻለሁ" እያለ ገንዘቡን ብዙ ነገር ላይ ያወጣ ነበር:: በዚያ በልጅነት ዘመኔ ከሚገዛልኝና ከሚያደርግልኝ ብዙ ነገሮች ሁሉ በላይ የሚያስደስተኝና በናፍቆት የምጠብቀው የነበረው ፣ በስንት ጊዜ አንዴ አብሮኝ የሚያሳልፋቸው ጥቂት ጊዜያት ነበሩ:: እነዚያ ጥቂት ጊዜያት ለኔ ምን ያህል ዋጋ እንደነበራቸው ቢያቅ ኖሮ፣ ከመሞቱ በፊት ቢረዳ ኖሮ ብዬ እመኛለሁ ብላ መጽሐፏ ላይ ታወሳለች:: ስለ እናቷም ስታነሳ፣ ከዚያ ያልተለየ ትዝታን ታወሳለች:: ከእሷ በላይ የጠቀመችኝ እና ብዙ ያደረገችልኝ

የምወዳት የልጅነት ሞግዚቴ ነች፤ እናቴ ከገዛችልኝ ውድ እቃ ሁሉ በላይ ሞግዚቴ የሰጠችኝ ፍቅር ትልቅ ጥቅም ሆኖልኛል ብላ የልጅነት ጊዜ ትዝታዋን ትተርካለች።[4]

እነዚህ እናትና አባት ልጃቸውን ይወዱ እንደነበር ጥርጥር የለውም። ይሁንና፣ "ልጃችንን የእውነተኛ ደስታ የሚሰጣት ምንድነው?" ብለው ቆም ብለው የእሷን ሕይወት አልገመገሙም፤ ምክንያቱም ለእርሷ ሕይወት ጥቅም የሌለው ነገር ላይ ሀይልና ጊዜያቸውን ሲያወጡ ኖረዋል። እኛም ሳናስበው በተመሳሳይ የስህተት ወጥመድ ውስጥ እንዳንገባና ለልጆቻችን ዋነኛ የሚባሉ ነገሮችን እንዳንነፍጋቸው እንጠንቀቅ።

ሴት ልጃችን፣ አብረናት ለአምስት ደቂቃ ስለ ትምህርት ቤቷ ስናወራት ያ በጣም ሊስደስታትና ቀኗን ብሩህ ያደርግላት ይሆናል። እናቷ ዐይን ዐይኗን እያየች ስለ ቀኗ ከልቧ ማዳመጧ ለልጇ ትልቅ ደስታ ይሰጣት ይሆናል። እናት ግን የእሷን ፍላጎት ሳታስተውል በራሷ መንገድ ትሄድ ይሆናል። "ለልጄ ጥሩ የሆነው፣ ሠርቼ ይህ የምገዛላት ነገር ነው" ብላ በማሰብ ኀይሏን ለልጇ ህይወት ምንም ዋጋ የሌለው ነገር ላይ ልታወጣ ትችላለች። "በይ ባክሽ ጊዜ የለኝም፤ ይልቅስ አጥኚ" ብለን ሁሌ በመናገር ፈንታ "ዛሬ ቀለል ያለ እራት እንበላለን፤ በሚተርፈን ጊዜ ደግሞ አብረን ቁጭ ብለን እናወራለን"፣ ብላ እናት ከልጇ ጋር ብታሳልፍ፣ ያ ልጇን የሚያበረታታት፣ የሚያስደስታት፣ ቀኗን የሚያበራላት ነገር ሊሆን ይችላል።

ወንድ ልጅ ለምሳሌ ከአባቱ ጋር የሚኖረው፣ አብሮ የሚያሳልፈው ጊዜ ምን ያህል ውስጣዊ አመለካከቱን፣ ደስታውን እንደሚለውጥና፣ ለሕይወቱ ትልቅ ነገር እንደሚያደርግለት ብዙ አስተማሪዎች ይናገራሉ። ምናልባት ወንድ ልጃችን ያንን የአንድ ለአንድ ጊዜ

[4] Spelling Tori (2008) sTORI TELLING, Simon Spotlight





እየተጠማ ይሆን? ለምሳሌ ስፖርት በትምህርት ቤት ሲጫወት አባቱ መጥቶ ቢያየው፣ ወይም ስለሚወደው ነገር ሲያወራ ቁጭ ብሎ ቢያዳምጠው ያ ሕይወቱንና ስለራሱ ያለውን አመለካከት፣ ከፍ ያደርግለት ይሆናል። እኛ ግን "ለልጄ አሁን የሚያስፈልገው ይህ ነው" ብለን በተቃራኒ አቅጣጫ ልንገሰግስ፣ እና ያ አለመስማማት ከልጆቻችን ጋር ሳንግባባ እንድንቀር ሊያደርገን ይችላል። ለልጄ ደስታ የሚሰጣት/የሚሰጠው ይህ ነው በሚል፣ በራሳችን ውሳኔ ብቻ በመሯሯጥ ፈንታ ልጆቻችንን እንይ፤ እናዳምጣቸውም።

ልጆቻችን፣ የሚያስደስታቸውን ብቻ ሳይሆን፣ የሚጎዳቸው ነገር ምን እንደሆነ በተለያየ መንገድ ያስታውሱናል። ምን ስናደርግ ወይም ምን ሳናደርግ ስንቀር ውስጣቸው እንደሚጎዳ፣ በተለያየ መንገድ ያሳዩናል። ቁም ነገር ብለን ካላየናቸውና ካላዳመጥናቸው "አዩ እሱ ልጅ ነው ፤ምንም አያውቅም" በሚል ልጃችንን የሚጎዳ ነገር ልናደርግ እንችላለን። እንዲህ አባባሎችን መጠቀምን በመተው ልጆችን እንስማቸው፤ ሁኔታቸውንም እንከታተል።

### *የቤታችን ባህልና ፋይዳ ይኑረን፤*

የራሳችንንና የቤታችንን ባህል እንያዝ። ለእኔና ለቤተሰቤ ምን ያስደስተናል የሚለውን እንጂ "ቆይ በዚህ ጊዜ ሌሎች ሰዎች ለልጃቸው ምን እያደረጉ ነው? ልጅን ለማስደሰት የሚደረገው የሁኑ ዘመን ፋሽን ምንድን ነው?" በሚል ሌሎች ያደረጉትን ለማድረግ አንሞክር። ይህ ዐይነቱ ነገር እውነተኛነትን ደምስሶ አስመሳይ የሆነ ነገር ያመጣል። የራሳችን የሆነ ነገር ስለሌለን፣ የምናደርገው ነገር የማይጥም ይሆናል። ሌላ ቤተሰብን እያየን ሕይወታችንን ከእነሱ ጋር የማስተያየት ልምድ ውስጥ ከገባን ምሬት፣ ዝለት፣ ክስረት እና ውሸት የሕይወታችን ክፍል ይሆናሉ።

ዋናው፣ ልጆቻችን በደስታ የተሞላ ቤት ውስጥ እንዲያድጉ እንጂ፣ የተወሳሰበ ነገር ውስጥ መግባት የለብንም። አብረን ጊዜ እናሳልፍ፣

ከልብ እናውራ እንጂ በራሳችን ነገር ልንዋብ እንችላለን:: ምሳ ሰርተን ከቤተሰባችን ጋር መናፈሻ ሄደን ምሳ እንብላ:: የቤተሰብ ውድድር እንጫወት:: አብረን መጻሕፍት ቤት እንሂድ:: እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ወደሚወደው ቦታ ተራ በተራ እንሂድ:: ቤተሰቡ በመላ በኅብረት ሄደን የበጎ አድራጎት ሥራ እንሥራ:: ቤታችን ውስጥ "የፊልም" ምሽት ብለን ቤተሰብ ሁሉ ተሰብስበን እንይ:: ቁጭ አድርገን ስለ ድሮ አስተዳደጋችን እናውራቸው:: ፍቅራችን ተጠናክሮና ደስታችን ሰምሮ እስከ ቀጠለ ድረስ የቤተሰብ ባህላችንንና ወግ ተከትለን መኖር እንችላለን::

ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ ለልጆቻችን ያማረ ያበበ ሕይወት ለመስጠት "ሁሉ መስተካከል አለበት" ብለን አናስብ:: የተጓደሉ ነገሮች በሕይወታችን እያሉ፣ ግን ለልጆቻችን ውብ የሆነ የልጅነት ጊዜን ልንሰጥ እንችላለን:: ዋናው ነገር ችግሩን ቆመን እያየን ሀይልና ጊዜን አለማጥፋት፣ በዋነኝነት ማቀፍ ያሉብን ነገሮችን መረዳታችን ነው::

ሕይወቱን በሙሉ፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ እርስ በእርስ መተሳሰር አስፈላጊነት ሲያስተምር የኖረ፣ በብዙዎች የተወደደ፣ ሊዮ ቡስካግሊያ (Leo Buscaglia) የሚባል የታወቀ ጸሀፊና ተናጋሪ ነበር:: ይህ ሰው በንግግሮቹና በጽሁፎቹ፣ በብዛት ስለ ልጅነቱ ጊዜ ያወሳ ነበር:: ከጣልያን አገር መጥተው አሜሪካ በጥገኝነት በሰፈሩ እናትና አባት ስር ነው ያደገው:: እናት አባቱ ከአገራቸው መጥተው በዚህ ባሜሪካ ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ፣ ብዙ የኑሮ ፈተና አጋጥሟቸው ነበር:: ከተለየ አገር መጥተው በማያውቁት አገር ልጆቻቸውን ሲያሳድጉ ብዙ ገንዘብ አልነበራቸውም:: ባላቸው ትንሽ ገንዘብ፣ የሚያስተዳድሩት ብዙ ልጆችን ነበር:: ባጠቃላይ የሌላ አገር ሰው መሆናቸው፣ ከድህነታቸውና ከልጆቻቸው ብዛት ጋር ተጨምሮ ሸክም ነበረው:: በዚህ ሁሉ መሀል ግን ምን ያህል ጣፋጭ የሆነ የልጅነት ጊዜ እንዳሳለፈ ይህ ሰው ደጋግሞ ይናገር ነበር:: ቤታቸው ውስጥ ሳቅ፣ ጨዋታ፣ ፍቅር፣ መተቃቀፍ እንደ ነበር ያወሳል:: ወላጆቹን ልዩ ያደረጋቸውን ነገር ሲናገር፣





ለራሳቸው ቁጭ ብለው በማዘን ፈንታ ባላቸው ይዋቡ እንደነበር ያናገራል:: ይህና ያ ጎደለ ሳይሉ፣ ራሳቸውን ከሌላ ጋር ሳያስተያዩ፣ ባላቸው ለልጆቻቸው ይሰጡ የነበረው ፍቅር፣ ምን ያህል ያበበ ህይወት እንዲኖረው እንደረዳው ይገልጻል:: በራሱ በማንነቱ እንዲቆም፣ ሌላን እንዲወድ፣ የጠቀመው፣ ያ ከቤተሰብ ያገኘው እውነተኛ የሆነው መሰረት እንደሆነም ይጠቅስ ነበር::

ይህ ጎደለ ብለን ችግር ላይ በማተኮር፣ ቆሞም ለራስ በማዘን ፈንታ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ልጆቼን ለመርዳት ምን ማድረግ እችላለሁ ብለን መላ ላይ ካተኮርን፣ በዋናነት መያዝ ያለብንን ነገሮች ከተገነዘብን፣ በራሳችን መንገድ የተሳካ፣ የለመለመ ሕይወት ለልጆቻችን የመስጠት ሙሉ ሀይሉ ይኖረናል::

ያለ አባት ወይም እናት፣ በተናጠል ልጆቻችንን የምናሳድግ ከሆነ፣ ሸክሙ ከበድ ያለ ሊሆን ቢችልም፣ ጉልበታችንን እና ገንዘባችንን በተገቢው መንገድ ከተጠቀምን፣ ለልጆቻችን ውብ የሆነ የልጅነት ጊዜን የመስጠት ኀይል ይኖረናል። ከልጆቻችን ጋር የምንተሳሰርበት፣ ከልብ የምናወራበት ፍቅራችንን በግልጽ የምናሳይበት ተስማሚ ጊዜ ማግኘታችን፣ ዋነኛ ነገር መሆኑን አስታውሰን፣ ሌሎች ውጫዊ ነገሮች ላይ ከመጠመድ ይልቅ እነዚህን ዋነኛ ጉዳዮች እናስቀድም:: ከልጆቻችን ጋር የበለጠ ጊዜ እንዲኖረን፣ ልጆች ቤት ውስጥ እንዲያግዙን እናበረታታ:: ለልጆቻችን ትልቅ ምሳሌ የምንሆነው እኛ ሰላማዊ ሕይወት ሲኖረንና ደስተኛ ስንሆን እንደ ሆነ አስታውሰን፣ ራሳችንን ለመጠበቅ እንጣር:: ሊረዱንና ሊደግፉን የሚችሉ፣ የዘመድ አዝማድ እንዲሁም ወዳጆች ድጋፍ ለመቀበል አንፍራ::

ከዚህ ጋ ተያይዞ፣ ጥሩ የሆነና ሚዛን ያለው ማኅበራዊ ሕይወት፣ በማንኛውም ወላጅና ልጆች ኑሮ ላይ፣ ትልቅ አዎንታዊ ተጽእኖ ሊያመጣልን ይችላል:: ኢትዮጵያውያን ካለን ጥሩ ባህል ውስጥ አንዱ፣ ማኅበራዊ ግንኙነታችን ነው:: የምንወዳቸውና የሚወዱን ዘመድ ወይም ወዳጆች በሕይወታችን

ውስጥ ሲኖሩ፣ ድጋፍ እናገኛለን፤ ከብቸኝነት ነጻ እንወጣለን፤ ሕይወታችንም ይበራል። ልጆቻችንም ከማኅበራዊ ሕይወት የሚገኘውን ፍቅር ቀምሰው ያድጋሉ። አጎቴ አክስቴ የሚሉትና የሚወዱት ቤተሰብ መካከል ከማደጋቸው በተጨማሪ፣ የዕድሜ ጓደኞቻቸውን ያገኛሉ። ዕድሜያቸው ተቀራራቢ የሆኑ ሌሎች ልጆች ጋር አብረው በማሳለፍ፣ የሚያገኙት የልጅነት ጊዜም የማይረሱት፣ጣዕም ያለው ትዝታ ያተርፍላቸዋል። ያ ማህበራዊ ሕይወት ከሌለ ቤተሰባችን ደስታና ሰላም አይኖረውም ለማለት አይደለም፤ ተጨማሪ ጣእምን ወደ ሕይወታችን ሲያመጣ ግን ትልቅ ሀይል አለው።

## ማጠቃለያ

በአሜሪካን አገር ካናዳ፣ አውሮፓና በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩ፣ ሕይወታቸውን በመጽሐፍ ያስቀመጡ ብዙ ሰዎች አሉ። የእነዚህ ሰዎች የግል ታሪክን ብናነብ፣ ብዙዎቹን የሚያያይዛቸው አንድ እውነት አለ። ጥሩ የልጅነት ጊዜ ነበረኝ ብለው የጻፉ ሰዎች፤ፍቅር፣ የቤተሰብ የጋራ ጊዜ፣ መከባበር፣ ወዘተ ዋነኛ ነገሮች እንደነበሩ ያወሳሉ።

በአንጻሩ ደግሞ ምድራዊ ንዋይ ኖሮአቸው እነዚህ ነገሮች ስላልነበሯቸው ሕይወታቸው ምን ያህል አሳዛኝ እንደነበር የጻፉ ብዙ አሉ። ከዚህ ተመክሮ እንማር። ማስቀደም ያለብንን ጥቂትና ዋና ነገሮች እንቀፍ፤የኛና የልጆቻችን ዘመናት የደስታ፣ የተድላና፣ የፍሥሐ ጊዜ እንዲሆን ጠንክረን እንሥራ።





# የሕይወት ተሞክሮ



## የእህት ጣእም

ዛሬ 23 አመት ሰው ሆኜ መለስ ብዬ ቤተሰቦቼ ያደረጉልኝን ሳየው ከድሮው በበለጠ በጣም አመሰግናቸዋለሁ። አንድ ነገር ምን ታውቂያለሽ ተብዬ ብጠየቅ፣ ወላጆቼ ሁሉን ያደረጉት "ለልጆቻችን ምን ይጠቅማቸዋል" ከሚለው ቦታ ተነስተው ነው። ከተወለድንበት ጊዜ ጀምሮ፣ ዋና አትኩሮታቸው የነበረው የደስታ ሰላም፣ ልምላሜ የተሞላበት ህይወት እንድንኖር በመጣር ላይ ነበር። የእኛ፣ ፍቅርን አግኝቶ ማደግ፣ ለቤተሰቦቼ ዋነኛ ነገር ነበር። ልዘርዝረው ብል ያደረጉልኝን አልቆጥርም፤ ግን አርቀው አስበውና አይተው ካደረጉልኝ ዋና ነገር ብዬ የምለውን ልጥቀስ።

እኔና እህቴ ከሚገመተው በላይ ተቃራኒ የሆንን ሰዎች ነን። እንደዛ ስል የማጋነን ሊመስል ይችላል። ግን እውነቱ ያ ነው። እህቴ፣ ፍጥነትን፣ እንቅስቃሴንና አዲስ ነገርን የምትወድ ሰው ናት። የተሰማትን ወዲያው የምትናገር፣ ካገኘችው ሰው ጋር ወዲያው ተግባብታ የምታወራ፣ ሰው ናት። ከሷ ጋ ተቀምጦ አንድ ሰው የድብርት ስሜት ይሰማዋል ለማለት ይከብደኛል።

በተቃራኒው፣ እኔ በተፈጥሮዬ እርጋታ ጋ የተዛመድኩ ሰው ነኝ። ስወስን ቀስ ብዬ ነው ፤ አዲስ ነገር ውስጥ ቶሎ መግባት አያስደስተኝም። ጊዜዬን ወስጄ ቁጭ ብዬ ነገሮችን መመልከት ማየትና መገምገም፣ ማጥናት ማብሰልሰል ውስጤን ያስደስተኛል።

የእኔና አንድ እህቴ ጸባይ፣ ልዩነቱ የታየው፣ ገና ከእናታችን ማህጸን ጀምሮ ነው። እኔ እናቴ ማህጸን ውስጥ እያለሁ እንኳ፣ ተመችቶኝ በእርጋታ ጸጥ ብዬ ከመተኛቴ የተነሳ፤ ቤተሰቦቼ፣ "ይህ ጽንስ አይንቀሳቀስም፤ ይህች ልጅ ደህና ነች እንዴ" ብለው፣ ከመጨነቅ ደረጃ ደርሰው ነበር። በተቃራኒው ታናሽቱ እህቴ፣ ገና ማህጸን ውስጥ እያለች እየተንፈራገጠች፣ መወለጃ ሰአቷ መድረሱን ለማስታወቅ ትሞክር ነበር። የመወለጃ ሰአቱ እንደዘገየበት ሰው ስትንፈራገጥ፣ ወላጆቼ ይህችኛዋ ፍጹም የተለየች እንደሆነች ገምተው ነበር።

ከገለጻዬ እንደሚታየው እኔና እህቴ በጸባይ በአሰራር አመለካከት በጣም ተቃራኒ የሆንን ሰዎች ነን፤ ህይወትንም የምናይበት መነጽር በጣም የተለያየ ነው። እንደዛም ሆኖ፣ እህቴ ዋነኛ የልቤ ጓደኛዬ ነች ብል ማጋነን አይሆንም። የጋራ የሆነ የሚያገናኘን አንድ ጸባይ ሆነ አመለካከት ባይኖረንም እህቴ ከህትነት ያለፈች ውዴ ነች።የልቤን የምነግራት በስቃይ ሆነ በደስታ ጊዜ ዞሬ የማማክራት ጓደኛዬ ናት። ከእህቴ ጋር ያለኝ ግንኙነት ከልቤ የምደሰትበት በህይወቴ የምረካበት ነው። ለዚህም ደግሞ፣ በዋነኝነት የማመሰግነው፣ ወላጆቼን ነው፤ ምክንያቱም እኔና እህቴ እንዲህ አይነት ግንኙነት ሁሌም አልነበረንም።

በእኔ እና በታናሽ እህቴ ሳራ መሀል የአራት አመት ልዩነት አለ። እውነቱን ልናገር ብል፣ በአስራዎቹ አመታት ውስጥ እያለሁ፣ ስራዋ ሁሉ ያናድደኝ ነበር። "እየረበሸችኝ ነው" ብዬ የምማረርባቸው ብዙ ጊዜዎች ነበሩ። ፍጹም የተለያየን ሰዎች





ነበርንና፣ የጋራ የሆነ መኝታ ቤት ውስጥ መተኛት፣ በጋራ መጫወቻዎች መጫወት በጣም ይከብደን ነበር። ብዙ ጊዜም እንጣላና እንጯጯህ ነበር። በተለያየ ጸባያችን ምክንያት እንደዛ ብንጣላም፣ ወላጆቻችን ሁሌ አብረን ጊዜ እንድናሳልፍ ያደርጉ ነበር። በእህትና እህት መሀል መዋደድ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ደጋግመው ይነግሩን ነበር። የሆነ ቦታ ልሄድ ብዬ ከተነሳሁ፣ ወይም የሆነ ነገር ላድርግ ብዬ ስነሳ ከወላጆቼ የሚመጣው ጥያቄ "እህትሽስ፣ እሷንስ ለምን አትወስጃትም" የሚል ነበር። በዛ ጊዜ የምማረርበት፣ ምንድነው የሚያስጨንቁኝ ብዬ የማስብበት ብዙ ወቅት ነበር። በኋላ ግን አብረን ጊዜ እንድናሳልፍ እኛን በማበረታታቸው፣ ዋነኛ ስጦታ እንደሰጡኝ ተረዳሁ። እኔ የሌለኝ ጠንካራ ጎን፣እህቴ አላት፤ እሷም የሌላት እኔ አለኝ። አብረን ብዙ ጊዜ ስናሳልፍ፣ ከእርስ በእርስ መማማር ጀመርን። ከእርስ በእርስ ከመማማርም አልፈን፣ እርስ በእርስ መከባበር ጀመርን።ቀስ በቀስ ጥላችን ወደ አብሮ መጫወት፣መጮጯሃችን ወደ ሳቅና ፈገግታ ተለወጠ። ያ አብቦ ዛሬ እህት ብቻ ሳይሆን ጓደኛም ሆነናል። በአሁኑ ጊዜ 80 ከመቶው የሚሆነው፣ የምዝናናበት ጊዜ ከእህቴ ጋር አብሮ መሆን ያስደስተኛል። የእኔ ጓደኞች የእሷም ናቸው። ሁሌ አብረን ነንና፣ አንድ ቦታ እንኳ ብቻችንን ከታየን፣ "እህትሽ የታለች" መባላችን አይቀሬ ነው።

አሁን መለስ ብዬ ሳስበው፣ ወላጆቼ ስራዬ ብለው በእኔና በአንድ እህቴ መሀል ያለው ግንኙነት እንዲያብብ እንደጣሩ እረዳለሁ። እናትና አባቴ፣ ከብዙ ቤተሰብና ወዳጅ መሀል ከነበሩበት፣ ከአገራቸው ርቀው እዚህ ፍጹም የተለየ ባህል ውስጥ መጡ። ኢትዮጵያ ያደጉበት አካባቢ ጎረቤት ወዳጅ ዘመዱ ተሰብስቦ ልጅን ያሳድግ ነበር። እዚህ ሲመጡ ግን እናትና አባቴ ሁሉን የተጋፈጡት ብቻቸውን ነበር። በዚህ ብቸኝነትን በሚያበረታታ ባህል ውስጥ ለእርስ በእርስ ያለነው እኔና እህቴ እንደነበር ይረዱት ነበር። እንደወላጅነታቸው ስራዬ ብለው፣ በእኔና እህቴ መሀል ትስስር እንዲኖር ካላደረጉ፣

ውጤታችን የሚሆነው ተራርቆ ማደግ እንደሚሆን እናቴና አባቴ ከመጀመሪያውኑ ተረዱት፤ ትልቁን የቅርርብ ስጦታ፣ በዛ መልክ ለእኛ ለልጆቻቸው አስረከቡን::

ወንድም እህት ሁልጊዜያቸውን አብረው እንዲያሳልፉ መጣሩ እነሱን ለማቀራረብ ብቸኛው መላ ነው ለማለት ብዬ አይደለም:: ወንድምና እህት ስለሆኑ ብቻ ይቀራረባሉ ብለን ደምድመን መተዉ ግን ጥሩ ላይሆን ይችላል:: እህት፣ ወንድም እንዲዋደዱ፣ እንዲቀራረቡና ለእርስ በርስ እንዲተሳሰቡ ወላጅ ስራዬ ብሎ ግንኙነታቸውን ማነጽ፣ ማነጋገሩ ትልቅ ጥቅም አለው ብዬ አስባለሁ፤ በልጅነት የታነጸ ግንኙነት ሲያድጉም ይቆይላቸዋል፤ እኔና እህቴ እንደሆንነው ለእርስ በርስ ድጋፍ እንዲሆኑ፣ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋልና::





# ምዕራፍ ሁለት

## የልጆች ለቁምነገር መብቃት

ልጆች እንዴት ለቁምነገር ሊበቁ ይችላሉ? የሚለው ጥያቄ መሰረታዊ ጥያቄ ነው። ልጆቻችን ለቁም ነገር እንዲደርሱልን ማድረግ ያለብንን በተመለከተ፣ ዋነኛው ነገር እኛ የምንሰጣቸው ድጋፍና እገዛ ነው:: ከእኛ የሚያገኙት ድጋፍ፣ የእነርሱ ወደ ሆነው ትልቅ ቦታ እንዲደርሱ ይረዳቸዋል::

### *1) __ወላጅ በልጁ ማመን አለበት__*

"ልጅዎ ስለራሱና ስለችሎታው የሚኖረው አዎንታዊ አመለካከት፣ ከእርስዎ ዕለት ተዕለት በሚያገኘው ድጋፍ ይወሰናል።"[5]

ወላጅ በልጁ መተማመኑ፣ "አስፈላጊ እርዳታና ድጋፍ ያገኘ እንጂ ልጁ ሊደርስ የሚገባው ጥሩ ቦታ ይደርሳል" ብሎ ጉዞውን መጀመሩ፣ ሁሉን ይወስናል፤ እውነት ሆኖ የሚወጣው ከልብ ያመንበት ነገር ነውና::

ልጃችንን የማናምንበት፣ትልቅ ቦታ አይደርስም ብለን በውስጣችን የምናስብ ከሆነ፣ ከሁኔታችን ሊገነዘበው ይችላል:: እኛ አፋችንን አውጥተን ባንናገር እንኳ፣ ከውስጣችን ያለው የተደበቀ እምነት በተለያየ መልክ ተፈናጥቆ ወጥቶ ይታያል:: "አላምንብህም፤ ትልቅ ቦታ አትደርስም" እያለ፣ የልጃችንን አቅጣጫ ይመራል::

[5] Dyer Wayne (1985) <u>what do you really want for your children</u>, Addison Wesley publishing company.

አዎ፣ አንዳንዴ የልጃችንን ጠባይ፣ ፍላጎትና አደራረግ ከወዲሁ ገምግመን፣ "አይ፣ እንጃ ይህ ልጅ ትልቅ ቦታ የሚደርስ አይመስልም" ብለን እናስባለን:: አንድ ትልቅ እውነት እናስታውስ:: ማንም ልጅ ቢሆን ከተደገፈ ይለመልማል፤ከነበረበት ወደ ላይ ይነሣል:: ይህ ሁሉንም ልጅ የሚያገናኝ እውነት ነው፤በራሱ በሆነውና በተወለደበት ችሎታው አሠራሩ ያብባል፤ የራሱ በሆነ መንገድ ያድጋል ይመነደጋል:: እያንዳንዱ ስር ሊያብብ፣ልዩ ፍሬን ሊያወጣ እንደ ተፈጠረ፣ የሚጠብቀው የእኛን ድጋፍ እንደ ሆነ ተረድተን፣ በነገው ትልቁ ልጃችን ላይ እንበርታ::

ቃላት ኀይል አላቸው::ቃላቶቻችን ልጆቻችንን ፍቅር ማሳያ ብቻ ሳይሆኑ ወደ ላይ እንዲመጥቁ የሚያግዙ መሰላል ናቸው:: አዎ፤ልጆቻችን ወደ ላይ እንዲመጥቁ ስንፈልግ፣ ቃላቶቻችን ለመገንባት ወይ ለመስበር ትልቅ ሀይል እንዳላቸው እንረዳ:: ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ለልጆቻችን፣ ያሰቡት ቦታ ሁሉ መድረስ እንደሚችሉ እንንገራቸው:: "እንዲህ መሆን እፈልጋለሁ" ሲሉ አንሳቅባቸው:: ሌላው ቀርቶ እንዲህ መሆን እፈልጋለሁ የሚሉት ነገር የማይቻል ቢመስለን እንኳ፣ በመሳቅ ፋንታ ያ ውስጣቸው የተቀመጠውን፣ ትልቅ ቦታ የሚያየውን ኀይል ማበረታታትና መደገፍ አለብን:: ለምሳሌ ልጃችን መጥታ፣ "የዓለም አንደኛ እግር ኳስ ተጫዋች መሆን እፈልጋለሁ" ብትለን በልባችን ዋናው ማሰብ ያለብን "እንዴት የማይሆን ነገር ተናገረች"፣ የሚለውን አይደለም፤ይህ በውስጧ የተቀመጠውን ወደ ትልቅ ቦታ ለመመዘዝ የሚያስበውን ኀይል እንዴት ማበረታታት እንዳለብን ነው:: ሲሆን፣ "አዎ ትችያለሽ ልንላት፣ አለበለዚያም ያንን ትልቅ ቦታ የሚያየውን፣ በውስጧ የተቀመጠውን ውድ የሆነ ኀይል መደገፍ ይኖርብናል:: "ትልቅ ቦታ ታስቢያለሽ፣ የራስሽ የሆነ ህልም አለሽ፤ ያ በጣም ጥሩ ነው"፣ ብለን ማበረታታት አለብን:: ዋናው የሚፈለገው ትልቅ ቦታ አነጣጥሮ የሚያይ ዓይን ልጃችን ያላት መሆኑ ነው እንጂ፣ እግር ኳሱ ነገ በሌላ ህልም ይተካል::





ልጃችን እንዲህ እሆናለሁ ብላ ስትናገር ግን፣ አዬ ብለን ብንስቅ፣ ወይም ይህ ከንቱ ምኞት ነው ብንል፣ ሳናውቀው አፍራሽ መልእክት እየላክን ነው:: እናስታውስ፤ ልጅ ሁሉን ነገር በውስጡ ይመዘግባል:: የዛሬ ትንሿ ልጃችን፣ እራሷን ትልቅ ቦታ አይታ እንዲህ እሆናለሁ ስትለንና እኛ የፌዝ ሣቅ ስንስቅ፣ መልእክት እያስተላለፍንላት ነው:: "ከሰው ለየት ያለና ትልቅ ቦታ ማሰብ ሞኝነት ነው" እያልናት ነው:: ጭራሽኑ ትልቅ ቦታ ራስሽን አትይ እያልናት ነው፤ በድርጊትና በቃል ሳናስተውለው፣ ልጃችንን እያሰናከልን ነው። የልጅን ኀሳብ ከማጣጣል እንቆጠብ፤ ዋናው ነገር፣ በልጅ ውስጥ፣ ትልቅ ቦታ የሚያይ፣ ለትልቅ ነገር የሚያነጣጥር፣ኀይል መኖሩ እንደሆነ ተረድተን እናበረታታቸው፤ ጠንክረው ከሰሩ የማይቻል የለምና::

ልጆቻችን ሲጎብዙና በሆነ ነገር ሲመጥቁ ስናይ በቶሎ እናበረታታቸው:: "ጎበዝ ልጄ በጣም በርትተሀል"፣ ብለን ምን ያህል እንደተደሰትንባቸው እናስታውቃቸው:: እየሰሙ፣ ሰው ፊት ስለ እነርሱ ጉብዝና፣ ስላደረጉት ጥሩ ነገር እናውራ:: "የእኔ ልጅ እኮ በዚህ ይህን ነገር አከናውኗል፤ልጄ እኮ ያንን ግሩም ጽሁፍ ጻፈች እያልን፣ ስለ ሁሉም ልጆቻችን ጥሩ ስለሰሩበትና ስለ ጎበዙበት ነገር ለዘመድ ወዳጅ እናውራ:: እንዲህ ሰው ፊት ስለ እነርሱ ጉብዝና ስንወራ፣ ምን ያህል እንደኮራንባቸው፣ ባደረጉት እንደተደሰትን ያሳያቸዋል፤የበለጠ ለመስራትም ይበረታታሉ::

ልጆቻችንን ትልቅ ቦታ እንደሚደርሱ፣ በማሰብ እናውራቸው:: ያ ማለት ምን ማለት ነው? ለምሳሌ ከአሁኑ ስለ ትልቅ ነገር እናውራቸው:: " ልጄ፣ ወደ ፊት ምን ማጥናት ትፈልጊያለሽ" እንበላቸው፤ይህንንና ያንን ብለው ሲነግሩን፤ በጥሞና እናዳምጥ:: "ለምን ይህን መሆን ፈለግሽ? እንዴት ያ ፍላጎት አደረብህ?" ብለን እንጠይቃቸው:: የሚያስቡት ነገር እውን መሆን እንደሚችል በሚያስገነዝባቸው መልክ እናነጋግራቸው:: ሰው ደጋግሞ ከአፉ የሚያወጣውን ነገር ያምናል:: ለእኛ ሲመልሱ እነርሱም እያሰቡበትና የሚናገሩትንም ከልብ እያመኑ ይመጣሉ::

በእውቀቱና በስራው ዝናን እና ብዙ ታዋቂነትን ያተረፈው፣ አሉ ከሚባሉት ዋነኛ የቀዶ ጥገና ሀኪሞች አንዱ የሆነው ጥቁር አሜሪካዊው ቤን ካርሰን፣ (Ben Carson) ስለ አስተዳደጉ በጻፋቸው መጽሐፎቹ ላይ አንድ ነጥብ ደጋግሞ ያነሳል። ያም እናቱ በሕይወቱ ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳደረገች ነው። ድሃ እናቱ የተማረችው እስከ ሶስተኛ ክፍል ድረስ ብቻ ነበር። ልጆቿንም የምታሳድገው ያለ አባት ብቻዋን ነበር። ይህች ሴት ግን አንድ የተለየ ነገር ነበራት። ለሁለት ልጆቿ ትልቅ ህልም ነበራት። በየቀኑ ቤታቸውን ልታጸዳ ስትሄድ የምታያቸውን ሀብታም ነጮችን በመመልከት፣ "ልጆቼም እነርሱ የደረሱበት ቦታ መድረስ ይችላሉ" ብላ ከልቧ ታምን ነበር።

ቤት መጥታም ለልጆቿ እንዲህ ብላ ታስታውሳቸው ነበር ፤"እነርሱ ከእኛ ምንም አይለዩም። እናንተም፣ እነርሱ የደረሱበት ትልቅ ቦታ መድረስ ትችላላችሁ ብላ ትገነባቸው ነበር። ዝቅ የሚያደርጉ ቃላትን ልጆቿ ፊት ፍጹም አትጠቀምም ነበር። "ባንድ ወቅት መምህሮች ተስፋ የቆረጡብኝ የማይገባኝ ልጅ ነበርኩ፤አምስተኛ ክፍል እያለሁ የክፍሉ የመጨረሻ ዝቅተኛ ውጤት የማገኘው እኔ ነበርኩ። በክፍሉ ውስጥ ቅጽል ስሜም " ያ ደደቡ ልጅ" የሚለው ነበር፤የክፍሉ መሳቂያም ነበርኩ። እናቴ ግን ህልሟ የተለየ ነበር። ታበረታታኝ ነበር። አንተ ደደብ አይደለህም፤ ጥሩ ጭንቅላት አለህ። በርታ ጠንክረህ ስራ እንጂ ያለምከው ቦታ ትደርሳለህ ብላ ታስታውሰኝ ነበር" ይላል። "ሁዋላ ተበረታችቼ፣ ወደፊት ትልቅ ቦታ እደርሳለሁ ብዬ ስነግራትም፣ ምን ያስቆምሀል ትሆናለህ ብላ ታበረታታኝ ነበር"፣ ብሎ ያስታውሳል። የህይወቱ እጣ ምን እንደደረሰ ሲያወሳ እንዲህ ይላል፤ "ከክፍሉ የመጨረሻ የተባለው ልጅ በዓለም ታዋቂ ቀዶ ጥገና ሀኪም ይሆናል ብሎ ማ ሊያስብ ይችል ነበር፤እናቴ ግን ያን ታምን ነበር። ይኸው እኔንም፣ ወንድሜንም ትልቅ ቦታ እንድንደርስ፣ ትልቅ ነገር አበረከተች" ብሎ በፍቅር ያነሳታል።[6]

[6] Carson, Ben; Gifted hands





ልጅ ከማንም በላይ ወላጁን ያምናልና፣ ያለሙበት ትልቅ ቦታ መድረስ እንደሚችሉ በንግግራችንና በድርጊታችን ስናሳያቸው፣ እውነትም ያ እምነት በውስጣቸው እየተደላደለ ይመጣል፤ እምነቱ የሕይወታቸው ክፍል ሊሆን ትልቅ እድል ያገኛል።

ልጆቻችንን ማበረታታት ብቻ አይደለም፤ ምንም የማይችሉ አድርጎ የሚያሳያቸውን አነጋገሮች እናስወግድ። እንዲሁ በግዴለሽነት የምንናገራቸውን ለምሳሌ፣ "አዬ አንተ የማትረባ ነህ፤ መቼም አንቺ ጥሩ ቦታ አትደርሽም፤ አንተ የማያልፍልህ ሰው ነህ፤ አንቺ ደደብ ነሽ" ...ወዘተ የሚሉ አባባሎች በጣም አደገኛ ናቸው። ንግግሮቻችን ልጆቻችንን ሊቀርጹ የሚችሉ ነገሮች ናቸው። የወላጆቹን ቃላት ከልቡ ያምናልና፣ በመጥፎ ቃላት ስንከበው፣ እውነትም ልክ እኛ እንደምንለው መቀረጽ፣ እና ያለውን ጥሩ ነገር ሁሉ ጭራሽ መተው ይጀምራል። የሰደብነው ስድብ፣ አስተሳሰቡን፣ አካሄዱን፣ ውሳኔውንና ህልሙን መቅረጽ ይጀምራል። በግዴለሽነት የምንናገራቸው ቃላቶች ልጆቻችንን እንደሚሰብሩ እና በቶሎ ተስፋ እንዲቆርጡ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ተረድተን፣ ልጅን የሚያቆረቁዙ ስድቦችን ፍጹም እናቁም።

Carson Ben; Think big

## *2) የልጅን ማንነት አክብሮ መያዝ*

ልጃችን እንዲያድግ እንዲያብብ ስንፈልግ፤ በችሎታ በዕውቀትና በአሠራር አንድ ልጅን ከሌላው እያስተያየን፣እንደሱ ብትሆን እንደሷ ብትሆኝ አንበላቸው። ልጅ የሚያብበው፣ ትልቅ ቦታ ለመድረስ የሚዘረጋው፣ በራሱ በሆነው፣ የተፈጥሮው በሆነው አሠራሩ፣ አደራረጉና ጠባዩ እንዲያብብና እንዲለመልም ስናበረታታው ነው እንጂ፣ የራሱ ነገር ዋጋ እንደሌለው ነግረን ሌላውን ልናስገለብጠው ስንሞክር አይደለም።

ልጃችንን፣ በራሱ መስፈርት በመለካት ፋንታ፣ ከወንድም እህት ወይም ከሌላ ከውጭ ልጅ ጋር በማነጻጸር፣ "አንተ በዚህ ነገር እንደ እርሷ ጎበዝ አይደለህም፤ በእዚህ ጉዳይ እንደ እነርሱ አይደለህም" እያልን ዝቅ በሚያደርግ ሁኔታ ስንነግረው ክፉኛ ይጎዳል። ስለ ራሱ፣ዝቅ ያለ አስተሳሰብ ሊኖረው ይጀምራል። "ከቤታችን ጥሩ ነገር የሌለኝ እኔ ብቻ ነኝ" ብሎ እንዲያስብ ይዳርገዋል።በዚህም ምክንያት የራሱ የሆነውንና ሊያብበት የሚችለውን፣ የራሱን የተፈጥሮ ችሎታ እርግፍ አድርጎ ይተዋል። ልጅ ደግሞ የራሱን የሆነውን የተፈጥሮ ነገር ትቶ ሌላን ለመገልበጥ መሞከሩ አድካሚ ብቻ ሳይሆን ጭራሽኑ ወደ ኋላ እንዲቀር የሚያደርገው ነገር ነው። ልጅን ከሌላ ጋር ደጋግመን ስናስተያየው ሲያይ፣ ምሬተኛ ሰው ይሆናል። ሌላ ሰው ለመሆን እየሞከረ ነውና ሁሌ ባለበት ነገር ደስ ሳይለኝ እንደ ተደናቀፈ እንዲያድግ ይሆናል።

ሁሉ ልጅ ሲወለድ ጀምሮ የራሱ የተለየ አስተሳሰብ እና የራሱ የሆነ፣ ደረጃ አወጣጥ አለው። አንዳንድ ልጅ ሰው በቶሎ ይቀርባል፤ሌላው ደግሞ ዝምተኛ ነው፤አንዳንድ ልጅ በተፈጥሮው የተለያየ ነገር ማድረግ ፣መሯሯጥ ይወዳል ። ሌላው ልጅ ደግሞ፣ ቁጭ ማለት ይወዳል። አንዳንድ ልጅ ትምህርት ቤት ገብቶ በቶሎ መጻፍና ማንበብ ይጀምራል። አንዳንድ ልጅ ጊዜ ሊፈጅ ይችላል።



ልጅን እንዴት ላሳድግ? በምዕራብ አገሮች

በትምህርት ጉዳይ ላይ ጥናት ያደረጉ ብዙ ሰዎች እንደሚጠቅሱት፣ ልጆች ትምህርትን በቶሎ የሚቀስሙበት ዘዴም የተለያየ ነው። አንዳንድ ልጆች በማየት የበለጠ ይማራሉ። ሌሎች በመስማት የበለጠ ይማራሉ። በእንቅስቃሴ እጃቸውን በመጠቀም መማር የሚቀላቸው ልጆችም አሉ። ሁሉን ልጅ በአንድ አይነት የማስተማር ዘዴ እንዲበረቱ ከጠበቅን በራሳቸው በሆነው ጥንካሬ በመምጠቅ ፈንታ መካከለኛ ወይም ከዛም ያነሱ እንዲሆኑ መንገድ እንከፍታለን። በሌላ በኩል፣ ልጃችን በቀላሉ እውቀት የሚቀስምበትን ዘይቤውን ተረድተን በዚያ ላይ መደገፋችን፣ በራሱ መንገድ ወደ ትልቅ ቦታ እንዲያመራ ይረዳዋል። የልጆቻችንን ሁኔታና ነገሮችን በቀላሉ የሚማሩበትን ዘዴ ከገመገምን በኋላ፣ በተፈጥሮዋቸው መንገድ እንዲመጥቁም እናበረታታ። የልጅ፣ በቀላሉ የመማርያ ዘይቤውን በተመለከተ፣ ጠለቅ ያለ ግንዛቤ ማግኘት ከፈለግን "children learning style" ብለን ኢንተርኔት ውስጥ ብንፈልግ ጥሩ መረጃን እናገኛለን።

ተፈጥሮአዊ በሆነ ችግር ምክንያት የሆነ ነገር የሚከብደው ልጅ ካለን፣ "ለምን እንዲህና እንደዚያ አልሆነም" ብለን ከመቸገር፣ ትእግስትን ተላብሰን፣ ያ ልጅ ካለበት ሁኔታ መጀመሩ ትክክለኛው ምርጫ ነው። ያ ልጅ ጥሩ የሆነበትን ነገር ዐውቀን በእዚያ ላይ የበለጠ እንዲያብብ መርዳት እና ማበረታታት፣ የጥንካሬና የተስፋ ስሜት በውስጡ እንዲመሰረት፣ ሌላውንም ነገር እንዲያሻሽል የሚረዳው ውስጣዊ ጥንካሬ በውስጡ እንዲፈጠር ይረዳል።

ልጅ፣ "ወንድምና እህቴ እንዲህ ናቸው ፤እኔ ግን እንዲህ አይደለሁም" ብሎ ራሱን ሲኮንን ካየነው፣ እንዲህ አይነት ጎጂ ምግባርን እንዲያቆም እናበረታታው። ጉድለቱን ብቻ ነጥሎ እያየ ራሱን መኰነኑ፣ ትርፉ የሚሆነው ተስፋ ማስቆረጥ እንደ ሆነ እናስታውሰው። ሁሉ ልጅ፣ የየራሱ ችሎታ እና ጥንካሬ እንዳለው፣ ማንም በቻለው መጠን ጠንክሮ ከሰራ እና የድል ቃል ከተናገረ ሊደርስ የሚገባው ቦታ እንደሚደርስ፣ የራሱን ውብ ነገር ይዞ እንደሚዘልቅ፣ ለልጃችን እናስረዳ።

## *3) ጠንክሮ መስራት ወሳኝ ነው*

ሁላችንም እንደምንስማማው ጠንክሮ መሥራት የግብ መድረሻ ዋነኛ መንገድ ነው። ልጆቻችን ጠንክሮ ለግብ መስራትን ካልተማሩ፣ የቱንም ያህል ትልቅ ነገር በውስጣቸው ቢኖር፣ ቀጭጮ ይቀራል። ለአላማቸው ተግቶ መሥራትን፣ ሰአታቸውን በአግባብ መጠቀምን፣ ተስፋ ሳይቆርጡ መሞከርን ካልተለማመዱ፣ ችሎታቸውና ተፈጥሮዋዊ ስጦታቸው ሁሉ እንዳልነበር ይሆናል።

የልጆችን የቀን ከቀን ልምምድ በዋነኝነት የሚቀርጹት፣ ጠንክሮ ለግብ የመስራት ባህል እንዲዋሀዳቸው መንገዱን የሚያመቻቹት፣ ወላጆች ናቸው። ወላጅ የሚወስነው ውሳኔ፣ ልጅ ጠንክሮ እንዲሰራ ወይም ትምህርትን ችላ እንዲል ትልቅ ድርሻን ያበረክታል። ተግቶ በመስራት ህግ ላይ የማያወላውል አቋም ከሌለን፣ ልጅም ይሳነፋል፤ የመካከለኛ ውጤት ተማሪም ሆኖም ይቀራል። ልጆቻችን ችሎታው፣ጉብዝናው እንዳላቸው፣ እንዲሁ ፈተናን እንደምንም ብለው ለማለፍ ብቻ ሳይሆን፣ ጠንክረው እንዲሰሩ እንዲያጠኑ እንደምንጠብቅባቸው እንንገራቸው።

***ልጆቻችን ለግብ ጠንክሮ የመስራት፣ የማጥናት ባህል እንዲዋሀዳቸው፣ ወላጅ ምን ሊያደርግ ይችላል?***

- ✓ ለቤት ሥራ፣ ለጥናት የተመደበ፣ የተወሰነ ሰአት መኖር አለበት። ለምሳሌ "ከዚህ ሰአት እስከ እዚህ የቤት ስራ የሚሰራበት፣ ጥናት የሚጠናበት ጊዜ ነው" ብለን ካወጣን፣ ያ የተመደበ ሰአት ሁሌ ለጥናትና የቤት ስራ ለመሥራት መሆን አለበት። እንደዚህ የተወሰነ የጥናት ጊዜ ሲኖራቸው፣ ልጆቻችን ሠዓትን በአግባብ መጠቀምን ይማራሉ። ጠንክረው እንዲሰሩ፣ ለወደፊትም በዕቅድ መስራትን እንዲለማመዱ ይረዳቸዋል።





- ✓ ሁልጊዜ አንድ አይነት የሆነ ህግ ይኑረን። ዛሬ አጥኑ ብለን ተቆጥተን ነገ ይጫወቱ ብለን ዝም ካልናቸው ልጆቻችን በዚህ ጉዳይ ላይ የማያወላውል ህግ እንደሌለን ይረዳሉ። እነርሱም ነገሮችን በቀላል መውሰድ ይጀምራሉ። ካላጠናችሁ እንዲ አይነት ቅጣት ይመጣል ብለን አንዴ ከወሰንን በኋላ፣ የማይለዋወጥ አንድ አይነት አቋም ይኑረን።
- ✓ በልጆቻችን የጥናት፣ የቤት ስራ ጊዜ ቴሌቭዥንን እናጥፋ፤ ወደ መጫወት የሚስቧቸውን ነገሮች ሁሉ ካጠገባቸው እናስወግድ። ለጥናት የተመቸ ቦታ እናዘጋጅላቸው። እንደዚህ ጸጥ ያለ ቦታ ሲቀመጡ፣ ሳይደናቀፉ ለማንበብና ሥራቸውን ለመሥራት ዕድል ያገኛሉ።
- ✓ ልጆቻችን ጥያቄ ሲጠይቁን ሁሉን በመመለስ ፈንታ፣ እንዲያስቡበት፣ ራሳቸው መልሱን እንዲያገኙ የሚረዳቸውን ምሪት እንስጣቸው።
- ✓ ልጆቻችን የሚያጠኑበት አካባቢ መዝገበ ቃላት፣ የሚያስፈልጋቸው ወረቀት፣ እርሳስ፣ እስክሪብቶ መኖሩን እናረጋግጥ።
- ✓ በልጅ ትምህርት ምጥቀት ላይ የሚያስተምሩ ብዙ ባለሙያዎች ለወላጆች ደጋግመው የሚያስገነዝቡት ነገር፣ ወላጆች ከልጆች አስተማሪዎች ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት መፍጠር ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ነው። ልጃችን አዲስ ክፍል ሲጀምር፣ ከአስተማሪ ጋር እንተዋወቅ፤ አንዳንድ ጊዜ ከልጃችን አስተማሪ ጋር እየተገናኘን ስለ ልጃችን የትምህርት ጉዳይም እንወያይ። ልጃችን የደከመበት ነገር ካለ፣ ለአስተማሪ "ልጄን ለመርዳት ምን ማድረግ እችላለሁ" ብለን እንጠይቅ። ትምህርት ቤቱ ልጃችንን ለመርዳት ያለውን ፕሮግራም እናጣራ።

- ✓ የቤተሰብና የመምህር ስብሰባ ላይም በተቻለ መጠን እንገኝ:: እንደዚህ በትምህርት ቤቱ ውስጥ መሳተፋችን፤ልጃችንን በምን በምን ልንረዳ እንደሚገባን ጠቃሚ ግንዛቤ እንዲኖረን ይረዳናል:: ከዚያም በላይ አስተማሪዎቹ፣ የልጃችን ትምህርት ጉዳይን ስራዬ ብለን እንደምንከታተል ሲረዱ፣ እነርሱም ችላ እንዳይሉ፣ ጠንክረው እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል::

- ✓ ልጃችን ከትምህርት ውጭ በሆነ እንቅስቃሴ ላይ እንድትሳተፍ እናበረታታ:: ሙዚቃ ሆነ ስፖርት፣ ስእል በመሳሰሉት ነገሮች ችሎታዋን በሚያጎለብቱ ነገሮች ውስጥ መሳተፏ በጣም አስፈላጊ ነው:: እንደዚህ ችሎታን በሚያጎለብቱ ከትምህርት ውጭ ያሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ልጃችን መሳተፏ በተለያየ መንገድ ይጠቅማታል:: ለግብ ጠንክሮ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ መስራትን እንድትማር ይረዳል:: በምትወደው፣ችሎታዋን በሚያጎለብት እንቅስቃሴ ላይ ስትሳተፍ፣ ትምህርቷ ላይም ለመጎበዝ እንድትበረታታ ዕገዛ ያደርግላታል:: ከዚያም በላይ ደግሞ፣ በተፈጥሮ ችሎታዋ እንድትመጥቅ፣ ከሌሎች ጋር አብሮ መስራትን፣ ጥምረትን፣ እንድታዳብር ይረዳታል:: እዚ ጋር፣ እነዚህ ከትምህርት ውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ ሰአታችንን ሁሉ አጣበው በሩጫ እንዳያስኖሩን ጥንቃቄ እንውሰድ:: ሚዛን ባለው፣ ለሌላም የቤተሰብ ትስስሮች ጊዜ በሚተውልን መንገድ በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ላይ ልጆቻችን እንዲሳተፉ ካደረግን ግን ለልምላሜያቸው በትልቁ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል::

ባጠቃላይ፣ ልጆቻችን፣ እንዲጎብዙ፣ ባላቸው አቅምና ችሎታ እንዲተጉ እናበረታታ:: ከላይ ያነሳነው፣ ታናሽ ከሆነ ጅማሬ ጀምሮ የአለም ታዋቂ ቀዶ ጥገና ሀኪም ለመሆን የበቃው ቤን ካርሰን (Ben Carson) የተባለው ሰው፣ እርሱና ወንድሙ ጠንክረው እንዲሰሩና እንዲበረቱ እናቱ ምን ያህል ትጠብቅባቸው እንደ ነበር ደጋግሞ ይገልጻል:: ባንድ ወቅት፣ ልጆቹ በትምህርት ቤት ዝቅተኛ ውጤት





ማምጣታቸውን ተመልክታ ይህች ቆራጥ እናቱ ቴሌቭዥኑን እንደዘጋች፣ ተግተው እንዲያጠኑ፣ በሳምንት ሁለት መጽሐፍ አንብበው እንዲነግሯት እንዳዘዘቻቸው ያወሳል:: በውስጣቸው ያስቀመጠችው ተግቶ የማጥናት ባህል ወደ ትልቅ ቦታ እንዳሸጋገረውም ደጋግሞ ያነሳል:: እኛም ይህንን ሁሌ ልብ እንበል:: ልጆቻችን ምንስ የተፈጥሮ ጉብዝና ቢኖራቸው፣ ተግቶ ማጥናትን ካልተማሩ ሊመጥቁ የሚችሉበት ቦታ እንደማይደርሱ ተረድተን ጠንክሮ ለአላማ ግብ መስራት ላይ የማያወላውል ህግ ይኑረን::

## *4) ማንበብ የዕውቀት ቁልፍ ነው*

መጻሕፍ፣ ልጆቻችን ውስጥ ያለውን ዘር ለማፍካት ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ተረድተን ልጆቻችን መጸሀፍ የማንበብ ልማድ እንዲኖራቸው እንጣር፤ መጽሐፍ እንግዛላቸው ቤታችን ሁሌ መጻሕፍት ይኑሩ:: እንዲ ዐይነት መጽሐፍ ካላነበብክ ወይም ካላነበብሽ ብለን ብዙም አናስጨንቃቸው:: ዋናው መጽሐፍ ማንበብ ይልመዱ፣ ይውደዱ እንጂ፣ የበለጠ ጥልቅ ነገሮች ውስጥ እየገቡ ይመጣሉ:: መጥፎ ለልጅ የማይስማማ ነገር እስከሌለበት ድረስ፣ እንደየፍላጎታቸው የሚወዱት አይነት መጽሐፍ እንዲያነቡ በመፍቀድ፣ የመጽሐፍ ፍቅራቸውን እናሳድግ::

መጽሐፍ ማንበብ የማይወድ ልጅ ካለን፣ያ ፍቅር ቀስ በቀስ በራሱ እንዲገባው ቦታ መክፈት እንጂ ብዙም ጫና አናድርግባቸው፤በጣም መጫኑ ጭራሽ እንዲጠሉ ሊያደርጋቸው ይችላልና:: ወላጅ ሲያነብ ሲያይ፣በንባብ ባህል ውስጥ ቤተሰብ ሲሳተፍ፣ ልጅም የማንበብ ፍቅሩ እንዲጨምር ያበረክታል:: ቤተሰብ፣ የአንባቢያን ቡድን ብለን የራሳችንን መመስረት፣ አንድ ጥሩ ዘዴ ነው:: አንድ የቤተሰብ አባል መጽሐፍ አንብቦ ከጨረሰ በኋላ፣ ወይም በቡድን አንድ መጽሐፍ ካነበብን በኋላ ቤተሰብ ተሰባስበን፣ ሻይ አዘጋጅተን ስላነበብነው መጽሐፍ መወያየት፣ ስላገኘንበት ቁምነገር ማካፈል የልጅ የማንበብ ፍቅርን ለመጨመር ትልቅ አስተዋጽኦ አለው::

## *5) የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ማስፋት*

በትምህርት ጠንክረው እንዲሰሩና የንባብ ልምድ እንዲያደርጉ መንገዱን ከማመቻቸት በተጨማሪ ልጆቻችንን እንዲመጥቁ የምናበረክትበት ሌላኛው መንገድ፣ የአስተሳሰብ አድማሳቸውን ማስፋት ነው:: ልጆቻችን ትላልቅ ነገር እንደ እውነት ሆኖ በውስጣቸው እንዲሳልባቸው፣ ከትላልቅ ነገር ጋር ከአሁኑ ማስተዋወቅ ጠቃሚ ነው:: ሙዚየም ቦታ ይዘናቸው መሄድ፣ መጻሕፍት ቤት መውሰድ፣ የተለያዩ የሳይንስ ግኝቶች ያሉባቸውን ቦታዎች ማሳየት አለብን። ኮሌጅ እንገባለን ብለን አብረናቸው እንገባ:: እንደ ግዴታ ነገር አድርገን ሳይሆን ቀስ በቀስ እያደረግን እድሜያቸው ከእነርሱ ከፍ ያለ፣ ኮሌጅ የገቡ የሚማሩ ልጆች ጋር እናስተዋውቃቸው:: ከእነርሱ ጋር እንዲያወሩና ጊዜ እንዲያሳልፉ እናድርግ::

እነርሱ፣ "ወደፊት እደርሳለሁ" ብለው የሚመኙት ግብ ላይ ከደረሱ ሰዎች ጋር እንዲገናኙ እናድርግ፤ "ይኸውልህ እነኚህ ሰዎች፣ልክ አንተ ልትሆን የምትፈልገው፣ አንቺ ልትደርሺበት የምትፈልጊው ቦታ ላይ የደረሱ ሰዎች ናቸው" እንበላቸው። ከዛም በተጨማሪ፣ ተስፋ ሳይቆርጡ ፣ ከባድ የሆነ የሕይወት ፈተናን ካሸነፉ በድል ከተወጡ ሰዎች ጋር እናገናኛቸው

በዓለም ትላልቅ ነገር ስለ ሠሩ ሰዎች እንንገራቸው:: የወደፊት አላማቸው ምን እንደሆነ፣ እነርሱ ለየት ያለ ችሎታና ክህሎት አለኝ የሚሉት በምን አንጻር እንደ ሆነ እንጠይቃቸው:: በአጠቃላይ በትላልቅ ሀሳብ ዘወትር እንክበባቸው፤ የሰው ልጅ የከበበው ነገር እውነቱ ይሆናልና::





## *6) እኛ የምንተልምላቸውን ብቻ አንይ*

ልጆቻችን እና የወደፊት ግባቸውን በተመለከተ፣ የእኛ የራሳችን በሆነ እቅድ፣ በምናስበው ነገር ልንቀርጻቸው እንዳንሞክር በጣም እንጠንቀቅ:: "ልጆቼ ለመምጠቅ ይህንና ያንን ማጥናት አለባቸው" ብለን አናስብ:: በተለይ እንደዚህ እንደ አሜሪካ ባለ፣ ለተለያየ ሥራ ምርጫና ሰፊ ማደጊያ አማራጭ ባለበት አገር፣ ለተለያዩ ፍላጎቶች እና የትምህርት ዐይነቶች ሰፊ ቦታ አለ:: ልጃችን ይበርታ፣ ጠንክሮ ይስራ እንጂ ለማደጊያ ሰፊ ቦታ አለ፤ የራሱ ወደ ሆነው ወደተጠራበት ትልቅ ቦታ ይደርሳል::

"ለእኔ ትልቅ መስሎ የታየኝ ነገር ለእነርሱም መሆን አለበት" በማለት፣ ልጆቻችንን አስገድደን ልናስገባቸው ከሞከርን ግን፣ መጥቀው የማይሄዱ ሰዎች እናደርጋቸዋለን:: "ያንን ዐቢይ ትምህርት ካላጠናችሁ፣ ይህንን ካልተማራችሁ፣" ብለን ቀንና ለሊት ስንጨቀጭቃቸው፣ በውስጣቸው ያለው ፍላጎት መነቃቃት እና ትልቅ እሳት ይጠፋል:: ለማጥናት ቢነሳሱ እንኳ፣ እኛን ለማስደሰት ብቻ በማስመሰል ማድረግ ይጀምራሉ:: እኛም እንደማናምንባቸው ይሰማቸዋል:: በኋላ ጊዜ አልፎ፣ በትልቅነት እድሜያቸው፣ ያንን እኛን ለማስደሰት ብለው ያጠኑትን ትምህርት ይዘው ሲኖሩ፣ በእኛ ሁሌ እንደተናደዱና እንደተማረሩብን ይዘልቃሉ:: "በዚያ ልባዊ ፍላጎት በነበረኝ ጥናት ብመረቅ ኖሮ ዛሬ የት እጀርስ ነበር፤ እንዴት ደስ የሚለኝን ስራ እሰራ ነበር" በማለት፣ ሁሌ በቁጭትና በምሬት ያስቡናል፤ በራሳቸው ሳይሆን የእኛ ህልም በሆነው ነገር ውስጥ ናቸውና። በተለያየ የጥናት መስክ ላይ ምክር፣ አስተያየት መስጠቱ ጥሩ ነው፤ ከዚያ በተረፈ ግን፣ ሰው የሚያብበው በራሱ ህልም ሲዋብ መሆኑን አስታውሰን እንዲህና እንዲያ ዐይነት ዛፍ ካልሆናችሁ በማለት ፈንታ፣ የራሳቸው ማንነት፣ ሥሩ ጠንካራ በሚሆንበት ጉዳይ ላይ እናተኩር::

## *የልጆቻችን ትምህርት ቤት*

ልጆቻችን ትምህርት የሚያገኙበት ተማሪ ቤት የትምህርት አሰጣጣቸውን ይወስናል፤ ስለዚህም ለምጥቀታቸው ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል:: ይህንን እውነት ተረድተን፣ በተቻለን መጠን የትምህርት አሰጣጥ ጥራቱ የተሻለ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ እንጣር:: እውነት ነው፤ ብዙዎቻችን፣ ልጆቻችንን የግል ትምህርት ቤት ለመላክ፣ አቅሙ ላይኖረን ይችላል፤ ስለዚህም ያለን ብቸኛ አማራጭ፣ በአካባቢያችን ያለ ትምህርት ቤት ልጆቻችንን ማስገባት ብቻ እንደ ሆነ ሊሰማን ይችላል:: ነገር ግን፣ ከዛ ያለፉ የተለያዩ ምርጫዎች አሉ:: መሰረታዊ የሆኑ እነዚህ ፕሮግራሞች በምንኖርበት አካባቢ ውስጥ እንዳሉ ማጥናትና ማጣራት ይገባል::

## ማጠቃለያ

የልጆች በትምህርት መምጠቅ ላይ፣ ወላጅ ትልቅ ቦታ እንዳለው ተረድተን፣ ከልጅነታቸው እንገንባቸው:: ጠንክሮ መሥራት፣ ትልቅ ነገር ማለምን፣ አደርገዋለሁ ብሎ ማመን፣ተስፋ አለመቁረጥ፤ በልጆቻችን ውስጥ እንዲቀረጽ ጠንክረን እንስራ፤ በራሳቸው በተጠሩበት ነገር አብበው ይወጣሉ::

**(የልጅዎን ትምህርት ቤት ምርጫ በማስመልከት ስላሉት የተለያዩ ፕሮግራሞች ለመገምገም፤ ከስር ይመልከቱ፤[7])**

---

[7] **የትምህርት ቤት ምርጫን አስመልክቶ ያሉ የተለያዩ ፕሮግራሞች**

Open enrollment፤ በዚህ ፕሮግራም ስር፣ ከመኖርያዎ አቅራቢያ ባለ ትምህርት ቤት አይወሰኑም። በእርስዎ ወረዳም ያሉ ሌሎች ትምህርት ቤቶች ሆኑ በሌሎች ወረዳዎች፤ ለልጅዎ ትምህርት ቤቶችን መምረጥ ይችላሉ።[7] (ስለዚ ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ ቢፈልጉ፣ኢንተርኔት ጉግል ውስጥ ገብተው open enrollment school ብለው በመፈለግ የበለጠ ገለጻ ያገኛሉ)

Charter school፤ እነዚህ በህዝብ የተመሰረቱ (የሚደገፉ) አንደኛ ደረጃ ፤ ሁለተኛ ደረጃና አጠቃላይ ትምህርት ቤቶች ናቸው። የህዝብ ትምህርት ቤት ቢሆኑም፣ ሌሎች የህዝብ ትምህርት ቤቶች በሚተዳደሩበት ህግ ሁሉ አይተዳደሩም። ብዙ ጊዜ ቻርተር ስኩልስ ልጆችን የሚቀበሉት በዕጣ መልክ ነው። ቻርተር ስኩልስ ክፍያ እንዲያስከፍሉ አየፈቀድላቸውም። አንዳንድ የቻርተር ትምህርት ቤቶች በተወሰኑ የትምህርተ መስኮች ብቻ ስርአተ ትምህርተ አላቸው። ለምሳሌ ስነ ጥበብ፣ ሂሳብ። ሌሎች ደግሞ፣ የተሻለና ከሌሎች የህዝብ ትምህርት ቤቶች በጠራ ሁኔታ ሁሉንም ትምህርት ይሰጣሉ።[7] በአካባቢዎ ያለ ቻርተር ስኩል ለማግኘት ቢፈልጉ (www.ederform.com) ብለው ይዩ Charterschoolcenter.org ብለው ቢገቡ ስለቻርተር ስኩል የበለጠ ገለጻ ማግኘት ይችላሉ።

Magnet schools፤ የህዝብ ትምህርት ቤት አካል ናቸው። ማግኔት ስኩል የተለየ ችሎታ ወይም ምርጫ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች የተዘጋጀ ፕሮግራም አለው። ብዙ ጊዜ ትምህርት አሰጣጣቸው ጥራት ባለው መልኩ ነው። ትምህርት ቤቱ አመልካቾችን የሚመርጥበት የራሱ መስፈርት አለው።[7] (ስለዚህ ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ ኢንተርኔት ገብተው magnet.edu ብለው ይመልከቱ የበለጠ እርዳታ ለማግኘት 202-824-0672 ይደውሉ)

Voucher፤ ወላጆች የህዝብን ድጎማ (ፓብሊክ ፈንድ) ተጠቅመው የመረጡት ትምህርት ቤት ልጆቻቸውን ለማስገባት የሚረዳቸው ሰርተፊኬት ነው። አሪዞና፣ ፍሎሪዳ፣ አሀዮ፣ አታዋ ዊስከንሰንና ዋሽንግተን ዲሲ የቫውቸር ፕሮግራም አላቸው።[7] ስለ ቫዎቸር ፕሮግራም የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ
Schoolchoices.org/voucher
www.allianceforschoolchoice.org

Alternative schools በትምህርት በጣም ዝቅ ያለ ውጤት እያመጡ ያሉና በመውደቅ አደጋ ውስጥ ላሉ ተማሪዎች የተሻለ አካባቢ ለመፍጠር የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች ናቸው (በኢንተርኔት የበለጠ ገለጻን ማግኘት ይችላሉ)

No Child left behind (NCLB) የሚለው ህግ ይህን ይመስላል፤ የልጅዎ ትምህርት ቤት ከፌደራል የተለየ ድጎማ የሚቀበል (title 1) ትምህርት ቤት ከሆነ እና ለ2 ተከታታይ አመታት የሚጠበቅበትን ግብ ካልመታ፣ በዚያው ወረዳ (district) ላይ ልጅዎን ወደ ሌላ ት/ቤት የማዛወር መብት አለዎት። የፌዴራል ድጎማ የዚህ አይነቱን ዝውውር ወጭ ይሸፍናል። ልጅዎ ከነበረበት ት/ቤት ለተሻለ ለውጥ እስከተዘዋወረ ድረስ የወረዳው ትምህርት ቤት ለልጅዎ መጓጓዣ ወደ አዲሱ ትምህርት ቤት ያቀርባል።

ከላይ እንዳየነው፣ የትምህርት ቤት ምርጫን በተመለከተ፣ የተለያዩ አማራጮች አሉ። ወደ ልጅዎ ትምህርት ቤት ሄደው፣ ስለእነዚህ ፕሮግራሞች መጠየቅ ይችላሉ። በምንኖርበት ወረዳ (ዲስትሪክት) ውስጥ ትምህርት ቤትን በተመለከተ፣ የቱ አማራጭ እንዳለ ለማወቅ መሞከር በጣም አስፈላጊ ምርጫ ነው። በርስዎ ወረዳ (district) ምን አይነት ፕሮግራም እንዳለ ለማወቅ፣ ወደ ወረዳዎ ቢሮ ደውለው ማወቅ ወይም ዌብ ሳይታቸው ውስጥ ገብተው መመልከት ይችላሉ። ሌላው፣ የምንችል ከሆነ ያለን አማራጭ፣ የተሻለ የትምህርት አሰጣጥ ያለበት ወረዳ መግባት (ሰፈራችንን መለወጥ ነው)። በአካባቢያችን ያሉ የግል ትምህርት ቤቶች፣ ለልጆቻችን ስኮላርሺፕ ሊሰጡ የሚችሉበት አማራጭ ካለም ሄዶ መጠየቅ ሌላ ጥሩ አማራጭ ነው። በአካባቢዎ ያሉትን ወላጆች መጠየቅና ከእነሱ እይታ እና ምርጫ አንጻር ሁኔታውን ለመረዳት መሞከርም ይጠቅማል።

# ምዕራፍ ሦስት

## የልጆች ራስን ችሎ መቆም

ልጆቻችንን ከልብ የምንወድ ከሆነ፣ ይህንን እናስታውስ። ልጅን መጥቀም ማለት፣ በራሳቸው ጠንክረው መቆም ወደሚችሉበት ዐቅም፣ ቀስ በቀስ መምራት እንጂ፣ በእኛ ላይ ተጣብቀው ወደሚቀሩበት ቦታ መምራት አይደለም።ልጆቻችንን ምናሳድግበት ጊዜ፣ ከእኛ ውጭ ለሚኖሩበት ዘመን ጠንክረው መቆም እንዲችሉ እያዘጋጀናቸው ያለበት ወቅት እንጂ፣ እኛ ላይ በሁሉ ተመርኳዥ እንዲሆኑ የምናደርግበት አይሁን። እንዲጠነክሩ ስንል በሥራም፣ በአስተሳሰብም እንደሆነ ልብ ልንል ይገባናል።

### 1. <u>ሥራን በመውደድ እራስን መቻል</u>

> "የቤተሰብ ጥናት ምርምር እንደሚያመለክተው፣ ከ3 ወይም ከ4 አመት እድሜያቸው ጀምሮ፣ ልጆች ቤት ውስጥ እንዲያግዙ፣ ስራ እንዲሰሩ ማበረታታችን፣ ለወደፊት ችሎታ ጥንካሬያቸውና ማንነታቸውን በጥሩ ሁኔታ ለመቅረጽ፣ትልቅ ተጽዕኖ አለው።"[8]

ከፍቅር የተነሣ ቢሆንም፣ የልጆቻችንን እራስን ችሎ የመቆም ሂደት የምንገታ፣ በጣም ብዙ ወላጆች አለን። ሰበቡ ፍቅር ቢሆንም፣ልጆቻችን ያለ እኛ ጣልቃ ገብነት አንዳችም ነገር ማድረግ የማይችሉ የልጅ ጡረተኞች እንዲሆኑ አድርገን እያሳደግን ያለን ብዙ ሰዎች አለን። ይህን የምናደርገው ልጆቻችንን የተንከባከብን ስለሚመስለን ነው።

---

[8] (www. parent hood.com) wolf, Liz





ከልጅነት እስከ ዕውቀት ሁሉን ነገር እኛ እናደርግላቸዋለን። እነርሱ በራሳቸው አንድ ነገር እንዲያድርጉ አንገፋቸውም፤ በቤት ውስጥ የሚሠራ ሥራ አንሰጣቸውም። "ይህን ነገር መሥራት አቃተኝ" ባሉ ቁጥር ሁሉ፣ "እሺ ልጄ" ብለን እኛ የእነርሱን ሥራ እንሰራላቸዋለን። አንዳንድ ወላጆች፣ ብንችል እርምጃቸውን እንኳ እኛ ብንራመድላቸው ደስ ይለናል። ከላይ እንዳነሳነው፣ እንደዚህ የምናደርገው ለልጆቻችን ካለን ውዴታ የተነሳ ነው። ነገር ግን፣ ለእኛ ከፍቅር የሆነው ነገር፣ ለእነርሱ ማሰናከያ ኬላ ይሆንባቸዋል። ሕይወትን፣ ሁሌ በእኛ እቅፍ ሥር ሊኖሩ አይችሉም። ብርድ ካለበት ከውጪ መውጣታቸው አይቀሬ ነው። በዚያን ጊዜ፣ እኛ በሌለንበት ስፍራ ብቻቸውን ሆነው የውጪን አየር ሲቀምሱ፣ በእኛ ክንፍ ሥር ተጠልለው ያደጉት ልጆች መቆም ያቅታቸዋል፤ ይሰባበራሉ።

ከልጅነታቸው ጀምሮ፣ በራሳቸው እንዲቆሙ፣ ጠንክረው መስራት እንዲማሩ፣በገንዘብ ላይ የኀላፊነት ስሜት እንዲሰማቸው፣ መንገዱ ቀስ በቀስ እየተጠረበላቸው ያደጉ ልጆች፣ ውጭ ሲወጡ ግር አይላቸውም (መያዣው መጨበጫው አይጠፋቸውም)። ቀስ በቀስ ውስጣቸው እንዲቀመጥ በተደረገው በራስ የመተማመን ችሎታ ተመርተው፣ ወላጅ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ሁሉ ጠንክረው መቆም ይችላሉ። የራሳቸውን ሕይወት ለመምራትና ለመቆጣጠር ማድረግ ያለባቸውን ያውቃሉ።

ፍቅር በሚል ሰበብ በእኛ ክንፍ ሥር ተከልለው ያደጉ ልጆች ግን፣ ኋላ የሕይወትን ብርድ በግላጭ ሲጋፈጡ፣ ክንፏ እንደተመታ ወፍ መሆናቸው የግድ ይሆናል። ከፍቅር የተነሳ ነው ብለን ያደረግነው ነገር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝንና፣ ልጆቻችንን ያጠፋል። ምእራብያውያን ከጥሩ ባህላቸው መካከል አንዱ፣ ልጆቻቸውን በራስ ቆሞ የማደግ ልምምድን ማስተማራቸው ነው። "ቆሻሻ አፌ ላይ አለ" ባሉ ቁጥር፣ ሄደው አይጠርጉላቸውም። "ከፍሪጅ ውስጥ ይህን እፈልጋለሁ" ባሉ ቁጥር፣ "እሺ ልጄ" ብለው ሄደው

አያመጡላቸውም:: እድሜያቸውን አቅማቸውን በተከተለ መልኩ፣ ከመጀመሪያው ጀምሮ ቀስ በቀስ፣ ራስን ችሎ የመቆም ባህልን ያስተምሯቸዋል:: በእነርሱ ዕድሜና ዐቅም የሚሰራ የቤት ሥራ ይሰጧቸዋል:: በራሳቸው ሊያደርጉ የሚችሉትን ነገር እንዲያደርጉ ዕድሉን ይሰጧቸዋል:: "እናትና አባቴ፣ እጄና እግሬ ሆነው፣ እኔ የምፈልገውን ሁሉ ያደርጉልኛል" ብለው እንዳያስቡ፣ ይልቁንም እራስን መቻል፣ በራስ መተማመንን በተግባር ያስተምሯቸዋል::

በሕይወት ዘመኑ፣ ሚኒስተር፣ ጸሐፊ፣ ለሌሎች መብት ተከራካሪና አስተማሪ ሆኖ፣ ብዙ ሰዎች የማይደርሱበት ግብ ደርሶና ስኬታማ ሆኖ ያለፈ ሬቨረንድ ሃሮልድ ዋይክ (Reverend Harold wilke) የተባለ ሰው ነበር:: ይህ ሰው የተወለደው ካለእጅ ነው:: እናቱ ልጇ የሚያጋጥመውን የህይወት ሳንካ ተረድታ፣ እንዴት ከልጅነቱ እንዳጎበዘችው ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር፤ "ልጄ አካለ ስንኩል ነው በሁሉ ልርዳው በማለት ፋንታ በራሴ መቆም መጠንከር እንዳለብኝ ተረድታ፣ በዛ መንገድ እንድራመድ ታበረታታኝ ነበር" ብሎ ይገልጻል:: የእናቱን አርቆ ማየት ሲገልጽ አንድ ምሳሌ ይሰጣል:: "የሁለት የሶስት አመት ልጅ ሆኜ አንድ ቀን፣ ካናቴራዬን ለማድረግ እየሞከርኩ (በአካለ ስንኩልነቴ ምክንያት) ከብዶኝ በጣም እፍጨረጨር ነበር:: እናቴ (እንደ ወላጅነቷ) እጇን ዘርግታ እንድትረዳኝ ውስጥዋ ቢያስጨንቃትና ቢገፋትም፣ ስሜቷን ተቆጣጥራ ካለችበት ቆማ ዝም ብላ ታየኝ ነበር:: የእናቴ ጓደኛ ይህን ሁኔታ አይታ፣ በንዴት አግርሞት፣ "አይዳ ለምን ልጅሽን አትረጅውም" አለቻት፤እናቴም *እየረዳሁት ነው ብላ መለሰችላት*" ብሎ ያነሳል::[9] እናት ገብቷት ነበር፤ልጇን መርዳት ማለት ልጇን ማጠንከር፣ ራሱን እንዲችል መንገዱን መጥረግ ማለት እንደ ሆነ ከወዲሁ ተገንዝባ ነበር:: ራሱን ችሎ፣ በራሱ ጠንክሮ

[9] Rigby Jill (2008) Raising unselfish children in a self absorbed world, Howard books.





መቆም የተማረው ልጇ፣ አንድም እጅ ሳይኖረው፣ ግን ሁለት እጅ ያላቸው ብዙ ሰዎች የማይደርሱበት ግብ ደርሶ፣ በሌሎችና በራሱ ሕይወት ትልቅ ለውጥ አምጥቶ አለፈ::

የአሜሪካ ፕሬዚደንት ባራክ ኦባማ ባለቤት የሆኑት ሚሼል ኦባማ፣ የልጆችን ራስን ችሎ ማደግ በማስመልከት፣ ይህ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር፤ ልጆችዎ ዋይት ሀውስ ውስጥ እያሉ የፈለጉት ሁሉ እየተደረገላቸው በምቾት ነጻነት እየኖሩ ነወይ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት መልስ ይህን ይመስላል፤ "እንዲህ አይነት፣ "ሌላው እኔን ያገልግለኝ" የሚል፣ የንግስትነት አስተሳሰብና ስሜት እንዲወርሳቸው ፍጹም አልፈቅድም፤ እኔ የማስበው አሁን እዚህ ዋይት ሀውስ ስላላቸው የምቾት ሕይወትና ጊዜ አይደለም፤ ስለወደፊት ኑሮዋቸው እንጂ፤ እንደማንም ልጅ፣ ወደፊት ለሚጠብቃቸው የሕይወት ጫና፣ እነሱንም ማዘጋጀት አለብን፤ ያ ማለት የራሳቸውን አልጋ ማንጠፍ፣ ቤት ውስጥ ማገዝ፣ ስነስርአት መያዝ፣ ለሌላ ሰው አክብሮት መኖር፣ ይጠበቅባቸዋል፤ ይህ ጊዜያዊ ቤታቸው ነው በውስጣቸው የተመሰረተው የሀላፊነት ስሜት፣ ቀና አስተሳሰብ እና አረማመድ ግን፣ ሁሌም አብሯቸው የሚቆይ ነው::" የሚለውን ምላሽ ሰጥተዋል::[10]

ወላጅ እንዲህ ራቅ አድርጎ አይቶ፣ ራሳቸውን እንዲችሉ ተደርገው ያደጉ ልጆች፣ እጅግ በሚያስደንቅ መጠን ልቀው ይገኛሉ፤ ሁሉን አድርገን ያሳደግናቸው የእኛ ልጆች ግን፣ ሁዋላ ውጭ ሲወጡ፣ ግራ ገብቷቸው ራቁታቸውን እንዳሉ ያህል ተሰምቷቸው፣ ሊቆሙ ግድ ይሆናል::

እኛ ሁሉን እያደረግን ስናሳድጋቸው፣ ልጆቻችን እኔነት ውስጣቸውን ሊወርሳቸው ትልቅ እድል አለው:: የቱንም ያህል በፍቅር ያደጉ ልጆች ቢሆኑ፣ በተግባር ሌላን ማገልገል

[10] December 2011- Jan 2012; Readers Digest; Michelle Obama Interview

አልተማሩምና፣ እኔ ሁሌ መገልገል አለብኝ የሚል እምነት የሚመራቸው ሰዎች ይሆናሉ። ወደፊት ሲያድጉ፣ እኔ እኔ የሚሉ፣ሁሌ መገልገል የሚፈልጉ፣ ከሌላ ሰው ጋር አብሮ ተስማምቶ የመኖር ችግር የሚኖራቸው ሰዎች እንዲሆኑ አስተዋጽኦ ያደርጋል። እቤት ውስጥ ቤተሰብን መርዳት፣ ወንድምንና እህትን ማገልገል ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ካስተማርናቸው ግን ራሳቸውን የቻሉ፣ከሌላም ጋር ተስማምተው መኖር የሚችሉ ሰዎች ይሆናሉ።

ሁሌ ልንንከባከባቸው እንደማንችል ተረድተን፣ ፍቅር ማለት ልጆቻችንን ማጠንከር፣ ለብርዱ ማዘጋጀት መሆኑን ተገንዝበን፣ ጠንካሮች የሚያደርጋቸውንና፣ በሁለት እግራቸው ለመቆም የሚያስችላቸውን ምርጫ እንምረጥ። ከልጅነታቸው ጀምሮ ቤት ውስጥ ኃላፊነት እንስጣቸው። ከመኝታ ቤት ጽዳት ጀምሮ በራሳቸው መሥራት እንዲለምዱ እናበረታታ። ቤት ውስጥም እንዲያግዙ እናድርግ።

ይህን ባህል ቤት ውስጥ ስንጀምር፣ መጀመርያ ላይ ከልጆች ዘንድ እንቢታ ሊመጣ ይችላል። ይሁንና፣ ይህ ጉዳይ ለልጆቻችን አስፈላጊ መሆኑን ተረድተን፣ በቃላችን እንቁም። "ይህ ቤት የእናታችሁና የአባታችሁ ቤት ብቻ አይደለም። የእናንተም ቤት ነው፣ ስለዚህ ሁላችንም የድርሻችንን ማበርከት አለብን" ብለን፣ የማይረሱትን ትምህርት እየደጋገምን እናስተምር። ልጆቻችንም፣ ባልነው እንደማናወላውል ሲረዱ፣ መሥራትን ልምዳቸው ያደርጋሉ።

በተለይ በሕጻንነት ዕድሜያቸው፣ ልጆቻችንን ለማነሣሣት ስንፈልግ፣ በትእዛዝ ወይም በጩኸት ይህን አድርጉ በማለት ፈንታ፣ እነርሱን በሚስብ መልክ ብናደርገው የበለጠ ጥሩ ውጤት እናገኛለን። ለምሳሌ የተለያዩ የስራ ክፍፍሎች ጽፈን፣ "ዕጣ እናወጣለን፤ ዕጣውን ሁላችሁም ታወጣላችሁ፤ ሁሉም ሰው የደረሰውን የሥራ ክፍል ያከናውናል ብለን ልጆች በዚህ ሂደት





ውስጥ እንዲሳተፉ ብናደርግ፣ ልጆችም ተነቃቅተው ይህ ልምድ ውስጥ እንዲገቡ ያበረታታቸዋል።

ከተለመደው የቤት ሥራ በላይም፣ ሠርተው ገንዘብ ሊያገኙበት የሚችሉት ዕድልም እንክፈትላቸው። አዎ፤ ልጆች እፈልጋለሁ ያሉትን ነገር ሁሉ በመግዛት ፈንታ ለሚፈልጉት ዕቃ መሥራት እንደሚችሉ ነግረን፣ ከተለመደው የኀላፊነት ሥራ ሌላ፣ ለገንዘባቸው መሥራት የሚፈልጉትን እንጠይቅ። ሠርተው ማግኘት እንደሚችሉም ሲረዱ፣ የስራን ጥቅም እያወቁ ይመጣሉ። እንደዚህ እያልን፣ ቀስ በቀስ የበለጠ ኀላፊነትን እየሰጠን ራሳቸውን የበለጠ ወደሚችሉበት አቅጣጫ እንምራቸው።

## *በአስተሳሰብ ራስን መቻል*

ልጆቻችን ራሳቸውን ችለው፣ ጠንክረው እንዲቆሙ የምናደርገው በድርጊታቸው ብቻ አይደለም። ልጆቻችን በአስተሳሰባቸውም ራሳቸውን የቻሉ፣አስተሳሰባቸው የበሰለና የጎለበተ እንዲሆን አድርገን ልናሳድጋቸው ያስፈልጋል። ለኋላቸውም የሚቆይላቸው አስታዋሽ መሪ የሚሆናቸው፣ የማመዛዘን ችሎታና የግንዛቤ ስሜት እንዲጠልቅባቸው ጠንክረን እንሥራ እንጂ፣ ራሳቸውን ችለው ማሰብ ያልተማሩ፣ እኛን ለማስደሰት ብቻ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ያወቁ "እንደ ሮቦት" የሆኑ ልጆች አናሳድግ። ልጆቻችን አርቀው እንዲያስቡ፣ ክፉና ደጉን ማመዛዘን እንዲችሉ፣ጠንክረን እንሥራ እንጂ፣ ወላጅን ለጊዜው ለማስደሰት ብቻ መሯሯጥ የለመዱ የልጅ ምርኮኛ አድርገን አናሳድግ፤ በግንዛቤ ደረጃ እኛ ላይ ተመርኳዥ የሆኑ ልጆች እንኳን ለሌላ ለራሳቸውም አይሆኑምና።

*ልጆቻችን በአስተሳሰብ ግንዛቤያቸው ራሳቸውን እንዳይችሉ፣ አርቀው ማየት እንዳይማሩ እክል የምንፈጥርባቸው እንዴት ነው?*

"ይህን አድርግ፤ ይህን መንገድ ተከተል" እያልን እናዛቸዋለን። "እኔ ለእናንተ የሚበጃችሁን አውቃለሁ፤ ስለዚህ ይህን ምርጫ ምረጡ"

እንላቸዋለን። ግን ከዛ አልፈን፣ ያ ነገር ለሕይወታቸው ያለውን ጥቅም ወይም ጉዳት፣ ጊዜ ወስደን አናስረዳቸውም:: የአንድን ነገር ጥቅም ወይ ጉዳት እንዲያስቡበት ቦታና ዕድልን አንሰጣቸውም ::

ልጆች እኛ ፊት ሲሆኑ ብቻ ሁሉን ነገር ለይምሰል በማድረግ፣ ማስመሰልን ብቻ እንዲማሩ ማድረግ፣ የማንኛውም ወላጅ ግብ አይደለም፤እኛ በሌለንበትም የእውነት ለወደፊት ሕይወታቸው እንዲያስቡ፣ የሚጠቅማቸውንና የሚጎዳቸውን ነገሮች በእውነት እንዲረዱ፣ ምን ይበጀኛል ብለው እንዲያመዛዝኑ እንጂ::

"እኔ አጥኚ ስላልሁ አጥኚ፣ እኔ ስራ ስላልኩ ይህን ሥራ" እያልን ልንመራቸው ስንሞክር፣ ልጆቻችንን ያስተማርናቸው ሊመስለን ይችላል፤እውነታው ግን፣ የሚያደርጉትን ነገር የሚያደርጉት፣ እኛን ለማስደሰት ወይ እኛን ስለፈሩ ብቻ ነው፤ ያስተማርናቸው እኛን ማስደሰት ብቻ ነውና:: እኔ ስላልኩ ብቻ አድርጉ የሚለውን መርሆ ስንከተል፣ ልጆች ይህን ያን ማድረግ ያለባቸው፣ ለራሳቸው መሆኑን ሳይረዱት ይቀራል:: የሚያጠኑት ለቤተሰቦቻቸው ብለው ይመስላቸዋል:: ኮሌጅ የሚሄዱት፣ ሥራ የሚይዙት ወላጆቻቸውን ለማስደሰት ብቻ ይመስላቸዋል:: የሚያደርጉትን ሁሉ እኛን ለማስደሰት ወይም እኛን ዝም ለማስባል ብቻ ያደርጉታል::

ያቺ ልጅ በልጅነቷ፣ እኛን ስለፈራች አድርጊ የተባለችውን የምታደርግ ከሆነና፣ በኋላ ግን እኛ ሳንኖር አብሯት የሚቆየው ግንዛቤ በውስጧ ከሌለ ምን ፋይዳ ይኖረዋል? የተማረችው ብቸኛ ነገር እኛ ፊት መታዘዝ እንጂ፣ ጉዳዩን እውነት ይሁን ውሸት ካልተረዳች፣ ያ ምን ይጠቅማታል? ልጃችን እኛን ስለ ፈራ ብቻ ማጥናት ቢለማመድ፣ ኋላ ብቻውን ኮሌጅ ሲገባ የሚያቋቁመው የሚያጠነክረው፣ የሚገፋው የኃላፊነት ስሜት አብሮት ካልገባ ኪሳራ አይደለምን?

ልጆቻችንን ኋላ አጠንክሮ የሚያቆማቸው የእኛ ትእዛዝ አይደለም፤ በውስጣቸው እንዲተከል የተፈቀደለት የእውቀት፣ የሀላፊነት፣ የግንዛቤ ስሜት እንጂ፤ ያ ነው መሪ ሆኖ ከጥፋት የሚከልላቸው::





አድገው ከጓደኞቻቸው ይህንና ያንን ሲሰሙ፣ "እንዲህና እንዲያ አድርጉ" ሲባሉ አጠንክሮ የሚያቆማቸው፣ በጥሩ መንገድ የሚመራቸው፣ የእኛ ማስፈራራት አይደለም፤ በውስጣቸው ያለው የግንዛቤ ስሜት ምጥቀት እንጂ::

በሕይወት ተሞክሯችን አስፈላጊው ዕውቀት ገብቶናል:: ልጆቻችንም ይህንን ዕውቀት እንዲረዱ እንፈልጋለን:: ያ ጥሩ ሆኖ ሳለ፣ ዋናው ቁም ነገሩ ግን፣ ይህንን ዕውቀት ወደ እነርሱ የምናሻግረው፣ ግንዛቤ ሆኖ እንዲጠልቃቸው የምናደርገው እንዴት ነው፣ የሚለው መሰረታዊው ነጥብ ነው::

ግንዛቤን በሰው አእምሮ ውስጥ በግድ ልንወሽቃት አንችልም:: በሰው አእምሮ ውስጥ ግንዛቤ የሚተከለው፣ አንድን ነገር ማድረግ እና አለማድረግ የሚያስከትለውን መዘዝ በውል ሲመለከትና ልዩነቱን ሲያውቅ ብቻ ነው። አልፎ በመሄድ፣ እኛ በሌለንበት ጊዜ ሁሉ ወደ ጥሩ መንገድ የሚወስዳቸውን የጠለቀ ግንዛቤ፣ በውስጣቸው እንዲመሰረት፣ ታዛዥነታቸው ብቻ ሳይሆን ግንዛቤያቸውም እንዲጎለብት ማድረግ ይጠበቅብናል::

ምንነቱ ሳይነገር በግዳጅና በአፈና የሚደረግ ነገር፣ ምንስ ጥሩ ቢሆን መምረር እንደሚጀምር ተረድተን ልጆቻችን እውነተኛ ግንዛቤ በሚሰጣቸው መልክ እናነጋግራቸው፤የአንድን ነገር ስሕተት እና ትክክልነት ስንነግራቸው፣ እነርሱን ሊመስጥ በሚችል መንገድ እናቅርብላቸው:: "በትምህርትሽ ከወደቅሽ በሕይወት ልታሳኪ የምትፈልጊውን ነገር ልታጪ ትችያለሽ፣ ጠንክረህ ካልሠራህ ሌላው ካንተ በልጦ የፈለገው ቦታ ሲደርስ፣ አንተ ወደኋላ ትቀራለህ:: ጠንክረህ ስትሠራ፣ ያለምከው ቦታ ደርሰህ ደስ ትሰኛለህ፤ በርትተሽ ለግብሽ ስትሰሪ ሕይወትሽን ደስ በሚልሽ መንገድ ለመምራት እድል ታገኛለሽ፤ ነጻ ሆነሽ ህልምሽን ለማሳካት እድል ታገኛለሽ::" እያልን ልጆቻችንን እናስረዳቸው፤ ጥያቄያቸውን በትዕግሥት እናዳምጥ። ትክክለኛ መልስም እንፈልግለት:: ግንዛቤ ከፍርሐት የበለጠ ኃይል እንዳለው ሁሌ እናስታውስ፤ የጠለቀ

ዕውቀት እንዲኖራቸው ስንል፣ ጥያቄያቸውን ሰለቸኝ ሳንል እናዳምጣቸው፤ እናነጋግራቸው፤ እናበረታታቸው።

ኀላፊነትን የምናስተምርበት ሌላኛው ዋነኛው መንገድ፣ ሰው ሁሌ የሥራውን (ጥሩም ሆነ መጥፎ)፣ ውጤት እንደሚያገኝ ካሁኑ በግልጽ በማሳየት ነው። እነሱ ሊገባቸው በሚችል መንገድ የምርጫቸው ውጤት ምን እንደሚያስከትል ከህጻንነት ጀምሮ እንዲረዱ፣ ተግተን መሥራት አለብን። ብዙ ጊዜ የምርጫቸው ውጤት ምን ዐይነት ጥቅም ሆነ ጉዳት እንዳመጣ በግልጽ እንዲያዩ ዕድል አንሰጣቸውም። ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ለምሳሌ ልጅ ሊወስድ የሚገባውን ኀላፊነት ሳይወስድ ሲቀር፣ ተቆጥተን እዛው ነገሩን እናልፈዋለን፣ ወይም እኛው ተረክበን እናደርግላቸዋለን። በዚያ ፈንታ፣ ምርጫቸው ምን መዘዝ እንዳስከተለ በግልጽ እንዲረዱት ቦታ መክፈት ያስፈልጋል፤የሥራቸውን ውጤት በግልጽ ሲያዩት ጥቅሙን ወይም ጉዳቱን ይገነዘቡታልና።

ለምሳሌ ልጃችንን ቁጭ አድርገን፣ "ኀላፊነት ወስደህ መኝታ ቤትህን በራስህ ማጽዳት የምትችልበት ዕድሜ ላይ ደርሰሀል። ካሁን በኋላ ውል እንገባለን፤ ኀላፊነት ወስደህ መኝታ ቤትህን የምታጸዳ ከሆነ የምትወደውን ቴሌቭዥን ፕሮግራም እንድታይ ይፈቀድልሀል፤ ካላጸዳህ ግን፣ ያው አታይም" ብለን እንንገር። ምርጫውን ለእነርሱ እንተውላቸው፤ አሰላስለው ራሳቸው እንዲወስኑ እናድርግ። ላላጸዳም ካሉ ወይም ህጉን ባግባቡ ካልጠበቁ፣ ረጋ ብለን "ምርጫህ ይህ ከሆነ በተነጋገርነው መሠረት የምርጫህ ውጤት ይሄ ነው፤ያንን የቴሌቭዥን ፕሮግራም አታይም"፣ ብለን ምርጫው ያስከተለውን ውጤት እናሳይ። ልጅ ተናዶ "እንዴ፣ ይሄማ ልክ አይደለም፤ፕሮግራሜን ማየት እፈልጋለሁ ብሎ ከጮኸ ወይም የሙጥኝ ካለ፣ ይህ አጋጣሚ ትምህርትን ማስተማሪያ ጥሩ ሰአት መሆኑን ተረድተን፣ ምላሻችንን እንስጥ። ስሜታዊ ሳንሆን፣ ይህ የሕይወት ገጽታ እንደ ሆነ በግልጽ ለልጃችን ማስረዳት አለብን። "የዓለም አሠራር እንደዚህ ነው። እኔ ለምሳሌ ካልሠራሁ አይከፈለኝም። ሁሉ ሰው ለሚሠራው ሥራ ውጤት አለው። በዚህ ነገር ውስጥ የለሁበትም፤ ምርጫውን ላንተ ነው የሰጠሁት፤ አንተ ደግሞ አለማጽዳትን መርጠሀል፣ ስለዚህ ውጤቱ ደግሞ ይኸው፤"

"በትምህርትሽ ጥሩ እየሠራሽ አይደለም እና ይኸው ውጤቱ " ብለን መጽናት አለብን። እንደዚህ ስናደርግ፣ ልጅ "ይህን ማድረጌ ወይም አለማድረጌ ጉዳቱና ጥቅሙ ምንድን ነው?"፣ የሚለው በጥልቅ እየገባው/እየገባት ይመጣል። "አባቴና እናቴ ስለሚቆጡኝ" በሚለው ውስን እውቀት ፈንታ፣ እውነተኛ ግንዛቤ ይሰርጽባቸዋል።

በዚህ ሂደት ውስጥ በደንብ መገንዘብ የሚኖርብን ትልቁ ቁም ነገር፣ በአቋማችንና በቃላችን ጽኑና ታማኝ መሆንን ነው። ሐሳባችንን ለውጠን ልጅ ማየት በሚገባው ውጤት ፈንታ የፈለገውን መስጠት፣ የገዛ ልጃችንን መጉዳት ነው። "ስንፍናዬ፣ግዴለሽነቴ መጥፎ ውጤት የለውም፤ ስለ ጮህኩ ወይም ስላስመሰልኩ ከሀላፊነት ልርቅ እችላለሁ"ብሎ እንዲደመድም እየዳረግነው ነውና

ከላይኛው ጋር ተያይዞ፣ አስፈላጊ በሆነ መልኩ ሌላ ማድረግ ያለብን ዋና ነገር ይህ ነው። ልጆች የጥሩ ስራቸውንም ውጤት እንዲያዩ ቦታ መክፈት አለብን። አንዲት ልጅ የተነገራትን ነገር አመዛዝና በትምህርቷ ብታሻሽል፣ "ግብሽ ላይ ለመድረስ ለፍተሻል፤ ለጥሩ ሥራ ደግሞ ጥሩ ውጤት አለው፤ ልክ እንደ ተናገርኩት ያ ቃል የገባሁልሽን ነገር ታገኛለሽ"፣ ብለን የሚገባትን እንስጥ። ሀላፊነት ወስደው ለወሰዱት ጥሩ እርምጃ፣ መጠኑ ቢያንስ እንኳ መሸለም፣ ማሞገስን አንርሳ። እንደዚያ ስናደርግ፣ ምርጫቸው ትክክል እንደሆነ እያስተማርናቸው፣ እንዲሁም የበለጠ እንዲራመዱ እያበረታታናቸው ነውና።

ልጆቻችን ከሕፃንነታቸው ጀምሮ፣ ለራሳችው ማሰብ የሚጀምሩበትን ትናንሽ ዕድል እንክፈትላቸው። "ስለዚህ ነገር ምን ማድረግ ትፈልጊያለሽ? ስለዚያ ነገር ምን ማድረግ ትፈልጋለህ?"፣ እያልን ለእድሜያቸው በተገባ መጠን፣ የራሳቸውን ምርጫ እንዲያደርጉ ዕድል እንስጣቸው። ለምሳሌ የአራት ዓመትን ልጅ፣ መጫወቻህን እዚህ ቦታ አስቀምጥ በማለት ፈንታ፣"መጫወቻህን



ልጅን እንዴት ላሳድግ? በምዕራብ አገሮች

የት ልታስቀምጣት ትፈልጋለህ?" እንበል። የሆነ ነገር ማጠራቀም የምትፈልግ ልጅ ካለችን፣ የልጅ ሥራ ነው ከማለት ይልቅ፣ ኀበዝ በርቺ እንበል። ነገሩ ከዕቃው ሳይሆን ኀላፊነትን መውሰድ ከመማሯ ነውና። "ይህን ጠብቅልኝ፤ይህን ነገር እስቲ ያዥልኝ፤ ይህንን ነገር ባንተ ኀላፊነት ሥር ትቼዋለሁ፤ ለዚህ ልደት በአል ይህን ክፍል እንዴት እንደምናሳምረው አንቺ ኀላፊነት ወስደሽ ዕቅድን አውጭ"፣ እያልን የራሳቸውን ትናንሽ ኀላፊነት እንስጣቸው። እኛም፣ አውቀንም ቢሆን እንኳ፣ ጥያቄ እንጠይቃቸው። እንዲማሩት ስለምንፈልገው ነገር፣ እንደ ጥያቄ አድርገን እንጠይቃቸው። "ስለዚህ ነገር ምን ትመክሪኛለሽ"? እንበላቸው። ለእኛ ጥሩ መልስ ለመስጠት ሲያሰላስሉ ለራሳቸው እየተማሩ ይመጣሉ።

በትናንሽ ገንዘብ ላይ ኀላፊነት እንስጣቸው። ለምሳሌ "2 ብር በየሳምንቱ እሰጥሻለሁ፤ ያንን አጠራቅመሽ የፈለግሽውን መጫወቻ መግዛት ትችያለሽ፤ ወይንም "ይህን፣ ያንን ቤት ውስጥ ከሠራህ ይህን ያህል ደሞዝ ታገኛለህ፤ በዚያ ገንዘብ ያንን የፈለከውን እቃ መግዛት ትችላለህ" እንበላቸው። ይሄ ለገንዘብ ጠንክሮ መስራትን ያስተምራቸዋል። ገንዘብ እንደፈለጉት እንደማይገኝ ከማስተማሩም በላይ፣ ገንዘብን በብልሀት አወጣጥን ያስተምራቸዋል።

ልጆቻችን በራሳቸው መንገድ እንዲራመዱ በሚፈልጉበት ጊዜ ፍርሐት አይሰማን። "እኔ ባልኩት ብቻ ሂድ" የተባለ ልጅ፣ የኀላፊነት ስሜት በውስጡ አያድግም። ራሱን ችሎ ማሰብን የተማረ ልጅ ግን ለወደፊትም በራሱ ጸንቶ መቆምን ይማራል። "እዚህ ቦታማ አትሄድም፤ እንደዚማ አታደርጊም" ብለን፣ በስጋት ከሁሉም ነገር ከልለን ለማሳደግ በመሞከር ፈንታ፣ ቀስ በቀስ እንደ ዕድሜያቸው መጠን፣ በራስ ለመቆሚያው ጊዜ እያዘጋጀናቸው ይሁን። ያ የምንሰጣቸው ፈቃድ ጓደኛ ቤት እንዲሄዱ መፍቀድ ይሆናል፤ወይም ይህን ያን እንዲያደርጉ መፍቀድ ይሆናል። ለእኛ እውነቱን መናገር፣ ቃላቸውን መጠበቅ እስከተማሩ ድረስ፣ በነጻነት አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርጉ እንፍቀድላቸው። እዚህ ጋር፣ ልጆቻችን ላድርግ ያሉትን ሁሉን እንዲሁ እሺ እንበል ለማለት





አይደለም። እኛ በራሳችን ማጣራት ያለብን ነገር ሊኖር ይችላል። የጓደኛቸውን ቤተሰብ መተዋወቅ፣ የት እንደሚሄዱ ማጣራት ሊኖርብን ይችላል። ያ እንዳለ ሆኖ፣ የማይጎዳቸው መጥፎ ያልሆነ ነገር እስከ ሆነ ድረስ፣ ለልጆቻችን በሕይወታቸው ኀላፊነት መስጠትን፣ በራሳቸው እንዲቆሙ መንገዱን መክፈትን እንጀምር። እንዲህና እንዲያ እያልን የኀላፊነት ስሜትን ማበረታታታችን፤

1. ልጆቻችን፣ በእነርሱ ዕውቀትና የማመዛዘን ችሎታ፣ እኛ እንደምንተማመን ያሳያቸዋል።
2. እኔ ኀላፊነት መውሰድ የምችል ሰው ነኝ ብለው በራሳቸው እንዲተማመኑና ካሁኑ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል።
3. ለወደፊቱ ያዘጋጃቸዋል። ኋላ ሕይወትን ለብቻቸው ሲመሯት ከአሁኑ የለመዱት ኀላፊነት የመውሰድ ባህል፣አብሯቸው ይቆያል።

በቤታቸው አንዲት ነጻነት አግኝተው የማያውቁት፣ ለራሳቸው ማሰብ አንዲት እድል ያላገኙት ልጆች ኮሌጅ ገብተው፣ "አሁን በቃ፣ እናቴ አባቴ አያዩኝም" ብለው "ታስሮ እንደተለቀቀ ጥጃ" ሆነው ሁሉን ልቀላቀል ሲሉ፣ እነዚህ ከልጅነታቸው ጀምሮ ለራስ ማሰብ፣ ኀላፊነት መውሰድን ቀስ በቀስ እንዲማሩ ሆነው ያደጉት ልጆቻችን፣ ምንም ነገር አዲስ አይሆንባቸውም። "እኔ ከድሮውም እናትና አባቴ ለራሴ ማሰብ እንድችል አድርገው ነው ያሳደጉኝ" ብለው፣ በዛው በኀላፊነት ስሜት ይቀጥላሉ። በውስጣቸው ተደላድሎ የተቀመጠው የግንዛቤ ስሜት፣ አሻጋሪ መርከብ፣ መሪ መስታወት ይሆንላቸዋል።

# የሕይወት ተሞክሮ

## ልጆቻችንና ማንነታቸው

በውጭ አገር የተወለዱ ወይ የሚያድጉ ልጆችን በተመለከተ፤ አብዛኞች ልጆች፣ ንቅንቅ በማይል ስፍራ መካከል ሆነው፣ ተጨንቀው የሚገኙ መሆናቸውን አያለሁ፤ ይህም ማለት እነርሱ የሚኖሩት፣ በተለያዩት የወላጆቻቸው ዓለምና በጓደኞቻቸው ዓለም መካከል ነው። ይህ በበኩሉ በነርሱ ላይ የሚያስከትለው ውዥብርነትን ብቻ ሳይሆን የባይተዋርነትን ስሜት ጭምር ነው። ይህ ውጥረት የሚታየው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ልጆች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ እንደነሱው ወላጆቻቸው ከሌላ አገር በመጡ በሌሎችም ወጣቶች ነው።

ብዙ ወላጆች ለልጆቻችን ትላልቅ አላማና ህልም አለን፤ ያ እንዳለ ሆኖም፣ ልጆቻችን ሊደርሱበት የሚገባቸው ትልቅ ቦታ እንዲደርሱ፣ ወላጅ ሊይዝ የሚገባውን ቦታ መረዳት አለብን። ያ ምን ማለት ነው? ብዙ ሰዎች፣ ለልጆቻችን የምንወስነውን ውሳኔ ስንወስን፣ ነገሮችን የምንገመግመው ከራሳችን የግል እይታ ነው። "እኔ ልጅ ሆኜ ይህን እመኝ ነበር ስለዚህ እነሱም የሚመኙት ይህንን መሆን አለበት። እኔ ልጅ ሆኜ በእንደዚህ አይነት ችግር ውስጥ አልፌ ነበር፤ ስለዚህም ለልጆቼ ዋነኛ የሚያስፈልጋቸው ይህ ነው። እኔ ይህንን ነገር አያስፈልገኝም፤ ለእነሱም አያስፈልጋቸውም፤" ወዘተ። ባጠቃላይ አስበነውም ሆነ ሳናስበው፣ የራሳችንን ህይወት በምንመለከትበት መንገድ የእነሱንም ህይወት እንወስናለን። እንደዛ በማድረግ ፋንታ ግን፣ እነሱ የሚያስቡት የሚፈልጉት ምንድነው፣ 'በዚህ ጊዜ ለህይወታቸው ምንድነው የሚጠቅማቸው ምንድነው?' ብለን ቀስ ብለን ብናጠና፣ ለእነሱ የሚጠቅማቸው ነገር ላይ ሀይላችንን ልናወጣ እንችላለን።





የእኛ ግላዊ ምኞት፣ የልጆቻችንም አድርገን፣ መንገዳቸው ላይ አጋጅ ግድብ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን። ለምሳሌ፣ ኮሌጅ ስትገቡ ይህንን ብቻ አጥኑ፣ ወደ ጥሩ ቦታ ለመድረስ መራመጃ አቅጣጫው ይህ ብቻ ነው እያልን እኛ በምናስበው አቅጣጫ ብቻ ልንመራቸው እንዳንሞክር እንጠንቀቅ። ይህ የሚያመጣው አደጋ የልጆቻችንን የተፈጥሮ ምጥቀት ያደመድማል፤ ራሳቸውን ችለው ማሰብን እንዳይለምዱ፣ በተፈጥሮ ችሎታቸው አብበው ደምቀው እንዳይወጡ ያደርጋቸዋል።

የእኛ ግላዊ ምርጫ፣ ልክ የልጆቻችንም እንደሆነ አድርገን ከሚጠቅማቸው ነገር እንዳንከላከላቸው ጥንቃቄን እንውሰድ፤ ለምሳሌ፣ ከትምህርት ውጭ ባለው የእንቅስቃሴ ፕሮግራም (extra curricular activity) ለልጆች ብዙ ጥቅም አለው። ልጆቻችን በዚህ ስፖርት ውስጥ ልግባ ወይ ይህንን አክቲቪቲ ላድርግ ሲሉን፣ እኛ ስለማናውቀው ወይ ስላለመድነው ብቻ "አይይ ምንም አያደርግልህም" እንላቸዋለን። እነሱ ያንን ስፖርት ሲጫወቱ፣ ወይ በትምህርት ቤት ያንን አርት ሲያሳዩ፣ ብዙ ወላጆች ሄደን አንመለከትም። እነዚህ አክቲቪቲዎች፣ ምንነታቸው ብዙም ባይረዳን እንኳ በዚህ ባህል ውስጥ ለሚያድጉት ለልጆቻን ምጥቀት አስፈላጊ እንደሆነ ተረድተን፣ የማናውቀው ከሆነ እንኳ ብንጠይቃቸው፣ ወይ አብረናቸው ብንለማመድ ልጆቻችንን ከማበረታታቱም በላይ ያለንን ትስስር በትልቁ ይጨምረዋል። ሌሎቻችን ደግሞ፣ በመጀመሪያ ላይ ስምምነታችንን ቢንገልጽም ልጃችን መሀል ላይ ሲደናቀፍ፣ ተስፋ ሲቆርጥ፣ ከዚያም ለመውጣት ሲወስን፣ ብዙ ጊዜ ውሳኔውን ያለማመንታት፣ እሺ ብለን እንቀበላለን። ልጆች ተስፋ አለመቁረጥን እንዲማሩ በምሳሌነት ማስተማር ያለበት ወላጅ ነው። ልጅ ትንሽ በደከመው ወይ ባስጠላው ቁጥር በቃኝ ብሎ ማቆም፣ ልጁ እንዲጎለምስ፣ ጠንክሮም እንዲጓዝ አይረዳውም።

ወላጅ ሊረሳው የሚችለው፣ ሌላው ልጅን በትልቁ የሚጠቅም ነገር፣ በበጎ አድራጎት ስራ ውስጥ መሳተፋቸው ነው። እኔ

አለመድኩም ወይ አላደኩበትም በማለት ፋንታ፣ ከልጆቻችን ጋር አብረን የበጎ አድራጎት ስራ ላይ ብንሳተፍ ከማንም በላይ የራሳችኑ ልጆች ህይወት እናሳብባለን:: አብሮ መስራትን፣ መሪነትን፣ ለሌላ ማሰብን እና የመሳሰሉትን ያስተምራቸዋል:: ከዚያም በላይ፣ ጠንካራ ያደርጋቸዋል ኮሌጅ ለመግባት ሲያመልክቱም በዚህ ውስጥ ተሳትፌያለሁ ብለው መጻፋቸው ለልጆቻችን ሬዚሜ በትልቁ ይረዳል::

የወላጅ ግላዊ ፍርሀት በምናደርገው ላይ ተፈናጥቆ፣ ልጆቻችንን እንዳይጎዳ ልንጠነቀቅ ይገባል. አገራችን ስናድግ በችግር ውስጥ አልፈን የመጣን ብዙ ሰዎች ልጆቼን ከችግር መከላከል እፈልጋለሁ ብለን እናስባለን፤እንደዛ ማሰባችን ጥሩም ትክክልም ነው:: ከልክ ያለፈ ፍርሀትን ይዘን፣ በተሳሳተ ጎዳና እንዳናመራ ግን መጠንቀቅም አለብን:: ልጅን ከችግር መከላከል ማለት ልጆቻችንን ማሞላቀቅ፣ ሀላፊነት ሳያስተምሩ ማሳደግ መሆን የለበትም:: ለምሳሌ የኮሌጅ ተማሪ የሆኑ፣ እረፍት ጊዜ ሲመጣ የማይሰሩ ብዙ ልጆች አሉ:: ልጆች ናቸው ብለን እየተውናቸው ብዙ ልጆች ራስን ስለመቻል፣ ገንዘብን በቅጡ ስለመያዝ ሳይማሩ ይቀራሉ:: መስራት፣ ራሳቸውን መቻል ባለባቸው ጊዜ የሌላቸውን ገንዘብ እያጠፉ ጨዋታ ላይ ብቻ ማተኮር ልጆቻችንን በትልቁ ጎድቶ ሲያስቀር ይችላል::

ይህ ባህል የሚሰጣቸውን ብቻ ሳይሆን የእኛ ባህል የሚሰጣቸውን ጥሩ ነገርም ማጤን አለብን:: ልጆች ምንጫቸውን ተረድተው ማደጋቸው ለህይወታቸው ምን ያህል ዋጋ እንደሚያመጣ ብዙ ጥናቶች መዝግበዋል::ማህበራዊ ኑሮ፣ ከሌላ ጋር መካፈል፣ ትልቅ ሰው ማክበር፣ ባህልን ማወቅ ለልጆቻችን መማራቸው በዚህ ባህል ውስጥ ሲያድጉ በጣም ይጠቅማቸዋል:: ቤተሰብን ማክበር፣ እንግዳን ማክበር፣ ስነስርአት መያዝ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ማስተማር አለብን::ስራዬ ብለን ቋንቋ ባህላቸውን እንዲያውቁ መርዳት አለብን:: ካልተጠነቀቅን፣ በራሳችኑ መነጽር አይተን፣





አያስፈልጋቸውም ብለን ወስነን፣ ይህን ለእነሱ ከፍተኛ ግምት ያለውን ጉዳይ ልንነሳቸው እንችላለን፤ የራሳቸው የሆነውን የቤተሰባቸውን ቋንቋ ታሪክ ልጆቻችንን ሳናስተምር የማሳደግ አደጋ ውስጥ ልንወድቅ እንችላለን:: አንዳንዶቻችን ደግሞ የቤተሰባቸውን ቋንቋ ለመናገር መሞከራቸው ከእንግሊዘኛው ጋ ያምታታባቸዋል ብለን አስበን በጣም ከሚጠቅማቸው ነገር እንነሳቸዋለን:: ወላጆች ማስተማር ባለብን ሰአት ስራዬ ብለን ስለማንነታቸው አላስተማርናቸውምና እነሱም ሲያድጉ በዛው መንገድ ይቀጥላሉ:: የማንነታቸውን ክፍል የሆነውን ይህንን ቅርሳቸውን ሳናስተምር ካሳደግናቸው ባዶ ይቀራሉና ጠንክረን የሚጠቅማቸውን ነገር እንስጥ::

ልጆቻችን የሚያድጉት ከእኛ በተለየ ጊዜ፣ እንደሆነና የራሳቸው ብዙ ጫና እንዳለባቸው ተረድተን በግልጽ ልናናግራቸው ልንመክራቸው ይገባል:: ከእነሱ ቦታ ሆነን፣ ሁኔታዎችን ለመረዳት ልንጥር ይገባል:: በውጪ ያለባቸውን ግፊት ሳንረዳ፣ በግልጽ ሳናናግራቸው ፣ በደፈናው፣ እንዲህ አታድርግ እንዲህ አታጥፋ የሚለው ላይ ከማተኮር እንቆጠብ::

ባጠቃላይ ሁሉን ነገር በራሳችኑ መነጽር በመገምገም ፋንታ፣ እኛ በፈጠርነው አለም ውስጥ ልጆቻችን እንዲገቡልን ለመሳብ ከመሞከር ፋንታ፣ እነሱ ያሉበትን ሁኔታ አይተን ተረድተን ለልጆቼ ምን ማበርከት እችላለሁ፣ እንዲመጥቁ በምን ልረዳ እችላለሁ ብለን ብናይ በብዙ ሁኔታ ልንረዳቸው እንችላለን::

# ምዕራፍ አራት

## ፍሬያማነት በልጆች ሕይወት

ልጆቻችንን በተመለከተ፣ ፍሬያማነትን በአንድ በኩል ብቻ ከማየት እንቆጠብ። ምጥቀትን ስንለካ፣ ልጆቻችን በትምህርት መጎበዛቸውን፣ ጥሩ ውጤት ማምጣታቸውን ብቻ አናስብ። በትምህርት መጎበዝ አንድ አስፈላጊ የሆነ ምጥቀት ቢሆንም፣ ከትምህርት ቤት ውጤት ያለፉ፣ የሰው ልጅ ሊመጥቅባቸው የሚገባባቸው በጣም አስፈላጊ የሆኑ የሕይወት ክፍሎች አሉ።

ቀዳማይ የሕይወት ዐላማቸው፣ መብላት፣ መጠጣትና መተኛት የሆነ ልጆች ማሳደግ እንችላለን፤ ወይም ነገሮችን በጥልቅ የሚያስቡ፣ ራቅ ላለ ነገር የሚያነጣጥሩ ልጆችን ልናሳድግ እንችላለን። "ብዙኃንን የሚረዳ ጠቃሚ የሆነ ነገር አተረፉ" ተብለው የሚነሡ ልጆችን ልናሳድግ እንችላለን፤ ወይም "የ200 ብሩ ጫማ 150 ሲሆን እንዴት ነው የምገዛው" እያሉ ማሰላሰል፣ የሕይወት ዋነኛ አንቀሳቃሽ አላማቸው የሆነ የነገን ትላልቅ ሰዎች ልናሳድግ እንችላለን።

የሕይወት ዋነኛ ምሳሌያቸው፣ በቴሌቭዥን የሚያዩት ተዋናይ፣ የሆነ ልጆች ልናሳድግ እንችላለን፤ ወይም ከተብረቀረቀ ስእል አለፍ አድርገው የሚያዩ ልጆችን ልናፈራ እንችላለን። ዋነኛ ምኞታቸው፣ ጓደኛ ያደረገውን ሁሉ ለማድረግ በመጣጣር ላይ የተወሰነ ልጆችን ማሳደግ እንችላለን፤ ወይም ቆም ብለው በራሳቸው ማሰብን የማይፈሩ፣ በብዙ ዛፎች መሀል፣ ለየት ብለው ፈክተው የወጡ ልጆችን ማሳደግ እንችላለን።

አንድ ነገር ይህንን ውጤት በትልቁ ይወስነዋል። የልጆቻችንን ሥነ ምግባርና አእምሮ ለመቅረጽ ትልቅ አስተዋጽኦ ባለን በልጅነታቸው





ጊዜ፣ ልጆቻችንን ለምን ዐይነት ነገር እያጋለጥናቸው ነው? የሚለው የእነሱን የወደፊት አቅጣጫ ይወስናል። ሰው ማንነቱ እንደ ወፍ ዘራሽ ተክል፣ በአውላላ ሜዳ ላይ ዝም ብሎ አይበቅልም። የሰው ማንነቱ የሚቀረጸው፣ በሚያየው፣ በሚሰማውና በሚቀርብለት ነገር ነው። ምንስ ዐይነት ትልቅ ነገር በልጅ ውስጥ ቢኖር፣ ያለው ዕምቅ ኀይል፣ በትክክለኛ አቅጣጫ ካልተመራና ካልተገራ ወደ ታሰበለት ዐላማ ሊደርስ አይችልም።

እስቲ ራሳችንን እንጠይቅ፤ የምንፈልገው ነገር ምንድነው? ምን ዐይነት ትውልድ ነው ማፍራት የምንፈልገው? አዲስ ልብስ ለብሰው ፎቶ ተነስተው "አሜሪካ ኖርሁ" ብለው አርጅተው የሚሞቱ ልጆችን ነው ማሳደግ የምንፈልገው፣ ወይስ ከዚህ የላቀ ዐላማ አለን? ወይስ እንደ ከዋክብት ደምቀው የሚኖሩ፣ ምጡቅ አእምሮ ያላቸው ልጆች ማሳደግ እንፈልጋለን? በሰው አገር እንዲህ ከለፋን አይቀር፣ ፈክቶ ለሚያብብ፣ ፍንትው ብሎ ለሚበራ ነገር እንልፋ። ያለንን ሁሉ ከሰጠን አይቀር፣ ትክክለኛ ፍሬ የሚያፈሩ ልጆች በመቅረጽ ሂደት ላይ እንሰማራ። በቤታችን ያለው ያ ልጅ፣ትውልድን የሚመራ ልጅ ሊሆን ይችላል። ዛሬ ጎንበስ ብለን ወደ ታች የምናያት ያቺ ትንሿ ልጃችን፣ እስካሁን መድኀኒት ያልተገኘለትን በሽታ መድኀኒት ለማግኘት፣ በውስጧ ራእይ የተሰነቀባት ልጅ ትሆናለች፤ የነገን ትልቅ ሰው በቤታችን እያሳደግን መሆኑን ልብ ልንለው ይገባል።

ዋናውና ትልቁ ነጥብ፣ የልጆቻችንን አእምሮ መጠበቅ አለብን። በጠበበ ነገር ተከቦ ካደገ፣ በውስጡ ያለው ዘር የሚያስፈልገውን ውሀና ምግብ ካላገኘ፣ ያ ዘር ፍሬ መሆን ይሳነዋል፤ ተወሽቆ ወደ ውስጥ ሰምጦ ይቀራል። ምንም ያህል ለትልቅ ነገር የታሰበ ቢሆን፣ እንዳልነበር ይሆናል። ልጆቼ ምን አይነት ሰዎች እንዲሆኑ እፈልጋለሁ ብለን፣ ቆም ብለን እናስብ። ለእነርሱ የምንመኘውን ማንነት በጥራት ካየን በኋላ፣ እንደዚያ አይነት ሰዎች እንዲሆኑ የሚረዳቸውን ዘር በትጋት በውስጣቸው መትከሉ ላይ እንትጋ።

በዚህ ሂደት ውስጥ አንድ ነጥብ ልብ እንበል:: በሌላ አገር ባህል ውስጥ ስንኖር፣ ያ ባህል የሚሰጠውን ነገር በሙሉ ሳንመርጥ እንዲሁ ለልጆቻችን ከመስጠት እንቆጠብ:: "ትምህርት ቤት ያሉት ጓደኞቻቸው ይህን ያደርጋሉ፤ የዚህ ባህል ልጆችም እንዲህ ያደርጋሉ" ብለን አስበን ብቻ፣ ለልጆቻችንም ሁሉን አንፍቀድ:: ሳንለይ ሁሉን አቅርበንላቸው ካሳደግናቸው፣ ውጤቱ የሚሆነው አንድ ነው:: ለየት አድርገው ማሰብን ያልተማሩ የባህሉን ውላጆች እናተርፋለን:: የተለያዩ አስተማሪዎች፣ በልጅ አስተዳደግ ላይ ጥናት ያደረጉ ሰዎች፣ አንድ ደጋግመው የሚያነሱት ነጥብ አለ:: ያም ነጥብ፣ በዚህ ባህል ውስጥ ለልጆች ተስማሚ ያልሆነ፣ ልጆችን የሚጎዳ ብዙ ዘር እንዳለ ነው :: "የአሜሪካ ልጆች ናቸው፤ እንደ አሜሪካ ልጆች መኖር አለባቸው" ብለን፣ ሁሉን በገፍ በማቅረብ ፈንታ "ይህ ነገር ለልጆቼ ልምላሜን ያበረክታል ወይስ ያጠወልጋቸዋል? ብለን አርቀን እንመርምር:: ይህ የባህል ክፍል ልጆቼን አጥብቦ ያስቀራቸዋል? ወይስ ወደ ሰፋ ነገር ይወስዳቸዋል" ብለን ቆም ብለን እናስብ::

## *1) <u>የቴሌቪዥን ተጽእኖ</u>*

> "ልጆች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጨርሰው እስኪመረቁ፤ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያጠፉት ጊዜ፣ በአማካይ 11 ሺህ ሰአታት ይሆናል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ ቴሌቭዥን በማየት የሚያጠፉበት ጊዜ ደግሞ 15 ሺህ ሰአታት ይሆናል። ቴሌቭዥን ልጆችን በማስተማር ደረጃ ከአስተማሪም የበለጠ ትልቅ ተጽእኖ አለው ማለት ይችላል።"[11]

ቴሌቪዥን የልጆቻችንን አእምሮ ለመቅረጽ ትልቅ ኀይል ያለው ነገር ነው:: ብዙ ጊዜ ደግሞ በመጥፎ መንገድ ለመምራትም የሚጫወተው ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም::

[11] Murray J.P (1997) <u>Media violence and youth</u>; children in a violent society J. Osofsky (Ed),New York , Guilfor Press





> "ልጆች ብዙውን ሰአታቸውን ቴሌቪዥን በማየት ሲያጠፉ፣ ለወደፊት ማህበራዊ ህይወት እድገታቸው ጎጅ የሆኑ፣ጥል /ድብድብ/ በብዛት ከማየት ባሻገር፣ ገንዘባቸውን ያለአግባብ እንዲያወጡ የሚገፏቸው የቴሌቭዥን ማስታወቂያዎችንም በብዛት የማየት እድል አላቸው።"[12]

ልጆቻችንን በቴሌቪዥን ፊት ለፊት ለረጅም ጊዜ የምንተዋቸው ከሆነ፣ ጠባብነትንና በአንድ መንገድ ብቻ ማሰብን እንኩ እያልናቸው መሆኑን እንገንዘብ:: ይህ ብዙ ስለ ልጅ አስተዳደግ የሚያስተምሩ አስተማሪዎች ደጋግመው ለወላጆች የሚያስተምሩት ሐቅ ነው:: ብዙ ጊዜ ቴሌቪዥን፣ የገሐዱ ዓለም እውነት የማይንጸባረቅበት የራሱን አለም ያቀርባል:: የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ ሰውን መመሰጥና እዛው ጎልቶ ማስቀመጥ ዓላማቸው ስለሆነ፣ ጊዜና ስሜትን የሚሰልቡ፣ ከእውነት የራቁ ህልማዊ ድራማዎችን በየጊዜው ያቀርባሉ:: ከዚያ በተጨማሪ፣ በየደቂቃው የሚጮኸው የቴሌቪዥን ማስተዋወቂያ፣ የሕይወት ዋና ትርጉም ዕቃ፣ ልብስ፣ እንሥት... ወዘተ እንደ ሆነ የሚገልጽ መልእክት ያስተላልፋል:: በተለይ ልጆቻችን ዐደግ እያሉ ሲመጡ፣ አንዳችም እርባና የሌላቸው መልእክቶችን በየቀኑ ከቴሌቪዥን ይሰማሉ::

የልጆቻችንን ሥነ ምግባርና አእምሮ የሚቀርጹት የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ከሆኑ፣ በአደጋ ላይ መሆናችንን ልብ ልናደርገው ይገባል:: ልጆቻችንን በሥነምግባርና በአእምሮ የሚያሳድጉልን የቴሌቪዥን ተዋናይ ከሆኑ፣ የጠባብነት መንገድን እንዲወስዱ መንገዱ እየተመቻቸላቸው እንደሆነ፣ ልናስታውስ ይገባል:: መሪ፣ መሪ ነው:: ያ መሪ የቴሌቪዥን ሳጥን ቢሆንም እንኳ፣ በቤታችን መሪ እንዲሆን ተፈቅዶለታልና፤ ልጆቻችንን እየመራልን ይመጣል:: የሕይወት ዋነኛ አላማ፣ ያቺ ተዋናይ ለምሳ ምን እንደበላች ማጣራት መሆኑን እየመሰጣቸው ይመጣል:: ለየት ላለ ዐላማ

[12] Smith A Charles (1999) <u>The encyclopedia of parenting theory and research</u>

ተፈጥሮ የነበረው የልጆቻችን አእምሮ፣ ቀስ በቀስ እየተለወጠና በጠባብ ነገር እየተሞላ ይመጣል::

ልጆች ከቴሌቪዥን ጋር ተፋጠው መዋላቸው፣ አንድ ለአንድ ከሰው ጋር ያላቸውን ትስስርና ንግግር እንዳያዳብሩ ያደርጋቸዋል:: እንግዳ ሲመጣ ቁጭ ብለው ከእርሱ/ እርሷ ጋ መጫወት ይጠላሉ:: እነርሱ አፍጥጠው ማየት የሚፈልጉት ያቺን የለመዷትን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ነው፤ሱስ ሆናባቸዋለችና:: በሰው ውስጥ ሕይወት የሚኖረው ከሌላ ጋር ሲተሳሰር፣ ፍቅርንና ትዝታን ከሚያጣጥሙ ሕያዋን ከሆኑ ሰዎች ጋር ሲጫወትና ሲያወራ ነው፤ ይህ የተፈጥሮ ሕግ ነው:: ሰው ሕያዋን ከሆኑ ሰዎች ጋር መጫወት ትቶ፣ ሕይወት የሌለበትን ሳጥን ዘወትር መመልከቱ፣ ያፈዘዋል፤በብዙ መልክ የሰውን ልጅ የሚያዳብሩ ንግግሮችና ትዝታዎች፣ እንዳይኖሩት ያደርጋል::

የቴሌቪዥን ፕሮግራም ሁሉ መጥፎ አይደለም:: የሚያዝናኑና የሚያስተምሩ ጥሩ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች መኖራቸው እሙን ነው:: ነገር ግን ቀን ተሌት፣ ቴሌቪዥን የልጃችን ጓደኛ እንዲሆን መፍቀድ፣ ከትርፉ ኪሳራው ይበረታል፤ ከማዝናናት አልፎ ጉዳትንም ያስከትላል። የልጆቻችንን የቴሌቭዥን አጠቃቀም፣ በጤነኛ መልኩ እንዲሆን ምን ማድረግ እንችላለን?

1. ልጅ ለዕድሜው ተስማሚ የሆነ ፕሮግራም ያስፈልገዋል:: ቴሌቪዥኑ ሲከፈት፣ልጆቻችን የሚያዩትን ፕሮግራም ምን ይዘት እንዳለው በአንክሮ እንከታተል:: ፍትወት፣ተቀነባብሮ የቀረበ የእርስ በርስ ድብድብ፣ መገዳደል...ወዘተ በቴሌቪዥን ፕሮግራም ውስጥ በብዛት የሚቀርቡት ናቸው:: እኛ ራሳችን ለማየት ብለን፣ ልጅ ሊያየው የማይገባውን ፊልም መክፈት፣ ለልጅ ብልግናን እንካ እንደ ማለት ነው፤ የልጅ አእምሮው ነገሮችን ሳያገናዝብ ሁሉን ነገር ለመቅሰብ የተዘጋጀ ነውና::





> "በህጻናት፣ትምህርት ቤት እድሜ ባሉ ልጆች፣ እና ኮሌጅ ተማሪዎች ላይ የተደረጉ የምርምር ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በቴሌቭዥን ጥል ድብድብን ደጋግሞ ማየት፣ ልጆችን ቁጡና ለጥል የተጋለጡ የማድረግ ትልቅ እድል አለው። የወደፊቱንም ሕይወታቸውን ሊቀርጽ አመለካከትና አስተያየታቸውን ሊለውጥ ትልቅ ሀይል አለው።"[13]

ልጆቻችን የሚያዩዋቸውን የካርቱን ፊልሞች ይዘት፣ ምን እንደሆነ እናጣራ:: እኛ ካላወቅን ስለ ፕሮግራሙ ይዘት ሌላ ሰውን እንጠይቅ:: ድሮ በቴሌቪዥን የሚቀርቡ የካርቱን ፊልሞች፣ ለልጆች ብቻ የሚዘጋጁ ነበሩ:: አሁን ግን፣ ልጅ ሊሰማው የማይገባው የዐመጽና ፍትወት ነገር ያለባቸው፣ ነገር ግን "አስቂኝ" ተብለው የሚጠሩ ብዙ ካርቱን ፊልሞች አሉ:: በቴሌቪዥንም ሆነ ተከራይተው ሊያዩት የሚገባውን ፊልም የመምረጡ፣ እና ያንን ህግ የማስጠበቁ ስራ፣ የልጆቻችን ሳይሆን የእኛ ስራ እንደሆነ ልብ ልንል ይገባል:: <u>የቴሌቭዥን ሾው፣ ፊልም፣ መጻህፍና ቪዲዮ ጌምን በተመለከተ፣ ለልጆች ተገቢ ስለሆኑ እና ስላልሆኑት ጥሩ ግንዛቤ ለማግኘት ከስር ያለውን ድረገጽ (ዌብ ሳይት) ይመልከቱ</u>[14]

[13] Huston, A. C., Donnerstein, E., Fairchild, H., Fashbach, N. D., Katz, P. A., Murray, J. P., Rubinstein, E. A., Wilcox, B. L., Zuckerman, D., (1992). <u>Big world, small screen; The role of television in American Society.</u> Lincoln, NE: University of Nebraska.

[14] Commonsensemedia.org ወላጆች ሊያዩት የሚገባ በጣም ጥሩ ዌብ ሳይት ነው Reviews and advice የሚለውን ብንጫን ስለተለያዩ በቴሌቭዥን ስለሚታዩ (shows), ፊልሞች, ቪዲዮ ጌም፣ መጻህፎች ለልጆቻችን (እንደየእድሜያቸው) ተገቢ ይሁኑ አይሁኑ በግልጽ ያሳየናል::

2. "ግልግል ነው" በሚል፣ ልጆቻችንን ለረጅም ጊዜ፣ በቴሌቪዥን ፊት መተውን እናቁም:: እንደ ፕሮግራሙ ይዘት ሁሉ፣ የሰአቱ እርዝመትም፣ ተጽእኖ እንዳለው ተረድተን፣ እርምጃ እንውሰድ:: ቴሌቪዥን ለተወሰነ ጊዜ የሚከፈት መዝናኛና መማርያ እንጂ ቋሚ ጓደኛ እንዳይደለ ለልጆቻችን ነግረን፣ ያለ አንዳች ማቅማማት ቴሌቪዥኑን እናጥፋ::

3. በፋንታው፤ልጆቻችን ሊያደርጉዋቸው የሚችሉዋቸው ሌሎች ነገሮች እናቅርብላቸው እርስ በርስ እንዲጫወቱ እናበረታ። ልጆቻችን መጽሐፍ እንዲያነቡ እናበረታታ። አብረን የቤተሰብ ጊዜ እናሳልፍ። የፈጠራ ችሎታቸው እንዲያድግ፣ በተፈጥሮዋቸው የሚመጥቁበት፣ ስዕል፣ ጽሕፈት፣ ፒያኖ፣ መገጣጠም ስፖርት ላይ እንዲያተኩሩ እናበረታታ። አገር ቤት ላሉ ወዳጅ ዘመዶች ደብዳቤ እናጽፋቸው። መነቃቂያ የሚሆናቸው ነገር አዘጋጅተን ቤት ውስጥ እንዲያግዙን እናድርግ።ደጋግመን በህጋችን ከቆምን ልጆች ይለምዳሉ። "ቴሌቪዥን ካልተከፈተ ሞቼ እገኛለሁ" ብለው መቁነጥነጥ ያቆማሉ፤በቤት ውስጥ በፈልጉ ጊዜ ሁሉ የማይከፈትመሆኑን ስለሚያውቁ፣ የራሳቸውን፣ የሚያደርጉት ነገር ይፈጥራሉ።

የቴሌቪዥን አጠቃቀምን መቀየስ ብቻ ሳይሆን፣ ልጆቻችን ውስን አስተሳሰብ፣ ጠማማ አካሄድ እንዳይኖራቸው ይረዳል ብለን የምናስበውን ነገር አብረናቸው እንወያይ:: ሥራዬ ብለን ስለተለያዩ ጉዳዮች እየተወያየን የምናሳልፈው ጊዜ፣ ለየት ባለ መንገድ እንዲያስቡ ይረዳቸዋልና:: ለምሳሌ "ይህች ተዋናዪት የምትከበረው ለምን ይመስልሻል? እንደ እነርሱ ያልሆነ ሰው ከእነርሱ የሚያንስ ይመስልሻል ወይ?" ብለን እንጠይቃቸው። እንዲያስቡም ቦታ እንክፈት፤ "ጎበዝ ወይ ጀግና ማለት ቴሌቭዥን ላይ ወጥቶ የሚሰራ ሰው ነወይ" ብለን እንጠይቃቸው፤ እንዲያስቡበት ቦታ እንስጥ፤እንወያይ:: ባጠቃላይ፣ ከጠበበው ስእል ወጣ አድርጎ የሚያሳያቸውን የተለያየ ሀሳብ እናቅርብላቸው:: ስለ አገር ቤት፣





አስተዳደጋችን፣ ስለ ኅብረተሰቡ አኗኗር እናውራቸው:: ዓለም ውስጥ ስላሉ የተለያዩ ጉዳዮች አንሥተን እንወያይ:: ሰዎች የሚከራከሩባቸውን የተለያዩ ርእስ ጉዳዮች እንንገራቸው። "ስለዚህ ነገር ምን ታስባላችሁ?" ብለን እንዲያስቡበት ዕድል እንስጣቸው:: ስለተለያዩ ነገሮች ማወቃቸውና ስለ እነዚህ ነገሮች መነጋገራቸው፣ በአንድ ጎን ያዘመመና የተሳሳተ አካሄድ እንዳይኖራቸው ይረዳል::

## *የኮምፒዩተር አጠቃቀም*

ሌላው ልጆችን ወደ መጥፎ መንገድ የመሳብ ሀይል ያለው መሳርያ፣ ኮምፒዩተር ነው:: ኮምፒዩተር ልጆችን የሚጠቅም ብዙ ነገር ያበረክታል:: ልጆች ስለ አዲስ ነገር ለመማር እንዲችሉ፣ የሚፈልጉትን ለመጻፍ፣ ከሌሎች ጋ ለመገናኘት እንዲችሉ ይረዳቸዋል:: ኮምፒዩተር ብዙ ጥቅም አለው፤ ግን በዛውም መጠን ጉዳት ሊኖረው ይችላል:: ልጆች የፈለጉትን ይዩ ብለን ኮምፒዩተር ፊት የምንለቃቸው ከሆነ፣ ለእድሜያቸው ተስማሚ ያልሆኑ፣ጭራሽ ሊያዩ የማይገባቸው ምስሎችን ያቀርብላቸዋል:: እነዚህ ምስሎች የልጆቻችንን አእምሮ ለመቅረጽ፣ ልጆቻችንን ወደ መጥፎ አቅጣጫ ለመሳብ ትልቅ ሀይል አላቸው፤ ለአደጋም የተጋለጡ ያደርጋቸዋል::

> "ካለወሰን ኢንተርኔት ውስጥ እንዲገባ የተፈቀደለት ልጅ፣ ፍትወትን በግልጽ የሚያሳዩ ሳይቶችን በቀላሉ የማግኘት እድሉ በጣም ከፍተኛ ነው::"[15]
> "በዚህ ጉዳይ ላይ በተደረገ ጥናት፣ 70 % የሚሆኑ ልጆች፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ ፖርኖግራፊ (ፍትወት) ያለበት ሳይትን ተመልክተዋል።"[16]
> "ልጆች ሊያዩ የማይገባቸውን ሳይት የሚመለከቱት፣ ብዙውን ጊዜ (79% ያህል ጊዜ) ከቤታቸው ነው::"[17]

[15] (Internet safety 101.org)
[16] Victoria Rideout, Donald F. Roberts. Ulla G. Foehr. March 2005. The Henry J. Kaiser Family Foundation. 17 November 2006 (Generation M: Media in the Lives of 8-18 Year-Olds. http://www.kff.org/entmedia/up...f-8-18-Year-olds-Report.pdf
[17] http://www.unh.edu/ccrc/pdf/CV138.pdf).

ልጆቻችንን ወደ መጥፎ አቅጣጫ ሊስብ የሚፈልገው የጊዜው ቆሻሻ ወደ እነሱ አካባቢ እንዳይደርስ ከፈለግን፣ ኮምፒዩተር አጠቃቀማቸውን በብልሀት እናድርግ (ልጆቻችንን፣ ሊያዩዋቸው ከማይገቡ ከአስቀያሚ ሳይቶች ለመከላከል፣ ወላጅ ምን እርምጃ መውሰድ እንደሚችል፣ አለፍ ብለን ከስር እንመለከታለን::)

## *የቍሳቍስ ተጽእኖ*

ሌላው፣ የልጆቻችንን የአእምሮ ስፋትና ጥበት የሚወስነው፣ ሸቀጥን የሚያዩበት ዕይታ ነው:: ሸቀጥ እንደ ገፍ ባለበት፣ በውጩ አገር እንኖራለን:: በብዙ ዕቃ ተከበው ግን፣ መሳቅን እንኳ የረሱ፣ ብዙ ሰዎች እንዳሉ በአካለ ሥጋም ሆነ በቴሌቪዥን እናያለን::

ልጆቻችንን፣ ከሚያስፈልጋቸው በላይ በዕቃ አናፍናቸው:: "ሕይወታቸውን በደስታ ይሞላዋል፣ ስለ ራሳቸው ያላቸውን አስተሳሰብ በጥሩ ይለውጠዋል" ብለን አስበን፣ ጥሩ ወላጅ የመሆን ምልክት መስሎን፣ በማያስፈልግ ዕቃ አንክበባቸው:: እንዲህ አላደረኩላቸውም" የሚል፣ የጸጸት ስሜት በሸቀጥ ለማካካስ፣ አንሞክር፤ ያ ልጆቻችንን ይጎዳቸዋልና:: ስለ ቁሳቁስ ተጽእኖ የሚከተሉትን እውነታዎች እናስተውል፤

- ልጆቻችን ቁሳቁስ ላይ ከሚያስፈልገው በላይ ሲጣበቁ፣ ሰፋ አድርገው እንዳያስቡ ይገድባቸዋል፤
- ሸቀጥ በሕይወታቸው ትልቅ ስፍራ እንዲኖረው ቦታ ስለሚከፍት፣ ለሕይወት ዋነኛ ነገሮች ጊዜ እንዳይኖራቸው ያደርጋል:: ሕይወት በእነርሱ አዲሷ ዲቪዲ ጌም ዙርያ ብቻ እንደ ተወሰነች ማመን ይጀምራሉ፤
- ከእነርሱ ውጭ ሕይወት እንዳለ፣ በዓለማችን የሚበሉት እንኳ የሌላቸው ልጆች እንዳሉ ይረሳሉ፤
- ስላላቸው ጥሩ ነገር እንኳ በቅጡ አይረዱም:: ያ ነገር ለእነርሱ በግድ መደረግ እንዳለበት የሚያምኑ፣ ሸቀጡም እንዲያው ያለ አንዳች ድካም ዝም ብሎ የተገኘ ነገር እንደሆነ የሚያስቡ ይሆናሉ::
- ይህ ሁሉ ሆኖም ግን ደስተኛ አይሆኑም:: በውጩ ሁሉ ነገር ያላቸው ቢሆንም፣ ውስጣዊ ደስታ ስለማያገኙበት፣ የበለጠ ነገር የሚፈልጉና ለበለጠ ሸቀጥ የሚራቡ የሚጠሙ ይሆናሉ::
- ሁሉ ለእኔ ለእኔ የሚሉ ለራሳቸው ብቻ የሚያስቡ ስግብግቦች እንዲሆኑ በር ይከፍታል::
- ፍቅራችንን በምንገዛው ሸቀጥ ብዛት ልናሳያቸው ስንሞክር፣ ሸቀጥን የፍቅር መግለጫ ብቸኛ መንገድ አድርገው ይረዳሉ:: ሰው እንደወደዳቸው የሚያስቡት ዕቃ ሲገዛላቸው ብቻ ይሆናል:: ሲያድጉም ፍቅርን ለመግለጽ የሚሞክሩት፣ የትዳርን ፋይዳ የሚመዝኑት በሸቀጥ ብቻ ይሆናል::





በማደግ ላይ ባሉ ሐገሮች የተወለዱ ህጻናት፣ እጅግ ትንሽ ነገር ሲገዛላቸው፣ እንዴት ደስ ተሰኝተው፣ መጫወቻውን ወደው እንደሚንከባከቡት ግልጽ ነው:: እንደ አሜሪካ፣ ካናዳና አውሮፓ ባሉ በታዎች አብዛኛዎች ልጆች ብዙ ቢደረግላቸውም፣ እምብዛም እንደማይደንቃቸው እናያለን አይደለምን? አስገራሚ ቢሆንም፣ ሐቁ ይኸው ነው:: የሰው ልጅ ከሚገባው በላይ በውጫዊ ነገር ሲከበብ፣ ሸቀጡ ከማስደሰት ይልቅ አፋኝ ይሆንበታል::

- ልጆቻችን ሁሌ ይህ ዕቃ ይገዛልኝ የሚሉ ከሆነ፤
- ሁልጊዜ፣ ራሳቸውን ከሌላ ልጆች ጋር እያስተያዩ፣ "እገሊት ይሄ አላት፤ እገሌ ያ አለው እና እነርሱ ያላቸው ከሌለኝ" የሚሉ ከሆነ፤
- አንድ ስጦታ ሲሰጣቸው ሳያመሰግኑ የሚወስዱ ከሆነ፤
- መኝታ ቤታቸው በብዙ ነገር የተጣበበ ከሆነ፤

ምናልባትም ለልጆቻችን ሽቀጥ ከሚገባው በላይ በዝቶባቸዋል:: በሕይወት ውስጥ ከዕቃ የበለጠ ትላልቅ ዋጋ ያላቸው ነገሮች እንዳሉ የተረዱ፣ ደስታቸው ባላቸው ሸቀጥ ወይም በሌላቸው ነዋይ ላይ ያልተመሠረተ፣ ከዚያ ዐርነት የወጡ ልጆች ማሳደግ ከፈለግን፣ ካላግባቡ በሸቀጥ ፍቅር እንዳይነደፉ እንጠብቃቸው::

የፍቅር መግለጫ ሸቀጥ እንዳልሆነ እናሳያቸው:: ደስተኛ ለመሆን፣ ነጋዴ ሊሸጥ የፈለገውን እቃ ሁሉ መግዛት እንደሌለባቸው እናስተምራቸው:: እንዲያውም ይህ አጋጣሚ የሸቀጥን ጠባብነት ለማስተማር እንደ ምክር እንጠቀምበት:: "የሰውን ልጅ ዋጋ የሚሰጠው ምን ይመስልሀል? "አንድ ሰው ብዙ እቃ ስላለው፣ ጥሩ ስለ ለበሰ፣ ያን ሰው ዋጋውን የሚጨምር ይመስልሻል ወይ?" ብለን እንዲያስቡበት እንፍቀድላቸው:: በመገናኛ ብዙኀን ማስታወቂያ የሚሰሩ የተለያዩ አካላት፣ እቃቸውን ለመሸጥ ስለሚጠቀሙበት ስለተለያየ ዘዴ እንንገራቸው::

ጓደኛዬ አላት/አለው ያሉትን ዕቃ ሁሉ አንግዛላቸው:: "ጓደኛሽ አላት ማለት አንቺ ሊኖርሽ ይገባል ማለት ነው ወይ?" የሚለውን ቁልፍ ጥያቄ መልሰን መላልሰን እንጠይቃቸው:: በርግጥ በዚች ዓለም የሚኖሩ ሰዎች ናቸው፤ እንደ ጓደኞቻቸው መሆን፣ መልበስ ያምራቸዋል:: ልጆቻችንን ፍጹም ከሰው የተለዩ ሰዎች አድርገን እናሳድጋቸው እያልን አይደለም:: ነገር ግን ሸቀጥ በሕይወታቸው ውስጥ ትክክለኛውን ቦታ እንዲይዝ፣ ሸቀጥ አምላካቸው እንዳይሆን አድርገን እናሳድጋቸው ለማለት ነው::

መጫወቻ ልንገዛላቸው ያሰብነውን ገንዘብ ቤተሰብ አብረን ተሰብስበን ራት እንመገብበት፤ያ ለሕይወታቸው እጥፍ ድምቀት ያመጣል፤ ብዙ ገንዘብ የማያስወጣ ቦታ ቤተሰቡ ሁሉ አብረን እንሂድ፤በእቃ ላይ የሚወጣውን ሀይልና ጊዜ እንደዚህ አብሮ ማሳለፍ ላይ ስናወጣው የልጆቻችንንም የእኛንም ሕይወት በጣም እንጠቅማለን፤ ልጆቻችንም ከጠበበ አስተሳሰብ እንዲወጡ እናበረክታለን::





## *ልጆቻችን የለመለመ አስተሳሰብና ግንዛቤ እንዲኖራቸው ምን ማድረግ እንችላለን::*

- ***የበጎ ፍቃድ አገልግሎት***

ሌላን ሰው በመርዳት፣ ሌላን ሰው በፍቅር በመንካት ውስጥ እንዲሳተፉ፣ ከልጅነታቸው ጀምሮ ሁኔታዎችን ማመቻቸታችን፣ ለልጆቻችን ውስጣዊ ደስታ፣ ውስጣዊ ጤንነት፣ አርቆ ማየትና ማሰብ ያበረክታል። ልጆቻችን ከራሳቸው ያለፈ፣ ሌላ ሰውን የሚረዱ፣ የሚያገለግል ሕይወት ውስጥ እንዲገቡ መርዳታችን፣ ሕይወታቸውን በብዙ መንገድ ይለውጠዋል።

- ☞ ሌሎችን በመርዳት የሚገኘውን እውነተኛ ደስታ በትክክል እንዲያጣጥሙ ያደርጋቸዋል:: የሌላን ሰው ሕይወት በመንካት የሚገኘው ደስታ በሸቀጥ ከሚገኘው ደስታ ይልቅ፣ ጠንካራና ዘለቄታ ያለው እንደ ሆነ ይረዳሉ::
- ☞ ሰውን መውደድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ ከሰው ጋር የሚኖር ማኅበራዊ ግንኙነት ምን እንደሆነ በቅጡ ይረዳሉ:: እውነተኛ ፍቅር፣ እውነተኛ ሰላምና ከሰዎች ጋር ኅብረት ማድረግ ወደ ልጆቻችን ሕይወት ይገባሉ::
- ☞ አስተሳሰባቸውን ይለውጠዋል:: ሌላውን በመርዳታቸው፣ ዓለም በእነርሱ ችግር ዙርያ ብቻ የምታጠነጥን እንዳልሆነች ይረዳሉ:: ከዓለም ችግር ጋር ሲነጻጸር የእነርሱ ችግር እዚህ ግባ የሚባል ነገር እንዳልሆነ ይገነዘባሉ:: ባላቸው ነገር ተመስገን ማለትን እንዲማሩም ያደርጋቸዋል::
- ☞ የከበባቸው ዓለማዊ ነገር ሊሰጣቸው ያልቻለውን፣ ትርጉም ያለውን ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ሰውን ጧት ከዐልጋው አዘልሎ የሚያስነሣው፣ ውስጡ አንቀሳቃሽ ሞተር የሚሆን፣ ከዕለት ጉርሱ ያለፈ ዐላማና ትርጉም ሲኖረው ነው:: ሌላውን በመርዳታቸው ሂደት ውስጥ፣ የችግሩ ሳይሆን የመፍትሔው አካል እንደሆኑ እንዲያውቁ

ያደርጋቸዋል፤ ይህም የወደፊት አቅጣጫ አሳዩ፣ መሪ ይሆናቸዋል። የነገዎቹ ዶክተሮች፣ መሀንዲስ፣ ጸሐፊ፣ የነገ አስተማሪ፣ አዲስ ነገር ፈጣሪ፣ ልጆችን ሰብስቦ አሳዳጊ፣ የነገ ስለ ሰው መብት ተከራካሪ ይሆናሉ። ባጭሩ በተሰጣቸው ችሎታና ስጦታ፣ የሰብአውያን ሕይወት አብሪ ክዋክብትና ጸሐይ ይሆናሉ። በዚህ በውስጣቸው በተዘረጋው አቅጣጫን የሚቀይስላቸው ኀይልም ፣ ከማንም በላይ እነሱ በርተውበት ይኖራሉ።

☞ ቤተሰብ አብረን ሌላን ሰው በመርዳት ነገር ውስጥ ስንሳተፍ፣ ያስተሳስረናል። በቤተሰብ መኻል ፍቅርን፣ጥሩ ትዝታን ይፈጥራል። ቅዱስ ለሆነ አላማ ተባብረን እየሰራን ነውና፣ ይህ ለትስስራችን ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ዋናው ሰውን በመርዳት ነገር ውስጥ መሳተፋቸው ነው እንጂ፣ ለምናደርገው ነገር አንድ አይነት ቀመር መኖር የለበትም፤የተለያዩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራዎች ላይ ቤተሰብ አብረን ልንሳተፍ እንችላለን። አንዳንድ ምሳሌዎችን እንይ፤

- ቤተሰብ ሁሉ፣ ወላጅ የሌለው ልጅን በመርዳት ላይ እንዲሳተፍ ልናደርግ እንችላለን። "እናንተም በዚህ ትሳተፉላችሁ ብለን ለልጆቻችን ነግረን፣ ለዚህ ልጅ ወይም ለእነዚህ ልጆች በየሁለት ሳምንቱ ወይም በየወሩ ደብዳቤ እንዲጽፉ፣ የሚያበረታታቸው መልእክት እንዲልኩላቸው ልጆቻችንን ማበረታታት።
- በኛው አካባቢ የሚኖር የሆነ እርዳታ የሚያስፈልገው ሰው ካለ ለምሳሌ፣ "ዛሬ እኔና ልጆቼ ቤትህ መጥተን በዚህ ነገር እንረዳሀለን" ብለን ነግረን ልጆቻችንን ይዘን ሄደን በዚያው ውስጥ ማሳተፍ።
- ለታመመ ሰው ምግብ እንስራ ብለን እነርሱም በቻሉት ምግቡን መስራት ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ።
- መኖርያ የሌላቸው ሰዎች የሚኖሩበት ቦታ በምሳና ራት ሠዓት ሄደን፣ ምግብ ሲቀርብ መርዳት።





- አጠገባችን ያለ አሮጊት ሽማግሌዎች የሚኖሩበት ነርሲንግ ሆም ሄደን፣ ሰዎቹን ቁጭ ብሎ ማውራት ፣ ከእነሱ ጋር አብሮ ጊዜ ማሳለፍ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ።
- አገር ቤት ስንሄድ፣ ልጆቻችን እንደ ቱሪስት ጎብኝተው ብቻ እንዲመጡ በማድረግ ፈንታ፣ ለትንሽ ቀንም ቢሆን ሌላን በመርዳት በበጎ አድራጎት ስራ ውስጥ ተሳትፈው እንዲመጡ ማድረግ፤
- የገና በአል ሲመጣ ለራሳቸው ስጦታ ብቻ ማሰብ ሳይሆን፣ ለሌላ የሚሰጡበትንም መንገድ እንዲያስቡ፣ ጊዜ ኀይላቸውን እንዲሰጡ፤ ከምንሰጣቸው የኪስ ገንዘብ ትንሽ አውጥተው ሌላን እንዲረዱ ማበረታታት ወዘተ።

እኛም ጊዜ ወስደን ለልጆቻችን፣ የሕይወት ትርጉም ለራስ ብቻ መኖር እንዳልሆነ ሌላን መርዳት፣ ሌላን መደገፍ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እንንገራቸው። "እኔ ታምሜ ፣ተቸግሬ ሌላ ሰው መጥቶ ቢረዳኝ ደስ ይላችኋል አይደለምን? ለሌላም ለተቸገረ ለታመመ መርዳት እንዲሁ ያንን ቤተሰብ ደግሞ ደስ ያሰኛል፤ ይባርካል" እያልን፣ እነርሱን በሚገባ መንገድ እናስረዳቸው።

ልጆቻችን በውጭ ብቻ ሳይሆን በቤት ውስጥም፣ ከእኔነት የራቀ ተግባር እንዲማሩ ተግተን እንስራ። የሚፈልጉት ሁሉ እየተደረገላቸው፣ ግን መስጠት ሳይጠበቅባቸው አድገው እኔነትን ወርሰው የሚያድጉ፣ ለስጋ ወንድም እህታቸው እንኳ ከቦታቸው ወጥተው ማድረግን የማይፈልጉ ብዙ ልጆች አሉ። ልጆች በኋላ ሲያድጉ ከወንድም እህታቸው ጋር በፍቅር ከሚያስተሳስራቸው ዋና ነገር፣ በልጅነት የተማሩት እርስ በእርስ የመረዳዳት፣ የመካፈል እና የመተጋገዝ ጸባይ ነው። በወንድምና እህት መሀል ያ ጸባይ እንዲኖር እንጣር። ልጆች ቤት ውስጥ እህታቸውን መርዳት፣ ወንድማቸውን ማገዝ፣ እናት አባታቸውን ማገልገል እንዲማሩ አድርገን እናሳድግ። በቤተሰብ ውስጥ መቀበል ብቻ ሳይሆን መስጠት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እናስተምር። ልጆቻችንን በምን አይነት የበጎ ስራዎች ልናሳትፍ እንደምንችልና፣

ባጠቃላይ በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ጥሩ ሀሳቦችን የሚሰጠን ድረገጽን ከስር ይመልከቱ:: [18]

- ***በጎ ሥነ ምግባርን ማስተማር***

ውስጡ ተንኮል፣ ቂም፣ ያለበት፣ ስለሌላው መጥፎ የሚያስብ ሰው፣ ከማንም በላይ ራሱ በስቃይ ውስጥ ይኖራል:: በሚኖርበት ህብረተሰብ ውስጥም የልብ ጓደኛ አይኖረውም:: በውስጡም ሰላም አጥቶ ይኖራል፤ ከስጋ ያለፈ ትርጉም ያለው ሕይወትንም ሳያውቅ ያልፋል:: ልጆቻችንን፣ ቅንና ጥሩ ሰዎች እንዲሆኑ አድርገን ስናሳድጋቸው፣ ከማንም በላይ የራሳቸው ሕይወት እንዲለመልም እያበረከትን ነው:: ደስተኛ ይሆናሉ፤ በሰው ዘንድ በጣም የተወደዱ ይሆናሉ:: ለራሳቸውም ለሌላውም ሕይወት በትልቁ የሚያበረክቱ ሰዎች ይሆናሉ:: ልጆቻችን ውስጥ ይህን ዋነኛ ሀብት ማበልጸግ ከፈለግን፣ ከልጅነታቸው ጀምሮ እናስተምር፤ ሰውን ከልብ እንዲወዱ፣ እንዲያከብሩ እናስተምር። ስለ መጥፎና ጥሩ ምግባር ግንዛቤን እንስጥ:: ውሸት፣ ስለ ሌላ ሰው ቁጭ ብሎ ማውራት፣ሌላን ዝቅ ማድረግና ተንኮል፣ እንዴት መጥፎ እንደሆነ እንንገር:: አንድ ነገር አደርጋለሁ ብለው ቃል ከገቡ፣ ቃልን መጠበቅ ምን ያህል አስፈላጊ ምግባር እንደሆነ ከልጅነታቸው እናስተምር::

[18] (ልጆቻችን የበጎ አድራጎት ስራ (volunteer) ሊያደርጉባቸው ስለሚችሉ ስለተለያዩ ቦታዎች ጥሩ ግንዛቤ የሚሰጥ ዌብ ሳይት dosomething.org
ከዛ በተረፈ ኢንተርኔት ጉግል ውስጥ ገብተን ያለንበትን ስቴት፣ ካውንቲ ጽፈን (volunteer opportunity) ብለን ብንጽፍ ልጆቻችን በበጎ አድራጎት ስራ ሊሳተፉባቸው ስለሚችሉ የተለያዩ ቦታዎች ምሪት እናገኛለን።)





ልጆቻችን ሌላን የሚጎዳ ነገር ሲያደርጉ ስናይ፣ "አይ ልጅ ናቸው" ብለን ወይንም፣ "ለልጄ አግዛለሁ" ብለን፣ ዝም አንበላቸው፤ እንደዚያ ስናደርግ የኛኑ ልጆች እንጎዳለንና፤ ውስጣቸውን የሚበላ መጥፎ ትምህርት እንዲነግስ መንገድ እንከፍታለንና:: መጥተው ስለ ሌላ ሰው ሊያሙልን ከፈለጉ፣ በቶሎ ብለን ያንን ምግባር እንቃወም:: "ስለ ሌላ ሰው ማውራት አያስፈልግም፤ የምትነግሩት ነገር ካለ ለዛው ሰው ተናገሩ" ብለን፣ ትምህርት እናስተምራቸው:: እኛ በምናስተምራቸው ትምህርት ምክንያት፣ ወሬን እየጠሉ ይመጣሉ:: እርስ በእርስ ወይ ከሌላ ልጅ ጋር ሲጫወቱ፣ ሌላውን የሚጎዳ ወይ የሚጫን ነገር ሲያደርጉ ወይ ሲናገሩ ካየን፣ በስግብግብነት የሌላን እቃ ሲቀሙ ለኔ ለኔ ሲሉ ከተመለከትን፣ በቶሎ ብለን እናርማቸው፤ የወደፊት ማንነታቸው የሚቀረጸው፣ ዛሬ በሚማሩት ትምህርት ነውና:: ባጠቃላይ፣ ለሌላው ጥሩ እንዲያስቡ፣ እንዲያደርጉ እናስተምር::

እኛ ከምንነግራቸውም በላይም፣ ስናደርግ የሚያዩን ዋነኛ ትምህርት እንደሚሆናቸው እናስታውስ::

☞ የቱንም ያህል ሰውን አትሙ ብንላቸው፣ እኛ ቁጭ ብለን ስለ ሌላው ስናወራ እያዩ ካደጉ ወሬን ተምረው ያድጋሉ፤ እነሱም ሲያድጉ ሀሜተኛ እንዲሆኑ በትልቁ ያበረክታል እኛ ምንለውን በልባቸው ቋጥረው አድገው፣ ሰውን ሁሉ ተጠራጣሪ ይሆናሉ::
☞ በምሬት ስለሰው ሁሌ ስናወራ ካዩ ምሬተኛ፣ ልባቸውን የዘጉ ሰዎች እንዲሆኑ ያበረክታል::
☞ አንድ ነገር አደርጋለሁ ብለን ቃል ገብተንላቸው፣ ምንም ሳይመስለን ቃላችንን የምናጥፍ ከሆነ እነሱም በቃላቸው ጽኑ ያልሆኑ እንደፈለጉት የሚለዋውጡ ይሆናሉ:: በሌላ በኩል፣ አቅቶን ባናደርግ እንኳ፣ "ይቅርታ ተሳስቻለሁ" ብለን ሁኔታውን ካስረዳናቸው፣ ቃልን መጠበቅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የተረዱ፣ የነገ ትላልቅ ሰዎች ይሆናሉ::

ባጠቃላይ፣ ወላጅ የሚያሳየው ምሳሌነት የልጅን ምግባር በዋነኝነት እንደሚቀርጽ ተረድተን፣ የእኛንም፣ አረማመዳችንን እንመርምር:: ልጆቻችንን እንዲህ በምክርም በተግባርም ስናንጻቸው፣ በፍቅር ያበቡ የደመቁ፣ ቅን የሚያስቡ፣ በሌላውም ዘንድ የተከበሩ፣ የተወደዱ ሰዎች ይሆናሉ::

- ***ልምላሜ በመንፈሳዊ ሕይወት***

ልጆቻቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያብቡ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ትስስር ኖሮዋቸው እንዲያድጉ፣ የሚፈልጉ ብዙ ወላጆች አሉ:: በእነዚህ ወላጆች ስር አድገው፣ ከእግዚያብሔር ጋር ትስስራቸው ጠብቆ ለምልሞ የሚኖሩ ልጆች አሉ፤ ከቤት ሲወጡ የእግዚአብሔርን ነገር አታንሱብኝ የሚሉም ልጆች ይኖራሉ::

በዚህ ጉዳይ ላይ ዋነኛ ተጽእኖ ያለው፣ በወላጅ ሕይወት ውስጥ ተፈናጥቆ የሚያዩት ምሳሌነት ነው:: እመኑ የምንላቸው እግዚያብሄር፣ በኛ ሕይወት ውስጥ መታየት አለበት:: እኛ እግዚአብሔር እግዚአብሔር እያልን እየዋልን፣ ከኛ ውስጥ ግን ዘወትር ሾልኮ የሚወጣው፣ እግዚአብሔር ከሚጠብቅብን ማንነት የተለየ ከሆነ፣ እውነቱን ሳይረዱ ይቀራሉ፤ እውነተኛው የእግዚአብሔር ነገር በእኛ ውስጥ ተፈናጥቆ አይታያቸውምና:: ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ትስስርን ለማዳበር እየጣርን፣ ስህተታችንን ለማረም እርምጃ እየወሰደን፣ ከእውነት በመነጨ ቅንነት፣ ሌላን ይቅር ማለት፣ ውስጣዊ ሰላምና ፍቅር የምንኖር ከሆነ ግን፣ ያ ሀይል ተፈናጥቆ ለልጆቻችን ትልቅ ምስክርነት ይሆናቸዋል፤ የኛኑ መንገድ መከተልም ይፈልጋሉ::

ከእነርሱ ጋር ባለን አንድ በአንድ ግንኙነትም፣ እንደዛው ነው:: ቀን ለሊት ሀይማኖታዊ ልምምድ ስናደርግ ቢያዩ እንኳ፣ ዘወትር ከእኛ ውስጥ የሚወጣው ምሬት እነርሱን መዳኘት፣ መስደብ፣ዝቅ ማድረግ ከሆነ፣ እንዲያውም ጭራሽ እግዚአብሔር ጋር የተያያዘ ነገርን መፍራት ይጀምራሉ:: ከእኛ የያዙትን እልህ ከእግዚአብሔር



ልጅን እንዴት ላሳድግ? በምዕራብ አገሮች

ጋር አያይዘው፣ "የእነርሱ እግዚአብሔር ጫፌም እንዳይደርስ" ብለው፣ ጭራሽ ጀርባቸውን ይሰጣሉ:: ወደ ፊትም ስለ እግዚያብሄር ሲያስቡ ቶሎ ብሎ የሚታያቸው፣ ከእኛ ተፈናጥቆ ያዩት መጥፎ ምሳሌ ይሆናል:: ዘወትር ፍቅርን ስናሳያቸው፣ ለማንነታቸው ስናቅፋቸው፣ ስናከብራቸው፣ ደግነትን ደጋግመን ስናሳያቸው፤ ስለ እግዚአብሔር ስንነግራቸውም ልባቸውን ከፍተው ያዳምጣሉ፤ ውስጣቸውን ከፍተው እንዲያዳምጡን የሚያበረታታ ምግባር ከእኛ ውስጥ ተፈናጥቆ ያያሉና::
ሌላው ወላጅ ልብ ማለት ያለበት ነጥብ ይህ ነው:: እግዚአብሔርን ከልባቸው እንዲያውቁት፣ የእግዚአብሔር ማንነት ከልብ እንዲገባቸው መንገድ መጠረብ እንጂ፣ በሀይላችን ውስጣቸው ልንወሸቅባቸው አንሞክር:: እውነተኛ ማንነቱ እንዲገባቸው፣ ወደፊት አድገው ከቤት ሲወጡም የሚቆይላቸው እምነት በውስጣቸው እንዲሰራ እንጂ፣ እኛን ፈርተው ብቻ እንዲታዘዙ ማድረግ እናቁም:: ልጅ ልቡን ከፍቶ እግዚአብሔርን የሚወደው እና የሚቀበለው ውስጡ ሲመሰጥ እንጂ፣ በግድ ካልተከተልክ ሲባል አይደለም:: የምንወደውን ምግብ እንኳ "በግድ ብሉ" እያሉ ቢገርፉን፣ ያ ምግብ ሊያስጠላን ይመጣል:: እግዚአብሔርን ከልብ እንዲያውቁት ሁኔታዎችን በማመቻቸትና መንገዱን በመክፈት፣ ልጆቻችንን በመርዳት ፈንታ በግድ ጠምዝዘን ከእግዚአብሔር ጋር ተሳሰሩ ብንል፣ ግዴታው አስጨንቋቸው ጭራሽ ይርቃሉ:: ሲያድጉም ትዝ የሚላቸው በልጅነታቸው ልናስገድዳቸው የሞከርነው ነውና፣ ጭራሽኑም ዝር ማለት አይፈልጉም::

ልጆች፣ የእግዚአብሔር ማንነቱን፣ በእውነተኛ ሕይወታቸው ውስጥ ሊገባቸው በሚችል መንገድ እንዲረዱት እንዴት መንገድ እንከፍታለን? ቤተሰብ በሳምንት አንድ ቀን ወስነን፣ አብረን ተሰብስበን እግዚያብሄርን እናምልክ፣ ያ ለልጆች የማይረሱትን ትምህርትን ይሰጣቸዋል::ከልጅነታቸው ጀምሮ ስለእግዚአብሔር ስናስተምር፣ እውነቱ እንዳለ ሆኖ፣ ትምህርቱን ለእነርሱ በሚስባቸውና በሚገባቸው፣ መልክ እናቅርበው፤ ለምሳሌ ልናስተምራቸው የምንፈልገውን እውነት ከታሪክ ጋር እያያዝን

ብናቀርበው፣ ሊያዳምጡን የበለጠ እድል ይኖራቸዋል። ልጆች መዝሙር በጣም ይወዳሉና አብረን እግዚያብሄርን እናምልክ።

ከሕይወታቸው ጋር እያያዝን ትምህርትን እናስተምራቸው፤ ሩቅ ያለ፣ እንዲሁ ለአንዴ ጸሎት ብቻ የሚያስታውሱት አምላክ ሳይሆን፣ በየቀኑ ባለ ፈተናቸው፣ እርምጃቸው፣ ጥያቄያቸው እንዴት ሊረዳቸው እንደሚችል፣ ጊዜ ወስደን ለልጆቻችን እናስረዳ። ጊዜያችንን ወስደን ማስረዳት ብቻ ሳይሆን ጥያቄያቸውን እንመልስ። ማንም ሊረዳቸው በማይችልባቸው ሁኔታዎች እግዚያብሄር ግን ሁልጊዜ አብሯቸው እንደሚሆን እንንገር። እሱ እንደሰው ውጫቸውን አይቶ እንደማይዳኛቸው፣ በተፈጥሮ ማንነታቸው ከልብ እንደሚወዳቸው፣ ለልጆቻችን እናስተምር። ሕይወታቸው ትርጉም ያላት፣ ያበበች እንድትሆን፣እግዚአብሔር እንደሚረዳቸው ደግመን ደጋግመን እንንገራቸው። ልጆቻችን ስላላቸው ህልምና ፍላጎት እንጠይቅ፤ አብበው ፈክተው እንዲወጡ ከራሳቸውም አልፈው ለሌላም የሚሆን ትልቅ ፍሬ እንዲያፈሩ እግዚአብሔር እንደሚረዳቸው እናስተምር። ከልጅነታቸው እንሥቶ በችሎታ በእውቀታቸው፣ በጊዜያቸው ሌላን ማገልገል እንዲማሩ እናድርግ፤ ከስጋ ያለፈው የእግዚአብሔር ትልቁ አላማ እንዲገባቸው መንገድ ይከፍታልና።

ስለ እግዚአብሔር ትምህርት የሚያገኙበት ቦታም፣ ለልጆች በሚስማማ ሊያዳምጡት በሚችሉት መንገድ ትምህርቱ እንዲተላለፍላቸው፣ ሀሳብን እናቅርብ፤ እኛም ሀሳብን መስጠት ብቻ ሳይሆን የእውቀትና የጊዜን እርዳታን እንለግስ፤ ከሌሎች ወላጆችም ጋር እጅ ለእጅ እንያያዝ።ልጆቻችን እግዚአብሔርን ከልብ እንዲያውቁት መንገዱ ሲመቻችላቸው፣ ሰው ለቅርብ ወዳጅ ልቡን እንደሚከፍተው፣እግዚአብሔርን ከልብ መቅረብ ይጀምራሉ፤ ወላጅ በሌለበትም፣ በራሳቸው ባዳበሩት ትስስር ጠንክረው ጉዞዋቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ይቀጥላሉ።





- ***በራስ መተማመን***

ልጆቻችን ሌላን በደበና የሚከተሉ የሌላ ግልባጭ በመሆን ፋንታ፣ በማንነታቸው የሚቆሙ፣ ራሳቸውን መሆን የማይፈሩ ሰዎች መሆናቸው፣ ሌላው በጣም አስፈላጊ ምጥቀት ነው። ይህ በውስጣቸው የተሰራው ማንነት፣በሕይወታቸው ለሚገጥሟቸው ለተለያዩ ግፊቶች መከላከያ ከመሆኑም በላይ፣ ለየት ወዳለ ቦታ እንዲመጥቁ ትልቅ እርዳታ ይሰጣቸዋል።

ብዙ ልጆች፣ የተፈጥሮ እውነተኛ ማንነታቸው ከስር ተወሽቆ፣ የሌላ ግልባጭ፣ ተከታይ ሆነው ያድጋሉ። ይህ በተለይ በእኛ ባህል ውስጥ ለሚያድጉ ልጆች ዋነኛ ፈተና ሊሆን ይችላል፤ ልክ ሌላን መምሰል እንዳለብንና ሌላው እንዳደረገው ማድረግ እንዳለብን የሚጠብቅብን የማህበረሰብ ግፊት አለና። አንዳንዴም ወላጆች ሳናስበው፣ የራሳችንን ፍርሀት በቀላሉ ወደ ልጆቻችን ልናስተላልፍ፣ እንችላለን። ሁሌ ከሌላ ሰው ልጅ ጋር ካስተያየናቸው፣ "የነእገሌ እገሊት ልጆች እንደዚህ እንደዛ ናቸው እናንተ እንደዚህ አይደላችሁም" ብለን የምንደጋግምባቸው ከሆነ፣ "የሌላው ቤተሰብ እንዲህ ሞልቶለት የኛ ይህ ጎደለው" ብለን ስናወራ እየሰሙ ካደጉ፣ በውጥረትና ፍርሀት ሌላ ሰውን ሲመለከቱ የሚኖሩ፣ ሌላውን ለመገልበጥ ሲሯሯጡ የሚኖሩ ሰዎች ይሆናሉ። ይህ ጸባይ አብሮዋቸው ካደገም በኋላ፣ ዋነኛ የሕይወት ግባቸው፣ ሌላን መመሰጥ፣ለሰው አስመሳይ ስእል መሳል ብቻ ሆኖ ይቀራል።

ልጆቻችን የራሳቸው በሆነው እውነተኛ ማንነታቸው ውስጥ እንዲኖሩ አድርገን እናሳድግ። በራሳቸው ማንነት ይደጉ ማለት፣ "ለሰው መጨነቅ ካቆምን ቆይተናል"፣ የሚል መልእክትን ሊልክ የሚሞክር፣ የውጭ ሀይለኝነትና አላስፈላጊ ድፍረት፣ ማለት አይደለም፤ እውነተኛ ነጻነት ማለት በማንነት ሳያፍሩ፣ "ሌላ ምን አለኝ" ብለው ቀን ሌሊት ሳይወጠሩ፣ በውስጣዊ ሰላምና

እረፍት መኖር ማለት ነው። ልጆቻችን ከውስጣዊ እስራትና ፍርሀት፣ ነጻ የሆኑ ሰዎች እንዲሆኑ አድርገን እናሳድግ።


- ☞ ሌላን በጎን ሲመለከቱ መኖር እስራት እንደሆነ እንንገር።
- ☞ ሌላ ሰው ስላደረገው ብቻ አንድ ነገር ትክክል ነው ማለት አይደለም፤ ጠንክራችሁ ከሰራችሁ በራሳችሁ መንገድ ማበብ ትችላላችሁ፣ እንበላቸው።
- ☞ ከሌላ በመማር መሀልና ሌላን በመገልበጥ መሀል ትልቅ ልዩነት እንዳለ፣ ሌላን ሊመስጡ እየሞከሩ መኖር እስራት እንደሆነ እናሳውቃቸው።
- ☞ በሕይወት ውስጥ ለየት ላለ ነገር የተነሱ፣ አዲስ ነገር የሰሩ የፈጠሩ ሰዎች፤ ራሳቸውን መሆን ያልፈሩ፣ ሌላን ለመገልበጥ የማይጥሩ ሰዎች እንደሆኑ እንንገር፤ በምሳሌነታችንም ጠቃሚውን ትምህርት ወደእነሱ እናስተላልፍ።

ልጆቻችን ለየት ብለው መቆምን እንዳይፈሩ ስንፈልግ፣ ከጅምላ አስተሳሰብ ለመውጣት የማይፈሩ፣የራሳቸው ህልም ራእይ ያላቸው ሰዎች ጋር እናገናኛቸው፤ ከእነዚህ ዐይነት ሰዎች ጋር ቁጭ ብለው እንዲያወሩ እናድርግ። እነዚህ ሰዎች አንድ ለአንድ የማናውቃቸው ከሆኑ፤ንግግር የሚያደርጉበት ቦታ ልጆቻችንን ይዘን እንሂድ፤ እነሱ የጻፉትን መጽሀፍ፣ የቀረጹትን ቪዲዮ፣ እናሳይ፤ እነዚህ ሰዎች ለልጆቻችን ምሳሌ ሊሆኗቸው፣ ራስን ችሎ ማሰብ ምን ማለት እንደሆነ በተግባር ሊያስተምሯቸው ይችላሉና።





# የሕይወት ተሞክሮ



## ሐና ጎዲፉ

ሐና ለየት ብለው ከተነሱና፣ በአላማ፣ ህልማቸው ከመጠቁ ልጆች መሐል አንዷ ናት፡ በትንሽ እድሜዋ፣ ብዙዎችን ያስገረመ አስተዋጽኦ ለህዝቧ አበርክታለች። ከሐና ጋር የተደረገው ቃለ መጠይቅ እነሆ።

➢ እስቲ ስለራስሽ ትንሽ ንገሪን?

ሀና ጎዲፉ እባላለሁ፤ እድሜዬ 14 ነው። ተወልጄ ያደግኩት ካናዳ ውስጥ ነው። የምኖረው ከአባቴ፣ ከእናቴና ከታናሽ ወንድሜ ጋር ነው።

➢ ህልምሽ በውስጥሽ እንዴት እንደተጠነሰሰ፣ እስቲ ከመጀመሪያው ንገሪን?

ኢትዮጵያ መጀመርያ ስሄድ የዘጠኝ አመት ልጅ ነበርኩ:: አገር ቤት ሄጄ፣ ባህሌንና ዘመዶቼን ሳይ በጣም ደስታ ተሰማኝ:: ወላጆቼ ዘመድ ጥየቃ ገጠር ይዘውኝ ሄዱ:: እዛ አንዲት ጓደኛ አግኝቼ ደስ አለኝ፤ ከሷ ጋራም በጣም ተቀራረብን:: ወደ አሜሪካ መመለሻችን ሲደርስ፣ ዘመዶቼንና ጓደኛዬን ልለይ ስለሆነ፣ በጣም ቅር አለኝ፤ ለአባቴ፣ "ከሷ ጋር በደብዳቤ መጻጻፍ (pen pal) መሆን እችላለሁ ወይ" ብዬ ጠየቅኩት:: አባቴም፣ እዛ አካባቢ ያሉ ልጆች በጣም በድህነት እንዳሉ፣ መጻፍያ እርሳስም እንደማያገኙ ነገረኝ፤ ይህን ስሰማ በጣም ሀዘን ተሰማኝ:: ጓደኛዬንም ሆነ እንደሷ ያሉትን ሌሎቹንም ልጆች ለመርዳት ውስጤ ተነሳሳ:: ካናዳ መጥቼ፣ ትምህርት ቤትም ሆነ ከሌላ ቦታዎችም የእርሳሶችን እርዳታ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ጀመርኩ::

> እነዚህን እርሳሶች ለመሰብሰብ በምትሞክሪበት ሰአት፣ ያጋጠመሽ ሁናቴ ምን ይመሥል ነበር?

እንዳሰብኩት ቀላል አልነበረም፤ ከብዙ ቦታዎች የእንቢታ መልስን አገኝ ነበር፤ ግን ተስፋ ሳልቆርጥ በየቦታው እየሄድኩ፣ ሀሳቤን አቀርብ ነበር፤ ብዙ ልጆች መማር፣ መጻፍ እየፈለጉ ግን በእርሳስ እጦት ምክንያት መጻፍን ሳይማሩ እንደሚቀሩም፣ ለእነዚህ ልጆች መጻፊያ እርሳስ መላኩ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ፣ሀሳቤን እገልጥ ነበር

> በዛ ጊዜ የሥንት አመት ልጅ ነበርሽ? እቅድሽ ምን ያህል እርሳስ ለመሰብሰብ ነበር?

ዘጠኝ አመቴ ነበር:: እቅዴ፣ 20 ሺ እርሳሶችን ለመሰብሰብ ነበር:: ከብዙ ጥረትና የቤተሰብ እርዳታ በኋላ ግን፣ 25 ሺህ እርሳሶችን መሰብሰብ ቻልኩኝ ያንንም ይዤ ወደ አገር ቤት ሄድኩ::





> እዛ ስትደርሽ ምን ተሰማሽ?

ያንን የሰበሰብኩትን 25 ሺህ እርሳስ ይዤ፣ አገር ቤት ስሄድ፣ በውስጤ የተሰማኝን የደስታና የእርካታ ስሜት በቃላት መግለጽ ያቅተኛል፤ ልጆቹ እርሳሶቹን ሲያዩ፣ ምን ያህል እንደተደሰቱ ሳይ፣ እኔም የእነሱ ደስታ ተጋባብኝ:: የብዙ ሰዎችን ድጋፍና ማበረታቻም ቃላት ማግኘቴ ተጨማሪ ሀይል ነበር:: እርሳሱንም አስረክቤ ወደ ካናዳ ተመለስኩ::

> የሚቀጥለው የሕይወትሽ ምእራፍ ምን ይመስል ነበር?

ከተመለስኩ በኋላ፣ የረዳኋቸውን ልጆች ጨምሬ ሌሎችንም ለመርዳት የነበረኝ ፍላጎት የበለጠ ጨመረ:: በዚህ በሁለተኛው ጊዜ 200 ሺህ እርሳስ ለመሰብሰብም ዕቅድን አወጣሁ:: የተለያዩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የህብረተሰብ ማእከሎች፣ ኮምፓኒዎች፣ ቤተክርስትያኖች እየሄድኩ፣ ስለአላማዬ እናገር፣ ነበር፤ በተለያየ መንገድ እርዳታንም ለማግኘት መጣር ቀጠልሁ:: ከብዙ ጥረት በኋላ ህልሜ ተሳካ:: ቀድሞ ካቀድኩት 200 ሺህ ይበልጥ 400 ሺህ እርሳሶችን መሰብሰብ ቻልኩ:: እነዚህን 400 ሺህ እርሳሶች እንዴት እልካለሁ የሚለው ሌላው ጥያቄ ነበር::የኢትዮጵያን ኤርላይንስ በማጓጓዙ ወጪ እንዲረዱን ጠየቅን፤ ከብዙ ሙከራ በኋላ፣ የኢትዮጵያን ኤርላይንስን ድጋፍ ለማግኘት ቻልኩ:: (2000 ኪሎ ግራም) የሚመዝኑ 50 ትላልቅ ሳጥኖች በነጻ ሊያጓጉዙልኝ ተስማሙ፤ ለሰጡኝ ድጋፍም ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነበር:: እኔም በ 13 አመቴ፣ ተመልሼ ወደ ኢትዮጵያ ሄድኩ:: አገር ቤትም ሚድያው ተባበረኝ፤ የትምህርት ሚኒስትር እርሳሶቹን በማሰረጫጨት ረዳኝ::

> የተሰማሽ ደስታ ወሰን የሌለው እንደነበር መገመት አያቅትም::

አዎ፣ ለኔ ትልቁ ስጦታ፣ የልጆቹን ደስታና የመነቃቃት ስሜት ማየቱ ነበር:: ልጆቹ የመማርና ትልቅ ቦታ የመድረስ ፍላጎት እንዳላቸውም ይነግሩኝ ነበር:: "ወደ ፊት ስናድግ እኛም፣ ዶክተር፣ ጠበቃ እንሆናለን፣" ብለው ስለ ህልማቸውም ይነግሩኝ ነበር:: ልጆቹ ያላቸውን መነቃቃትና ህልም ሳይ፣ እነዚህን እርሳሶች ሲያዩ የተሰማቸውን ደስታም ስመለከት፣ ልፋቴ ሁሉ ዋጋ እንደነበረው ተሰማኝ

> ባሁኑ ሰአት ስለወደፊቱ ስታስቢ፣ ምን ይሰማሻል?

በዚህ ሰአት፣ በውስጤ የበለጠ መነቃቃት እና በአገሬ ባህሌ ኩራት ይሰማኛል:: ኢትዮጵያ የወደፊት ተስፋዋ የበራ ነው:: እግዚያብሄር፣ በኢትዮጵያ ላይ ትልቅ አላማ እንዳለውም ይሰማኛል፤ ላገሬና ለህዝቤ በቻልኩት ለማበርከት ውስጣዊ አላማ አለኝ:: ልጆችንና ትምህርታቸውን በተመለከተ፣ ብዙ ማበርከት እፈልጋለሁ:: በተለይ፣ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋ በተያያዘ፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችንና ዪኒቨርስቲ ተማሪዎችን የሚረዳ ነገር ማበረከት እፈልጋለሁ::

> በትንሽነት እድሜሽ፣ እንዲህ ለህዝብሽ እንድታበረክች ተጽእኖ ያደረገብሽ ምንድነው?

ከውስጤ፣ እንድገፋ የሚያበረታታኝ በዋነኝነት የእግዚያብሄር ድጋፍና ምሪት ነው:: ቤተሰቦቼም፣ ሩቅ ቦታ እንዳልም፣ ለህዝቤ እንዳበረክት በትልቁ አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ለሌላው ማድረግ፣ ሌላን በቻልኩት መርዳት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ፣ ከልጅነቴ ጀምሮ ይነግሩኝ ነበር:: ህዝቤን እንድወድና ትልቅ ቦታ እንዳስብም ያበረታቱኝ ነበር:: ሳድግ፣ ቤታችን ሁሌ ፍቅር ነበር፤ አባትና እናቴ ያሳዩኝ ፍቅር፣ ለኔ ትልቅ ድጋፍ ሆኖልኛል:: አባቴ ከኛ ጋ ጊዜ ለማሳለፍ ብሎ፣ (እናቴ ትሰራ ስለነበር) ስራውን ሰአት ቀንሶ ፣ ጊዜውን ለኛ ይሰጥ ነበር:: ባጠቃላይ፣ እናትና አባቴ ምንም እንከን የማይወጣላቸው ጥሩ ወላጆች ናቸው ብል ውሸት አይሆንም::





ሐና ለበጎ ስራዋና ድርጊቷ፣ ከተቀበለቻቸው ብዙ ሽልማቶች መካከል፤ Vaughan Volunteer Award; 2009, Recognition from members of parliament of Don Valley, Young diplomats for humanitarian, Awards for Regional council of Vaughan, Nominated for International peace price for children; 2012, Nominated for June callwood outstanding Award for Volunteerism 20011; Humanitarian of the year, Ethiopia 2007, ይገኙበታል፤

## ከሐና አባት፣ አቶ ጎዲፍ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

- አቶ ጎዲፉ፣ ልጅን ጥሩ አድርጎ ማሳደግን በተመለከተ፣ ለሌሎች ወላጆች የሚሰጡት ምክር አለ ወይ?
  ከሁሉ በፊት እግዚያብሄርን ማስቀደም፣ ለቤተሰብ ሰላምና ደስታ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብዬ አምናለሁ:: ሐና ሳትጸልይ ትምህርት ቤት ሄዳ አታውቅም፤ ሐና ጠዋት ጠዋት ሳትጸልይ ወጥታ አታውቅም፤ ይህ፣ በውስጧ ትልቅ እምነትንና ጥንካሬን ፈጥሮላታል ብዬ አምናለሁ:: ሩቅ ቦታ እንድታስብ፣ ለሌሎች ወጣቶችም መካሪ እንድትሆን፣ የህይወት ዋነኛ ዋጋዋ ውጫዊ ሀብት እንዳይደለ እንድታውቅ ረድቷታል:: ደጋግሜም የምመክራት እግዚያብሔርን በሁሉ ነገር እንድታስቀድም ነው
- አባትና እናት ግልጽ የሆነ የንግግር ልውውጥ፣ ከልጃቸው ጋር መኖራቸው በጣም አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ:: እንደዛ ከሆነ፣ ልጅም ግልጽ መሆንን ይማራል፤ ከናትና ካባቱ የሚደብቀው ነገር አይኖርም

- ለልጅ ፍቅርን ማሳየት በጣም አስፈላጊ ነው:: ልጆችን በፍቅር ስናሳድጋቸው፣ ፍቅራችንን በግልጽ ስናሳያቸው፣ ከወላጅ ጋር ትስስር ይኖራቸዋል::ምክር ሲያስፈልጋቸው ወላጅ ጋር ይመጣሉ፤ወደውጭ አይሄዱም:: ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ ከልጅ ጋር አብሮ ማሳለፍ በጣም ይጠቅማል::
- ልጆች የወላጆቻቸው ነጸብራቅ ይሆናሉ:: አባት እናት በልጆቻቸው ፊት መከባበር፣ ባል ሚስቱን ማክበር፣ ሚስት ባሏን ማክበር በጣም አስፈላጊ ነው:: ሀናን፣ "ከናትና ካባትሽ ማንን ትወጃለሽ" ብትያት፣ ሁለቱንም ነው የምትልሽ፣ ሁለታችንንም እንድታከብር እንድትወድ እንጂ፣ አንዳችንን ካንዳችን እንድትመርጥ አድርገን አላሳደግናትም:: ወላጆች ቤት ውስጥ ስምምነት ካጡ፣ ልጆች ውጭ ይወጣሉ፤ ወደ መጥፎ ነገርም ይሄዳሉ::
- ሰውን መውደድ እንዳለብን ሁሉ ሰው የእግዚያብሄር ልጅ ስለሆነ፣ ሌላን ማክበር እንዳለብን፣ ለልጆቻችን ልናስተምር ይገባናል:: ሌላን ሰው ስለማገልገል፣ ወላጅ በምሳሌነት ማስተማር አለበት:: ሁሌ ለራሴ ምን ላድርግ በማለት ፋንታ፣ ለሌላስ ምን ላድርግ እንዲሉ አድርገን ማሳደግ አለብን:: እኔ እራሴ፣ ለብዙ አመታት፣ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ፣ በነጻ አገልግሎት ስራ ተሰማርቻለሁ፤ የእርዳታ ኮምፓኒዬ፣ በነጻ የሚሰጠውን ዳቦ እየወሰድኩ፣ ለኢትዮጵያኖች ስደተኞች አድላለሁ:: ሐና፣ ከህጻንነቷ ጀምሮ፣ ከኔ ጋ አብራ እየመጣች ያንን ታይ ነበር እሷም አብራኝ ታገለግል ነበር:: ይህ በልጅነቷ ያየችው ሌላን የማገልገል ልምድ፣ በውስጧ መሰረት እንደሰራ አምናለሁ:: አሁንም ቢሆን፣ አባት እናት የሌላቸው ልጆች ጋ ሄዳ፣ በነጻ ታገለግላለች፤ እሁድ





እሁድም ቤተክርስትያን የልጆች ትምህርት ማስተማር ውስጥ ትሳተፋለች::

- ልጆች፣ መጸሀፍ የማንበብ ልምድ እንዲኖራቸው መጣሩ በጣም አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ:: ሐና መጸሀፍ በጣም ታነባለች፤የሌላ አገር ሰዎች፣ ልጆቻቸው የማንበብ ልምድ እንዲኖራቸው የተቻላቸውን ይጥራሉ:: ለምሳሌ ስሪላንካዎች፣ ቋንቋ እንኳን ባይለምዱ ልጆቻቸውን ላይብረሪ ሁሌ እየወሰዱ ያስነብባሉ እኛ ቋንቋውን ብዙ ባንችል እንኳ፣ እዛ ያሉ ላይብረሪ የሚሰሩ ልጆቻችንን በማንበብ ሊረዱልን የሚችሉ ሰዎች ካሉ መጠየቅ አስፈላጊ ነው::
- ልጆቻችን ሌላን በጭፍን ተከታይ እንዳይሆኑ፣ የራሳቸውን አይምሮ እንዲከተሉ አድርጎ ማሳደግ ተገቢ ነው:: ሥራ ስናስቀጥራቸው ማክዶናልድ፣ በርገር ቤት ብቻ ማድረጉን ትተን፣ ሆስፒታል አካባቢ ላይብረሪ፣ በነጻ እንኳ እንዲሰሩ ብናደርግ፣ ትላልቅ ህልም እንዲቀረጽባቸው ያበረክታል::